የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ የካቲት ፲፱ ቀን ፪ሺ፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No.27
ADDIS ABABA 19th February, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፪/፪ሺ፩ ዓ.ም

የጉምሩክ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፮፻፩

CONTENTS

Proclamation No. 622/2009

Customs Proclamation Page ....... 4601

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፪/፪ሺ፩
## የጉምሩክ አዋጅ

ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣም ህጋዊ ንግድንና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ የጉምሩክ ሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤

ሀገሪቱ የፈረመቻቸው አለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶች ወቅታዊ ሕግና የአሰራር ስርዓት እንዲኖር የሚያስገድዱ በመሆናቸው፤

ኮንትሮባንድና ሌሎች የንግድ ማጭበርበር ወንጀሎች በሕጋዊ የንግድ ዕንቅስቃሴ፣ በህዝብ ደህንነት፣ በመንግሥት ገቢና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ላይ የሚያስከትሉትን ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል የተጠናከረ የህግ ማስከበሪያ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፪/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 622/2009
## CUSTOMS PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to have an expedient and modern customs legal framework which is compatible with the increasingly growing international trade and encourages trade and investment;

**WHEREAS,** international, continental and regional trade agreements to which the country is a party require contemporary customs laws and procedures;

**WHEREAS,** strong system of law enforcement is required to prevent the increasing incidence, from time to time, of contraband and other commercial fraud crimes which are resulting negative impact to legitimate trade, public security, government revenue and other social and economic development;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Customs Proclamation No. 622/2009"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 24.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ዐዋጅ ውስጥ፤

፩/ "እቃ" ማለት ማናቸውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ግዙፍነት የሌላቸው በሕግ እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚታወቁትን ንብረቶችና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን በአገልግሎት ላይ የዋሉ የተፈጥሮ ሀይል ውጤቶችንና የከርሰ ምድር ሀብትን የሚያካትት ሲሆን ገንዘብንም ይጨምራል፤

፪/ "ጭነት" ማለት በማናቸውም የማጓጓዣ አይነት ወደአገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ዕቃ ሲሆን፣ በጉዞ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉትንና የመንገደኞችን የግል መገልገያ ዕቃዎች አይጨምርም፤

፫/ "ቀረጥ" ማለት በትክክል ለእቃው በተደረገ ጠቅላላ ወጪ ላይ ተመሥርቶና የአለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሠረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ታሪፍ ነው፤

፬/ "ታክስ" ማለት ፀንተው በስራ ላይ ባሉ የግብር ሕጎች መሠረት በገቢና በወጪ እቃዎች ላይ እየተጣለ የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፤

፭/ "ወደ አገር ማስገባት" ማለት ማናቸውንም ገቢ ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ማምጣት ወይም እንዲገባ ማድረግ ነው፤

፮/ "ወደ ውጭ አገር መላክ" ማለት ማናቸውንም ዕቃ ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ነው፤

፯/ "የጉምሩክ ክልል" ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፤

፰/ "የጉምሩክ ጣቢያ" ማለት በመግቢያና በመውጫ ወደብ ወይም በመተላለፊያ መንገድ ወይም በጉምሩክ ክልል የሚገኝ በገቢና በወጪ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቁጥጥርና ሥነ ሥርዓት የሚፈፀምበትና ወይም ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሥፍራ ነው፤

፱/ "የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ገቢና ወጪ ዕቃዎች ወይም ተላላፊ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚቆዩበት በባለስልጣኑ ወይም ከባለስልጣኑ ፈቃድ በተሰጠው ሰው የተቋቋመ ማናቸውም የዕቃ ማከማቻ ቦታ ነው፤

፲/ "የመጋዘን ኃላፊ" ማለት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስከሚፈፀምበት ጊዜ ድረስ ዕቃዎች የሚቆዩበት መጋዘንን የሚያስተዳድር ሰው ነው፤

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "goods" means any kind of corporeal chattels and other incorporeal chattels deemed to be corporeal chattels by law including natural forces and resources of an economic value which are employed to use, and includes money;

2/ "cargo" means any goods imported or exported by any means of transport other than goods required for consumption during the voyage onboard of the means of transport and bona-fide personal baggage of passengers;

3/ "duty" means tariff levied and collected on the basis of the actual total costs of any imported or exported goods in accordance with the Customs Tariff Regulations issued pursuant to the International Convention on the Harmonized Commodity Description and Coding System;

4/ "tax" means payment collected in accordance with the existing tax laws on imported and exported goods;

5/ "importation" means bringing or cause to be brought goods into the customs territory;

6/ "exportation" means taking or cause to be taken out goods from the customs territory;

7/ "customs territory" means the territory of Ethiopia;

8/ "customs station" means any place designated as customs office at the port of entry or exit of goods, transit routes or customs area for the control of import and export goods, accomplishment of customs formalities and/or collection of duties and taxes;

9/ "customs warehouse" means any warehouse established by the Authority or a person authorized by the Authority for the deposit of import, export or transit goods until the accomplishment of customs formalities;

10/ "warehouse operator" means a person who administers a customs ware house;

፲፩/ "ማጓጓዣ" ማለት በየብስ፣ በአየር ወይም በውሃ ላይ ሰውን ወይም እቃን የሚያጓጉዝ ማንኛውም የመጓጓዣ ዘዴ ሲሆን እንስሳትን ይጨምራል፤

11/ "means of transport" means any means of conveyance including animals used for carriage of goods and passengers on land, air or water;

፲፪/ "የማጓጓዣ ኃላፊ" ማለት ማናቸውንም ማጓጓዣ በጉዞ ላይ እንዳለ የማዘዝ፣ የመቆጣጠር ወይም ሥራውን የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ወኪሉ ነው፤

12/ "master of means of transport" means a person or an agent to command, supervise or manage any means of transport during the voyage;

፲፫/ "ተሳላፊ ዕቃ" ማለት ማጓጓዣ በመቀየር ወይም በመጣበት ማጓጓዣ በተፈቀደ የመተላለፊያ መሥመር የጉምሩክ ክልልን አቋርጦ የሚሄድ ወይም ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ የሚንቀሳቀስ ዕቃ ነው፤

13/ "transit goods" means the movement of goods from one country to another by crossing the customs territory or from one customs station to another through designated transit route either by the same or changing the means of transport;

፲፬/ "የመተላለፊያ መሥመር" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ገቢና ወጪ ዕቃዎች እንዲጓጓዙበት በባለስልጣኑ የተወሰነ ማናቸውም መንገድ ነው፤

14/ "transit route" mean any route designated by the Authority for the movement of imported or exported goods under customs control;

፲፭/ "የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት አስፈፃሚ" ማለት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን የማስፈፀም ተግባር ለማከናወን የሚያስችል የብቃትና የሙያ ማረጋገጫ የተሰጠው የአስመጪ ወይም የላኪ ወኪል ነው፤

15/ "customs clearing agent" means an exporter or importer or an agent with a certificate of competence and professional qualification authorized to effect customs formalities;

፲፮/ "የጉምሩክ ዲክላራሲዮን" ማለት ወደአገር የሚገቡ፣ ወደ ውጭአገር የሚላኩ ወይም የተሳላፊ ዕቃዎች ዝርዝር የሚገለጽበትና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምበት በባለስልጣኑ የሚዘጋጅ ቅጽ ወይም ሰነድ ነው፤

16/ "customs declaration" means a form or document prepared by the Authority in which the details of import, export or transit goods are described for the accomplishment of customs formalities;

፲፯/ "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት" ማለት ወደአገር የሚገባ፣ ወደውጭ አገር የሚላክ ወይም ተሳላፊ ዕቃ የጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ቁጥጥር ሥር እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም የጉምሩክ አፈፃፀም ሂደት ነው፤

17/ "customs formalities" means any customs operations carried out in connection with importation, exportation and transit of goods from the time of arrival at the customs port until released from the customs control;

፲፰/ "ሰነድ" ማለት ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም በአካል ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚቀርብ ማናቸውም ደረሰኝ፣ ቅጽ ወይም የጽሑፍ ማስረጃ ሲሆን፣ መዝገብን ይጨምራል፤

18/ "document" means an invoice, form or written evidence presented physically or by electronic means to customs to accomplish customs formalities and includes books of records;

፲፱/ "የዋጋ ሰነድ" ማለት በአምራች ወይም በአቅራቢ የተዘጋጀና የተፈረመ ስለእቃ ዋጋ የሚገልፅ ሰነድ ነው፤

19/ "invoice" means a price document prepared and signed by a manufacturer or supplier which shows the commercial value of goods;

፳/ "አንድ አይነት ዕቃዎች" ማለት በአካላዊ ባህሪያቸው፣ በጥራታቸውና በተፈላጊነታቸው አንድ የሆኑና በአንድ አገር የተመረቱ ዕቃዎች ናቸው፤

20/ "identical goods" means goods which are the same in all respects including physical characteristics, quality, reputations and country of origin;

፳፩/ "ተመሳሳይ ዕቃዎች" ማለት በሁሉም አንፃር ባይመሳሰሉም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው፣ ከተመሳሳይ ማቴሪያል የተመረቱ፣ ተመሳሳይ ተግባር ማከናወን የሚችሉና ተመሳሳይ የገበያ ተፈላጊነት ያላቸው ዕቃዎች ሲሆኑ፣ ጥራታቸው፣ በአንድ አገር የተመረቱ መሆናቸው፣ ተፈላጊነታቸውና የንግድ ምልክታቸው ስለተመሳሳይነታቸው ከግምት ውስጥ ይገባል፤

፳፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፫/ "ባለቤት" ማለት ማናቸውንም ዕቃ የመጠቀም፣ የመያዝ፣ ወደሌላ የማስተላለፍ፣ ወደውጭ አገር የመላክ ወይም ወደአገር የማስገባት መብት ያለው ሰው ወይም ወኪሉ ሲሆን፣ እንደባለቤት ሆኖ ዕቃ ለማጓጓዝ የሚረከበውን ኃላፊ ወይም ወኪሉን ይጨምራል፤

፳፬/ "ዕቃ ማስወገድ" ማለት ማናቸውንም ዕቃ በማቃጠል ወይም በሌላ መንገድ ማጥፋት ወይም በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው፤

፳፭/ "የተከለከለ እቃ" ማለት በሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ወደ አገር እንዳይገባ፣ ከአገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ የተከለከለ ማንኛውም እቃ ነው፤

፳፮/ "ገደብ የተደረገበት ዕቃ" ማለት በሕግ በተደነገገ ሥነ ሥርዓት ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር እንዳይገባ ወይም ከአገር እንዳይወጣ ወይም እንዳይተላለፍ ገደብ የተደረገበት እቃ ነው፤

፳፯/ "የጉምሩክ ቦንድ" ማለት ማንኛውም ሰው በውል ውስጥ በተዘረዘሩ ሁኔታዎች መሰረት ግዴታውን ለማሟላትና ለማክበር ከባለስልጣኑ ጋር በሕጋዊ መንገድ የሚገባው አስገዳጅ የዋስትና ውል ነው፤

፳፰/ "የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን" ማለት ዕቃዎች ቀረጥ እስኪከፈልባቸው ድረስ የሚከማቹበትና በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ማናቸውም ስፍራ ሲሆን በተጨማሪ ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ሱቆችን ወይም ቦንድ የተደረጉ ፋብሪካዎችን ያጠቃልላል፤

፳፱/ "ጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ" ማለት ገቢና ወጪ ወይም ተላላፊ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቀው እስከሚለቀቁ ድረስ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው የሚቆዩበት በባለሥልጣኑ የተፈቀደ ዝግ ወይም ክፍት የዕቃ ማከማቻ ቦታ ነው፤

21/ "similar goods" means goods which, although not alike in all respects, have like characteristics, and component materials, perform the same functions and to be commercially interchangeable; and the quality, origin, reputation and the trade mark of which are among the factors to be considered in determining their similarity;

22/ "person" means any natural or juridical person;

23/ "owner" means any person or an agent who has the right to use, possess, transfer, import or export goods into or from the country and includes the master or the agent of the means of transport who, as an owner, receives the goods for conveyance;

24/ "disposal of goods" means the act of destroying goods by way of burning or otherwise or transfer of goods through sale or otherwise;

25/ "prohibited goods" means goods of which the importation, exportation or transit is prohibited by laws or international agreement ratified by Ethiopia;

26/ "restricted goods" means goods which the importation, exportation or transit is restricted unless it is permitted by the competent authority in accordance with legal procedures;

27/ "customs bond" means an undertaking in legal form by which a person enters into a binding arrangement with the Authority to comply with the prescribed conditions;

28/ " customs bonded warehouse" means any premises licensed by the Authority for the deposit of dutiable goods on which duty has not been paid and it includes a duty free shop or bonded factories;

29/ "temporary storage of goods" means an enclosed or open premises approved by the Authority where import, export or transit goods are stored temporarily under customs control pending the completion of customs formalities;

፴/ "የጭነት መግለጫ" ማለት የዕቃ ላኪ፣ ተቀባይ፣ ምልክት፣ ዕሽግ ቁጥር፣ ዓይነት፣ ብዛት፣ ክብደት፣ ዝርዝር፣ የጭነት ዴክላራሲዮን ቁጥርንና የመሳሰሉትን የሚያመለክት ሰነድ ነው፤

፴፩/ "የስሪት አገር የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ እቃ ስለተመረተበት አገር ትክክለኛነት በተመረተበት አገር ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፤

፴፪/ "የሥሪት አገር ደንብ" ማለት በዓለም አቀፍ፣ በአካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ሥምምነቶች መሠረት ዕቃዎች የተሠሩበትን አገር ለመወሰን የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓትና መመዘኛ ነው፤

፴፫/ "ኮንቴይነር" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የተዘጋና ዕቃን ለመያዝ የተሰራ ክፍል ያለው፣ ለተደጋጋሚ አገልግሎት የሚውልና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ የመጓጓዣ ዓይነት ዕቃን በቀላሉ ለማጓጓዝ እንዲቻል ተደርጐ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ የዕቃ መያዣ ነው፤

፴፬/ "በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም" ማለት ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል እንዲገባ፣ ከጉምሩክ ክልል በድጋሚ ወደውጭ አገር እንዲላክ፣ እንዲወገድ፣ እንዲወረስ ወይም ለባለቤቱ እንዲመለስ በጉምሩክ የአሠራር ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፍ ማድረግ ነው፤

፴፭/ "የጉምሩክ ቁጥጥር" ማለት ሕጐችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚፈፀም ዕቃን የመፈተሽ፣ የሰነድን መኖርና ትክክለኛነትን የማረጋገጥ፣ ቃል የተገባለትን የሂሳብ መግለጫና መዛግብትን የመመርመር ተግባር ነው፤

፴፮/ "የጉምሩክ ወደብ" ማለት ለጉምሩክ ሕግ አፈፃፀም ሲባል የገቢ፣ የወጪና ተላላፊ ዕቃዎች የሚራገፉበት፣ የሚቆዩበትና የሚጫኑበት በባለሥልጣኑ የሚወሰን ማናቸውም ስፍራ ሲሆን ደረቅ ወደ ብንም ይጨምራል፤

፴፯/ "የቀረጥ ተመላሽ" ማለት በቀረጥ ተመላሽ የአሠራር ሥርዓት መሠረት ለወጪ ዕቃ ማምረቻ ጥቅም ላይ ለዋለ ጥሬ ዕቃ የተከፈለን ቀረጥና ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲመለስ ማድረግ ነው፤

፴፰/ "የቀረጥ ተመላሽ የአሠራር ሥርዓት" ማለት የወጪ ዕቃን ለማምረት ጥቅም ላይ ለዋለ ግብዓት የተከፈለ ቀረጥ ተመላሽ የሚደረግበት የጉምሩክ የአሠራር ሥርዓት ነው፤

30/ "cargo manifest" means a document which indicate the consignor, consignee, mark, package number, quality, quantity, weight, descriptions, cargo declaration number and other particulars of goods;

31/ "certificate of origin" means a document issued by a competent authority certifying the authenticity of the origin of goods;

32/ "rules of origin" means a procedure and criteria put in place to determine the origin of goods in accordance with international, regional or bilateral trade agreements;

33/ "container" means a receptacle which is fully or partially enclosed with a compartment for containing goods, suitable for repeated use and specially designed to facilitate the carriage of goods by one or more mode of transport;

34/ "customs approved treatment or use of goods" means the placing of goods under customs procedure for their re-exportation from the customs territory, disposal, forfeiture or return to the owner;

35/ "customs control" means the conducting, by the Authority, of examination of goods, verification of the existence and authenticity of documents, examination of the accounts of undertakings and other records to ensure that laws and directives are observed;

36/ "customs port" means any place that is designated by the Authority for unloading, storage and loading of import, export and transit goods for the purpose of enforcing customs laws and includes dry port;

37/ "draw back" means a refund of all or part of any import duties and taxes on inputs used to produce export goods in accordance with the draw back procedure;

38/ "draw back procedure" means the customs procedure which provides a refund to be made on the export of goods in respect of the duties and taxes charged on inputs used in their productions;

፴፱/ "የዕቃ ፍተሻ" ማለት የዕቃውን የስሪት ሃገር፣ የመጣበትን ሃገር፣ ባህሪ፣ ሁኔታ፣ አይነት፣ ብዛት፣ ዋጋ፣ የታሪፍ አመዳደብ፣ በዕቃ ማሳወቂያ ዴክላራሲዮን ቅፅ ውስጥ በቀረበው ዝርዝር መሰረት የተሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ በጉምሩክ የሚፈፀም አካላዊ ምርመራ ሲሆን፣ በተጓዦች የሻንጣ ማስታወቂያ ዴክላራሲዮን መሠረት የሚደረግ የዕቃ ምርመራን ይጨምራል፤

፵/ "የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር" ማለት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ክፍያ ነፃ የሆነ ዕቃ ለዓለም አቀፍ መንገደኞችና ለሌሎች የቀረጥ ነፃ ባለመብቶች የሚሸጥበት በዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎች ቦታዎች የሚቋቋም መደብር ነው፤

፵፩/ "የጉምሩክ ማቋረጫ" ማለት ሰውንና መጓጓዣን እንዲሁም የገቢ፣ የወጪና ተላላፊ ዕቃዎችን ለማስገባት፣ ለማስወጣትና ለማሸጋገር የተፈቀደ የድንበር መስመር ሲሆን ዓለምአቀፋዊ የድንበር ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚፈጸምባቸውን ሥፍራዎች ይጨምራል፤

፵፪/ "የጉምሩክ የጠረፍ መስመር" ማለት ከኢትዮጵያ የጉምሩክ ድንበር መስመር ወደ ውስጥ እስከ ፲፭ ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ ሥፍራ ነው፤

፵፫/ "የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት" ማለት በባለሥልጣኑ ለተለቀቀ ዕቃ ቀርቦለት የነበረው የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ እቃውን በማስመጣት ወይም ወደውጭ በመላክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈ ሰው እጅ የሚገኙ መዛግብትን፣ ሪኮርዶችን፣ የንግድ አሠራሮችን እና ሌሎች አግባብነት ያለቸውን ጉምሩክ ነክ የንግድ መረጃዎችን የመመርመር ሥረዓት ነው፤

፵፬/ "ድንገተኛ ፍተሻ" ማለት ዕቃ ከጉምሩክ ከተለቀቀ በኋላ በስጋት ሥራ አመራር ሥርዓት መሠረት ወይም በተጨባጭ መረጃ ላይ በመመስረት በድጋሚ የሚከናወን ፍተሻ ነው፤

፵፭/ "የሥጋት ሥራ አመራር" ማለት በጉምሩክ ክልል በሚገቡና በሚወጡ ዕቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የሥጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን አሰራር ነው፤

፵፮/ "ዕቃን መልቀቅ" ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያለ ዕቃ ለተገለጸለት ዓላማ እንዲውል የሚለቀቅበት ሥርዓት ነው፤

39/ "examination of goods" means the physical examination of goods by customs to satisfy that the origin, country of export, nature, condition, quality, quantity, tariff classification and value of the goods are in accordance with particulars furnished in the goods declaration and includes examination of goods on the basis of baggage declarations by travelers;

40/ "duty free shop" means a shop established in international airports or, where necessary, in other places in which duty and tax free goods are sold to international passengers and other duty free privileged persons;

41/ "customs crossing" means a designated point of crossing of the customs boundary line for persons and means of transport as well as for import, export and transit goods, and includes international border traffic routes;

42/ "customs frontier strip" means a 15-kilometer wide part of the customs territory from the customs boundary line of Ethiopia;

43/ "post clearance audit" means a process which enables the Authority, after the release of goods, to verify the accuracy of customs declarations through the examination of the books, records, business systems and other relevant customs commercial data held by persons directly or indirectly involved in the import or export of goods;

44/ "surprise check" means the re-examination of goods after their customs release based on risk management or receipt of concrete evidence;

45/ "risk management" means a system of management by which different risk bands are categorized on the basis of their risk levels in light of fair customs service provision and control with respect to goods brought to or taken out of customs territory;

46/ "release of goods" means a procedure whereby goods under customs control are released for the purposes declared;

፵፯/ "የጉምሩክ ሹም" ማለት የጉምሩክ ሥራን በኃላፊነት እንዲያከናውን የተመደበ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ሲሆን የምርመራ ሹምን ይጨምራል፤

፵፰/ "ዋስትና" ማለት ለጉምሩክ የተገባ ግዴታ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ፣ የባንክ ጋራንቲ፣ የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ነው፤

፵፱/ "መያዝ" ማለት ሕግን ከመፈጸም ወይም ከማስከበር ጋር በተያያዘ እቃን ወይም ሰነድን በቁጥጥር ስር ማድረግ ነው፤

፶/ "በሕጋዊ እቃ ከለላነት" ማለት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ከቀረበበት እቃ ጋር በዓይነት፣ በመጠን፣ በብዛት፣ በዋጋ ወይም በሥሪት አገር ልዩነት ያለውን እቃ የመቀላቀል ድርጊት ነው፤

፶፩/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤

፶፪/ "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፤

፶፫/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል::

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ወጥነት ባለው መልኩ ተፈፃሚ ይሆናል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ ከጉምሩክ ክልል በሚወጡ፣ በጉምሩክ ክልል በሚተላለፉና የጉምሩክ ቁጥጥር በሚያደርግባቸው ዕቃዎች እንዲሁም ከጉምሩክ አሰራር ጋር በተያያዘ መብት በተሰጣቸውና ግዴታ በተጣለባቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

## ፬. የጉምሩክ አሰራር መርሆዎች

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ግልፅነትንና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ተገቢ መረጃን መሠረት ባደረገና የሥጋት ስራ አመራር ሥርዓትን በተከተለ የምዘና መመሪያ አማካኝነት በሚደረግ የጉምሩክ ቁጥጥር ለተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆን አለበት::

47/ "customs officer" means an official or employee assigned to discharge customs operations and includes an investigation officer;

48/ "security" means cash deposit, bank guarantee, insurance bond or an undertaking provided for ensuring the fulfillment of an obligation to the customs;

49/ "seizure" means taking possession of goods or documents in relation with law execution and enforcement;

50/ "under the cover of legally declared goods" means the act of intermingling of goods that are different in type, size, quantity, value or country of origin with the declared goods;

51/ "Authority'' means the Ethiopian Revenue and Customs Authority;

52/ "Director General" means the Director General of the Authority;

53/ any expression in the masculine gender includes the femine.

## 3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall be applied in the entire territory of Ethiopia uniformly.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, this Proclamation shall regulate import goods, export goods, goods in transit and any goods subject to customs control including rights and obligations of persons who takes part in customs formalities.

## 4. Principles of Customs Procedures

1/ The customs procedures prescribed in this Proclamation shall be applied to effect customs control in a manner assuring transparency and accountability based on appropriate information and the principles of risk management and thereby create conducive condition for trade facilitation.

፪/ የጉምሩክ አሰራሮች በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፈርቶችን የተከተሉና ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በመደጋገፍና በመመካከር መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለመተንተን፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው::

## ክፍል ሁለት

## የጉምሩክ አሠራርና ቁጥጥር

### ፭. በጉምሩክ ማቋረጫና የጠረፍ መስመር ስለሚንቀሳቀስ ዕቃ

፩/ የጉምሩክ ጠረፍ መስመርና የጉምሩክ ማቋረጫ እንቅስቃሴ በሕግ ወይም በአለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ድንበር ለማቋረጥ ወይም ዕቃን ለማጓጓዝ መብት ለተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ያገለግላል::

፪/ በጉምሩክ የጠረፍ መስመር ውስጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያላቸው ሰዎች በጉምሩክ ማቋረጫዎች በኩል ለኑሯቸው አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ወይም በአለም አቀፍ ስምምነት ድንጋጌዎች መሰረት የተፈቀዱ ዕቃዎችን የማጓጓዝ መብት ይኖራቸዋል::

፫/ በጉምሩክ የጠረፍ መስመር አካባቢ የሚኖሩ ሐኪሞች፣ የእንስሳት ሐኪሞች፣ ሌሎች የሕክምና ሠራተኞች እና የሕዝብን ሕይወትና ንብረት በማዳን ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ለሥራቸው የሚያስፈልጓቸውን መድሃኒቶችና መሳሪያዎች አግባብ ያለው የመንግሥት አካል በሚሰጣቸው ፈቃድ መሰረት በጉምሩክ ማቋረጫዎች በኩል ማጓጓዝ ይችላሉ::

### ፮. የጉምሩክ ወደቦችና የመተላለፊያ መንገድ

፩/ ገቢ፣ ወጪ እና ተላላፊ ዕቃዎች በተወሰነ የጉምሩክ ወደብ ወይም ማቋረጫ በኩል በመግባት በተፈቀዱ የመተላለፊያ መንገዶች መጓጓዝ አለባቸው::

፪/ የጉምሩክ ወደቦች፣ ማቋረጫዎችና የመተላለፊያ መንገዶች በባለሥልጣኑ ይወሰናሉ፤ ይህም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ ይገለጻል::

2/ Customs procedures shall be based on internationally accepted information technology standards and shall be carried out in consultation with relevant parties in order to gather, analyze, use and store information.

## PART TWO

## CUSTOMS PROCEDURE AND CONTROL

### 5. Movement of Goods across Customs Crossings and within Customs Frontier Strip

1/ Customs frontier strip and customs crossing shall be used for border crossing or transport of goods only by persons entitled to such activities on the basis of laws or international agreements.

2/ Persons having real property within customs frontier strip shall be entitled to transport goods necessary for their living and work on their property as well as other things stipulated by international agreements.

3/ Doctors, veterinarians, other medical staff and rescue workers residing within customs frontier strip may carry instruments and medications needed for their activities through frontier crossings when approved by pertinent authority.

### 6. Customs Ports and Transit Routes

1/ Import, export and transit goods shall enter through prescribed customs ports or customs crossings and be transported through prescribed routes.

2/ Customs ports, custom crossings and transit routes shall be determined by the Authority and be publicized by public notice issued by the Authority.

**፯. <u>በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዕቃው ባህሪ፣ ብዛት፣ ሥሪት ሀገር፣ መድረሻ ሥፍራው ወይም በአላላክ ሁኔታው ላይ ልዩነት ሳይደረግ በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት በጉምሩክ አሰራር ተቀባይነት ያገኘ የዕቃ አያያዝ ወይም የአጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የዕቃ አያያዝ ወይም አጠቃቀም ከሕዝብ ሞራል አጠባበቅ፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳት ወይም ከዕፅዋት ጤንነትና ሕይወት አጠባበቅ፣ ከታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ወይም ከአእምሯዊ ንብረት አጠባበቅ ወይም በሌላ ሕግ ከተፈቀደ የዕቃዎች አያያዝ ወይም አጠቃቀም ጋር የሚቃረን ከሆነ በሥራ ላይ አይውልም::

**፰. <u>ስለገቢ፣ ወጪና ተላላፊ ዕቃዎች</u>**

፩/ ለጉምሩክ ሥራ አፈፃፀም የሚከተሉት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥርና ጥበቃ ሥር ይሆናሉ፤

ሀ) ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ጉምሩክ ወደብ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክን ሥነ-ሥርዓት አሟልተው አስመጪው ወይም ወኪሉ እስከሚረከብ፤

ለ) ወደጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚወጡ፤

ሐ) ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች ወደጉምሩክ ወደብ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞ እስከሚላኩ፤

መ) ተላላፊ ዕቃዎች እንዲንቀሳቀሱ ከተፈቀደበት ጊዜ ጀምሮ ለመተላለፍ የተሰጠው የጊዜ ገደብ እስከሚያበቃ፤

ሠ) ባለቤት የሌላቸው፣ የተተው፣ የተወረሱ፣ ወይም በኮንትሮባንድ የተያዙ ወይም ይህንን አዋጅና ባለሥልጣኑ የሚያስፈፅማቸውን ሌሎች ህጎች በመተላለፍ የተያዙትን ዕቃዎች እስከሚወገዱ ድረስ::

፪/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለፀው መሠረት በጉምሩክ ቁጥጥርና ጥበቃ ሥር ያሉ ዕቃዎች ወደ ተከማቹበት ሥፍራ መግባት፣ ዕቃዎችን መክፈት ወይም ማናቸውንም ነገር በዕቃዎች ላይ መፈፀም አይችልም::

**7. <u>Customs Approved Treatment or Use of Goods</u>**

1/ Unless otherwise provided in this Proclamation, customs approved treatment or use of goods shall be applied in accordance with standards prescribed without any discrimination as to the nature, quantity, origin, destination or shipment conditions of the goods.

2/ Sub-article (1) of this Article may not be applicable if such application is contrary to any measure taken for the protection of public morality, the protection of health and life of humans, animals or plants, the protection of historical and cultural heritages or intellectual property rights, or other specific treatment or use of goods provided by law.

**8. <u>Import, Export and Transit Goods</u>**

1/ For the purpose of carrying out customs activities, the following goods shall be under customs supervision and control:

a) imported goods, from the time of their arrival at customs port until the completion of customs formalities and they are received by the importer or his agent;

b) goods deposited to customs warehouse, from the time they are deposited until they are removed from the warehouse;

c) export goods, from the time they entered customs port until the completion of customs formalities and be exported;

d) goods in transit, from the time their movement is allowed until the completion of transit procedure;

e) goods found with out owner, abandoned, forfeited or contraband goods or goods forfeited for violating the provisions of this Proclamation or other laws enforced by the Authority until their disposal.

2/ Without prior authorization of the Authority, no person may be allowed to enter customs warehouse in which goods, put under the supervision and control of customs in accordance with sub Article(1) of this Article, are deposited, or open or do any acts on such goods.

፱. <u>በፖስታ ስለሚላኩ ዕቃዎች</u>

፩/ ማንኛውም ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይፈፀምበት በፖስታ ቤት በኩል ወደ አገር ሊገባ ወይም ከአገር ሊወጣ አይችልም::

፪/ በፖስታ ቤት በኩል ወደ አገር የሚገባ እና ከአገር የሚወጣ እቃ በሥፍራው በሚገኝ የጉምሩክ ሹም ቁጥጥር እየተደረገበት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ይፈፀምበታል:: ሆኖም የጉምሩክ ጣቢያ በማይኖርበት ጊዜ የፖስታ ቤት ሥራውን የሚያከናውነው አካል ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ የውክልና ሥልጣን የሚሰራበት ሁኔታ ሊዘረጋ ይችላል::: ዝርዝር አፈፃፀሙ በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

፫/ በፖስታ ቤት በኩል ወደ አገር ለሚገባ እቃ በላኪው የተሰጠ መግለጫ ወይም በእቃው ላይ የተለጠፈ ምልክትና ከእቃው ጋር የቀረበ ማናቸውም ደጋፊ ሰነድ፣

ሀ) የእቃው ዋጋ በባለስልጣኑ ከተወሰነው እኩል ወይም ከዚያ በላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ፣

ለ) ወደ አገር ለመግባት ሠርተፊኬት የሚያስፈልገው እቃ መሆኑን የሚገልፅ ከሆነ፣ ወይም

ሐ) የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሞበት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደ አገር እንዲገባ የሚፈቀድ እቃ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነ፣

ተቀባይነት ያገኘ ዲክላራሲዮን እንደ ቀረበበት እቃ ተቆጥሮ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ይፈፀምበታል:: ሆኖም በዚህ ሁኔታ የገባ ማናቸውም እቃ አስፈላጊ መሆኑ ከተረጋገጠ የተለየ ዲክላራሲዮን እንዲቀርብበት ይደረጋል::

፬/ በፖስታ ቤት በኩል ወደ ውጭ አገር የሚላክ ማናቸውም እቃ ስለመላኩ ሰርተፊኬት የማያስፈልገው ከሆነ፣ ከተወሰነው ዋጋ በላይ ካልሆነ ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሊፈጸምበት የሚገባ ካልሆነ የጉምሩክ ቁጥጥር አይደረግበትም::

፲. <u>የተከለከሉና ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች</u>

፩/ የተከለከለ ዕቃ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች መሠረት አግባብ ያለው እርምጃ እስከሚወሰድበት ጊዜ ድረስ በጉምሩክ ቁጥጥርና ጥበቃ ስር ይቆያል::

9. **<u>Postal Consignment</u>**

1/ Goods imported or exported through post office shall not be released without accomplishing customs formalities.

2/ Customs formalities with respect of goods imported or exported through post office shall be accomplish under the control and supervision of customs officer. Where there is no customs office, the Authority may delegate such power to the authorized post office. The details shall be prescribed by directive to be issued by the Authority.

3/ Where any form completed by the sender or label and supporting documents produced in respect of goods imported through post office shows that:

a) the goods have a value equal to or exceeding from the value determined by the authority;

b) importation of the goods require certification; or

c) the goods require to be placed under customs procedure for home consumption;

such form or label and supporting documents shall be considered as an acceptable declaration for the purpose of customs formalities; provided, however, that a separate goods declaration shall be required where necessary.

4/ Where any goods to be exported through post office, require no certification, have a value not exceeding the prescribed amount or are exempted from customs formalities, they shall not be subject to customs supervision.

10. **<u>Prohibited and Restricted Goods</u>**

1/ Prohibited goods shall be under customs supervision and control until appropriate measure is taken in accordance with this Proclamation and other laws.

፪/ ገደብ የተደረገበት ዕቃ ገደቡን ከሚያስከብረው መሥሪያ ቤት የተሰጠ ፈቃድ እስከሚቀርብበት በጉምሩክ ቁጥጥርና ጥበቃ ስር ይቆያል፡፡ ሆኖም ገደብ አስከባሪው መሥሪያ ቤት የሚሰጠው ፈቃድ በ፴ ቀናት ውስጥ ለጉምሩክ ካልቀረበ እቃው ከሀገር እንዳይወጣ ወይም ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

፫/ ገደብ የተደረገበት ዕቃ ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ በጉምሩክ ከተገለ ፀበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ከሀገር ካልወጣ እንደተተወ እቃ ይቆጠራል፡፡

## ፲፩. የጉምሩክ ቁጥጥር

፩/ ባለስልጣኑ የጉምሩክ ሥርዓቶች በተግባር ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ በሥራ ላይ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አግባብነት ያላቸውን ማናቸውም ዓይነት እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ ዕቃዎች ከጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ጀምሮ የጉምሩክ ሥርዓት ተጠናቆ ከጉምሩክ ክልል እስኪወጡ ድረስ በአይነት፣ በቅርፅ፣ በይዘትና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ያልተለወጡ ሆነው መቆየታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ በጉምሩክ የቁጥጥር ሥርዓት መሠረት የሚወሰዱት እርምጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤

ሀ) ዕቃዎችን በጉምሩክ ወደብ ውስጥ በተቋቋመ ጊዜያዊ ማከማቻ፣ በጉምሩክ ጣቢያ፣ በደረቅ ወደብ፣ በጉምሩክ መጋዘን፣ በመተላለፊያ መንገድ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው ማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ የመፈተሽ፣ የመከታተልና ጥበቃ የማድረግ፤

ለ) በመረጃና በስጋት ሥራ አመራር ላይ ተመርኩዞ ፍተሻ የተከናወነበትን ወጪ ወይም ገቢ ዕቃ በድጋሚ እንዲፈተሽ የማድረግ፤

ሐ) ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ ከአገር ወጥቷል ብሎ ማረጋገጫ የመስጠት፤

መ) የጉምሩክ ማህተሞችን ማድረግ፣የታዘዙ ሰነዶችን የመስጠትና የማረጋገጥ፤

ሠ) የዕቃዎቹ ዓይነትና ሁኔታ አለመለወጡን ለማረጋገጥ ናሙናዎችን፣ መግለጫዎችንና ፎቶዎችን የመውሰድ፤

2/ Restricted goods shall be under customs supervision and control until a permit issued by the office controlling its importation or exportation is presented; provided, however, that it shall be re-exported to the country from which it is imported or, in the case of export, it shall be barred from departing from Ethiopia, unless such permit is presented within 30 days.

3/ Where restricted goods are not re-exported within 30 days from the date of notification, it shall be considered as abandoned goods.

## 11. Customs Control

1/ The Authority may, in accordance with conditions laid down by the provisions in force, take any measure it deems necessary to ensure that custom rules are applied.

2/ Unless otherwise provided by this Proclamation, the Authority shall ensure that goods remain the same in kind, form, quality and in any other respect from their introduction into the customs territory till the end of customs procedure.

3/ Measures to be taken under customs control include:

a) examining, surveillance and safeguarding of goods at a temporary shelter in customs port, customs station, customs warehouse, dry port, transit routes or any other place determined by the authority;

b) re-examination of imported or exported goods based on information and risk management;

c) certification of exported goods;

d) affixing of customs seals, issuance and verifying of prescribed documents;

e) taking samples, prospectus, photos and other data for the purpose of ascertaining non-alteration in the kind and conditions of goods;

ረ) የተጓዦችን ሻንጣዎችና ሌሎች ዕቃ ዎች የመፈተሸ::

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሐ) መሠረት ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ ከአገር ወጥቷል ተብሎ በባለሥልጣኑ ማረጋገጫ የሚሰጠው ከኢትዮጵያ መውጫ በሆነው የመጨረሻ ጣቢያ ከሚገኘው የጉምሩክ ሹም ዕቃው ከአገር መውጣቱን የሚገልጽ ማረጋገጫ ወደ ባለሥልጣኑ አውቶሜሽን ሲስተም ሲገባ ወይም በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችና በጽሁፍ ሲደርስ ብቻ ነው::

## ክፍል ሦስት

## የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም

### ምዕራፍ አንድ

### ስለጉምሩክ ዲክላራሲዮንና ስለ ተላላፊ ዕቃዎች ስነ ስርዓት አፈጻጸም

**፲፪. የጉምሩክ ዲክላራሲዮን**

፩/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በፅሁፍ፣ በቃል፣ በአካል እንቅስቃሴ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ሊቀርብ ይችላል::

፪/ በጽሁፍ የሚቀርብ ዲክላራሲዮን ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ መሞላት፣ መፈረ ምና ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም አስፈ ላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን በሙሉ መያዝ አለበት::

፫/ በቃል፣ በአካል እንቅስቃሴ ወይም በኤሌክት ሮኒክስ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የሚቀርብበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፬/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር በአስመጪው ወይም በላኪው ወይም በወኪሉ መቅረብ አለበት::

**፲፫. ከጉምሩክ ዲክላራሲዮን ጋር በአባሪነት ስለሚ ቀርቡ ሰነዶች**

፩/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በሚቀርብበት ጊዜ የሚከተሉት ሰነዶች ዋና ቅጂ በባለሥልጣኑ በሚወሰነው ብዛት ተዘጋጅተው በአባሪነት መቅረብ አለባቸው፤

ሀ) የማጓጓዣ ሰነድ፤

ለ) የዋጋ ሰነድ፤

ሐ) የባንክ ፈቃድ፤

መ) የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፤

f) examining luggage and other goods carried by travelers.

4/ Exported goods certification shall be issued pursuant to sub-article 3(c) of this Article only when the information from the customs officer at the end of the customs checkpoint reach the Authority through its automated information network or delivered in writing through other communication media.

## PART THREE

## CUSTOMS FORMALITIES

### CHAPTER ONE

### CUSTOMS DECLARATION AND TRANSIT PROCEDURES

**12. Customs Declaration**

1/ Customs declaration may be made in written form, orally, by bodily action or electronically.

2/ Customs declaration to be presented in written form shall be filled in the prescribed form, signed and contain all the particulars necessary for completing customs formalities.

3/ The Authority shall issue directives on conditions of making customs declaration orally, by bodily action or electronically.

4/ Customs declaration, together with all documents required to be produced for the completion of customs formalities, shall be presented by an importer or exporter or by his agent.

**13. Supporting Documents of Customs Declaration**

1/ On the presentation of customs declaration, the following original supporting documents shall be supplied to customs in a number of copies determined by the Authority:

a) transportation document;

b) invoice;

c) bank permit;

d) packing list;

ሠ) የስሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤ እና

ረ) ሌሎች ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች::

፪/ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ሰነዶች ቅጂ ሊቀበል ይችላል::

፫/ ወደ ውጭ ሀገር ለሚላክ ዕቃ የሚጠየቀው የማጓጓዣ ሰነድ ዕቃውን ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ የወጣውን ወጪ የሚያሳይ የሀገር ውስጥ ማጓጓዣ ሰነድ ነው::

፬/ ባለሥልጣኑ በውጭ አገር ቋንቋ የቀረበ ሰነድ በሕጋዊ ተርጓሚ ወደ አማርኛ ወይም እንደሁኔታው ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል::

፭/ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ ከዲክላራሲዮኑ ጋር አባሪ ሆነው የቀረቡ ሰነዶችና ዲክላራሲዮኑ እንደ አንድ የማይነጣ ጠል ሕጋዊ ሰነድ ሆነው ያገለግላሉ::

## ፲፬. ቀለል ያለ የዲክላራሲዮን አቀራረብ

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ፣

ሀ) የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የተወሰኑ ዝርዝሮችን ሳይዝ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት ሰነዶች የተወሰኑትን በአባሪነት ሳይዝ እንዲቀርብ፣

ለ) የንግድ ወይም አስተዳደራዊ ሰነዶችን ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምባቸው ከሚጠይቅ ሰነድ ጋር በማያያዝ በጉምሩክ ዲክላራሲዮን ምትክ እንዲቀርቡ፣

ሐ) የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀምባቸው የተመዘገቡ ዕቃዎችን ለጉምሩክ እንዲያቀርብ በዲክላራሲዮን አቅራቢው ላይ የተጣለው ግዴታ እንዲነሣ፣ ሊፈቅድ ይችላል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ዝርዝር አፈጻጸም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

e) certificate of origin; and

f) other necessary documents prescribed by directives issued by the Authority.

2/ Where there are adequate reasons, the Authority may accept copies of the documents listed under sub-article (1) of this Article.

3/ Transportation document that is required in support of export goods shall be a document that is used as evidence for the cost of transportation of goods up to the customs point of exit.

4/ The Authority may require any document presented in a foreign language to be translated into Amharic or, as it may be appropriate, into English by an official translator.

5/ Supporting documents and customs declaration shall constitute a single indivisible legal instrument upon acceptance of the declaration.

## 14. Simplified Declaration

1/ Without prejudice to the provisions of this Proclamation regarding customs formalities, the Authority may permit simplified declaration in the following manner:

a) the customs declaration to omit certain particulars or some documents referred to in sub-article (1) of Article 13 of this Proclamation;

b) commercial or administrative documents, accompanied by a request for goods to be placed under customs procedure, to be presented in place of customs declaration;

c) to relieve a person presenting a declaration from his obligation to present to the customs the goods in respect of which customs procedure is to be applied.

2/ The specific application of the provisions of this Article shall be prescribed by directives to be issued by the Authority.

## ፲፭. የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ስለሚቀርብባቸው ዕቃዎች

፩/ ማናቸውም ወደ ሀገር የሚገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ይቀርብበታል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በፅሑፍ የማይቀርብባቸውን ዕቃዎች ባለሥልጣኑ በመመሪያ ሊወስን ይችላል::

፫/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የቀረበለት ማናቸውም ዕቃ፣

ሀ) ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የመጣ ነው ተብሎ የተመዘገበ ከሆነ ቀረጥ የሚከፈልበት፣ ከቀረጥ ነፃ የተደረገ ወይም የቀረጥ ተመላሽ የሚጠየቅበት መሆኑ ተለይቶ መመልከት አለበት፤

ለ) ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ነው ተብሎ የተመዘገበ ከሆነ በሄደበት ሀገር የሚቀር ወይም በጊዜያዊነት ከሀገር ወጥቶ ተመልሶ ወደ ሀገር የሚገባ መሆኑ ተለይቶ መመልከት አለበት::

፬/ ባለሥልጣኑ በባህሪያቸው ወይም በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት ዕቃዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት እንዲፈፀምባቸው ሊፈቅድ ይችላል:: ዝርዝሩ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## ፲፮. የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ስለማሻሻል

፩/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ከቀረበ በኋላ አስመጪ ወይም ላኪው ወይም ወኪሉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት በዲክላራሲዮኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት መግለጫዎች መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን እንዲያሻሽል ባለሥልጣኑ ሊፈቅድለት ይችላል:: ሆኖም የሚደረገው ማሻሻያ አስቀድሞ መግለጫ ለተሠጠባቸው ዕቃዎች ካልሆነ በስተቀር በሌሎች እቃዎች ላይ ዲክላራሲዮኑ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የሚያደርግ አይሆንም::

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ እቃዎቹን እንደሚፈትሽ ለአስመጭው ካስታወቀው ወይም በቀረበው የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ውስጥ የሠፈሩት ዝርዝሮች ትክክለኛ አለመሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ወይም እቃው ለአስመጪው ከተለቀቀ በኋላ ማሻሻያ ማድረግ አይፈቀድም::

## 15. Goods Subject to Customs Declaration

1/ Any import, export or transit goods shall be subject to customs declaration.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, goods exempted from written customs declaration may be determined by directives issued by the Authority.

3/ Any goods in respect of which customs declaration is presented shall, in the declaration, be identified as:

a) dutiable, duty free or under duty-draw-back import regime, if entered for home consumption;

b) an outright export or temporary export, if entered for export.

4/ The Authority may allow goods to be cleared urgently due to their nature or the service they are required for. The details shall be prescribed by directives to be issued by the Authority.

## 16. Amendment of Declaration

1/ The Authority may permit the importer or exporter or his agent, at his request, to amend one or more of the particulars of a customs declaration already presented; provided, however, that such amendment may not have the effect of rendering the declaration applicable to goods other than those originally declared.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, any amendment may not be permitted after the Authority has informed the importer that it intends to examine the goods or it has established that the particulars are incorrect or the goods have been released to the importer.

## ፲፯. ዲክላራሲዮንን ስለመሠረዝ

፩/ አስመጪው ወይም ላኪው ወይም ወኪሉ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ከቀረበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ ፭ ቀናት ድረስ ቀጣዩን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ካልፈፀመ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል::

፪/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የቀረበው በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ወይም ከጉምሩክ የአሠራር ደንቦች ውጪ መሆኑ ከተረጋገጠ አስመጪው ወይም ላኪው ወይም ወኪሉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ሊሰረዝ ይችላል::

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ባለሥልጣኑ ዕቃዎቹን እንደሚፈትሽ ካስታወቀ በኋላ የሚቀርብ የዲክላራሲዮን ይሰረዝልኝ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም::

## ፲፰. ስለ ጉምሩክ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ማግኘት

፩/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በባለሥልጣኑ ተቀባይነት የሚያገኘው ዲክላራሲዮኑና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫(፩) ላይ የተዘረዘሩት አባሪ ሰነዶች ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን በሚገባ መያዛቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው::

፪/ በተለየ ሁኔታ በግልጽ ካልተደነገገ በቀር የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በቀረበበት ቀን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ የሕግ ድንጋጌዎች ዲክላራሲዮኑ የቀረበለትን ዕቃ በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናሉ::

፫/ ባለሥልጣኑ የቀረበለት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሀ) ከዲክላራሲዮኑ ጋር አብረው የቀረቡ ሰነዶችን ይመረምራል፤

ለ) በዲክላራሲዮኑ ውስጥ የሠፈሩ መግለጫዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሌሎች ሰነዶች እንዲቀርቡለት ሊጠይቅ ይችላል፤

ሐ) ዕቃዎቹን ለመመርመርና የምርመራና ትንተና ናሙናዎችን ለመውሰድ ይችላል::

፬/ ዕቃዎቹ በሚመረመሩበት ወይም ናሙናዎች በሚወሰዱበት ወቅት የጉምሩክ ዲክላራሲዮኑን ያቀረበው ሰው በሥፍራው የመገኘት መብት ይኖረዋል፤ ሆኖም በሥፍራው ካልተገኘ ባለሥልጣኑ ዕቃ የመመርመር ወይም ናሙና የመውሰድ ተግባሩን ያከናውናል::

## 17. Cancellation of Declaration

1/ Where the importer or exporter or his agent fails to proceed with the customs formalities within five days after the presentation of a customs declaration or after completion of the preparation of an assessment notice, the customs declaration may be cancelled.

2/ Customs declaration may be cancelled upon the request of the importer or exporter or his agent, where it is proved that the declaration has been presented contrary to provisions of this Proclamation or in any inappropriate customs procedure.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, the request for cancellation may not be permitted where the Authority has informed of its intention to examine the goods.

## 18. Acceptance of Customs Declaration

1/ The Authority shall accept customs declaration where the declaration and supporting documents described under Article 13(1) of this Proclamation contain the necessary particulars required for the completion of customs formalities.

2/ Unless otherwise expressly provided, all provisions of the law, relating to customs formalities, in force on the day of presentation of a customs declaration shall be applied with respect to the goods for which the declaration is presented.

3/ The Authority may, for the verification of customs declaration presented to it:

a) examine the documents accompanying the customs declarations;

b) request the presentation of other documents for the purpose of verifying the accuracy of the particulars in the declaration;

c) examine the goods and take samples for examination and analysis.

4/ The person who presented a customs declaration shall be entitled to be present when the goods are examined or samples are taken; provided, however, that if he fails to appear, the Authority shall proceed to conduct the examination or to take the samples in his absence.

፭/ ዕቃዎቹ ወደሚፈተሹበት ወይም ናሙናዎቹ ወደሚወሰዱበት ሥፍራ ለማጓጓዝና ለምር መራ ወይም ናሙናዎችን ለመውሰድ የሚያ ስፈልገው ማናቸውንም የዕቃዎች አያያዝ በአስመጭው ወይም በላኪው ወይም በወኪሉ ኃላፊነትና ወጪ የሚፈጸም ይሆናል:: ሆኖም የምርመራና ትንተና ወጪ በባለሥልጣኑ የሚሸፈን ይሆናል::

፮/ በሕጉ መሠረት ለተወሰዱ ናሙናዎች ባለሥልጣኑ ለአስመጪው ወይም ለላኪው ወይም ለወኪሉ የካሣ ክፍያ የመፈጸም ኃላፊነት የለበትም::

፯/ ምርመራ የተደረገባቸው ዕቃዎች በጉምሩክ ዲክላራሲዮን ከተሸፈኑት ዕቃዎች ውስጥ ከፊል ብቻ ከሆኑ፣ የምርመራው ውጤት በዚያ ዲክላራሲዮን ለተሸፈኑት ዕቃዎች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

፰/ አስመጭው ወይም ላኪው ወይም ወኪሉ የተደረገው ከፊል ምርመራ የቀሩትን ዕቃ ዎች በተመለከተ ተቀባይነት እንደሌለው ካሰበ፣ በዕቃዎቹ ላይ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል:: ለተጨማሪው የምርመራና ትንተና ሥራ የሚያስፈልገውንም ወጪ ይሸፈናል::

፱/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮኑ ማረጋገጫ የማይከናወንበት ከሆነ፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓቱ ዲክላራሲዮኑ ላይ በገለፀው ዝርዝር መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል::

፲/ ስለሰነዶችና ዕቃዎች ምርመራ ባለሥልጣኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፱. ስለተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም

፩/ በተላላፊነት የተመዘገበ ማናቸውም ዕቃ የጉ ምሩክ ቀረጥና ሌሎች ክፍያዎች ሳይፈፀም በት በዚህ አዋጅ የተደነገገው የጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገበት በጉምሩክ ክልል ውስጥ በሚገኝ የመተላለፊያ መንገድ ሊንቀ ሳቀስ ይችላል::

፪/ የተላላፊ ዕቃ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም የሚጀ መረው በጉምሩክ ክልል የመግቢያ በር ሲሆን፣ የሚጠናቀቀው ዕቃው በሚቀርብበት የመድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ ነው::

፫/ ባለሥልጣኑ ስለተላላፊ ዕቃዎች አፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

## ፳. ስለተላላፊ ዕቃዎች እንቅስቃሴ

፩/ ማናቸውም ተላላፊ ዕቃ እንቅስቃሴውን ከማ ጀምርበት የጉምሩክ ወደብ ከመነሳቱ በፊት የተላላፊነት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ይፈፀ ምበታል::

5/ Transport of the goods to the place where they are examined or samples are taken and any other handling of the goods for the purpose of examination or taking samples shall be carried out by and all expenses borne by the importer, exporter or his agent; provided, however, that the cost of analysis and examination shall be borne by the Authority.

6/ The Authority shall not be liable for payment of any compensation to the importer or exporter or his agent for samples taken in compliance with the law.

7/ Where only parts of the goods covered by the customs declaration are examined, the result of such examination shall apply to all goods indicated by that declaration.

8/ Where the importer or exporter or his agent considers that the result or partial examination is not valid as regards the remainder of the goods, he may request further examination of the goods and shall cover the expenses incurred by such examination.

9/ Where the customs declaration is not made subject to verification, the customs formalities shall be applied based on the particulars stated in the declarations.

10/ The Authority may issue directives on examination of documents and goods.

## 19. Transit Procedures

1/ Goods registered under transit procedure shall move through transit routes within the customs territory and under customs supervisions as determined by this Proclamation without paying customs duties and other charges.

2/ Transit begins at the entry customs office and ends when the goods are presented to the destination customs office.

3/ The Authority may issue directives regarding goods in transit.

## 20. Movement of Goods in Transit

1/ Transit customs formalities shall be completed with respect to any goods in transit at the customs port of departure before the commencement of transit operation.

፪/ ማናቸውም ተላላፊ ዕቃ እንቅስቃሴው በሚያበቃበት የጉምሩክ ወደብ በባለሥልጣኑ በተወሰነለት ጊዜና ሁኔታ መሠረት መድረስ ይኖርበታል::

፫/ ማንኛውም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አስፈፃሚ በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሰው ተላላፊ ዕቃ እንቅስቃሴው በሚያበቃበት የጉምሩክ ወደብ በተወሰነለት ጊዜና በተላከበት ሁኔታ መሠረት የደረሰ መሆኑን ለመድረሻው የጉምሩክ ጣቢያ ወዲያውኑ የማስታወቅ ግዴታ አለበት::

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለጉምሩክ መጋዘኖች

### ፳፩. የጉምሩክ መጋዘን ስለማቋቋም

፩/ ወደአገር የሚገቡ ወይም ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስከሚፈጸምባቸው ጊዜ ድረስ የሚቆዩበት ወይም የሚከማቹበት መጋዘን በባለሥልጣኑ ወይም በንግድ ድርጅት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በግለሰብ ሊቋቋም ይችላል::

፪/ በባለሥልጣኑ የሚቋቋም መጋዘን በመንግሥት ጋዜጣ በሚወጣ የሕዝብ ማስታወቂያ መገለጽ አለበት::

፫/ በንግድ ድርጅቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅትና በግለሰቦች የጉምሩክ መጋዘኖች ሊቋቋሙ የሚችሉት በባለሥልጣኑ በሚሰጥ ፈቃድ መሠረት ይሆናል::

### ፳፪. በባለሥልጣኑ ፈቃድ ስለሚቋቋሙ የጉምሩክ መጋዘኖች

፩/ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ የሚቋቋሙ የጉምሩክ መጋዘኖች የጠቅላላ ወይም የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘኖች ናቸው::

፪/ የጠቅላላ ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘን ማቋቋም የሚፈቀድላቸው፣

ሀ) የዕቃ ማጓጓዝ ሥራ የሚያካሂዱ የንግድ ሥራ ድርጅቶች፣

ለ) የመጋዘን አገልግሎት ሥራ ለመሥራት የተቋቋሙ የንግድ ሥራ ድርጅቶች፣እና

ሐ) ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ የሚያካሂዱ የንግድ ሥራ ድርጅቶች፣

ይሆናሉ::

፫/ የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘን ማቋቋም የሚፈቀድላቸው፣

2/ Any goods in transit shall arrive at the point of customs destination within the time specified and in the condition prescribed by the Authority.

3/ Any customs clearing agent who is responsible for the movement of goods in transit shall report forthwith to the customs destination office the arrival of the goods in accordance with the time specified and condition prescribed.

## CHAPTER TWO
## CUSTOMS WAREHOUSES

### 21. Establishment of Customs Warehouses

1/ Customs warehouses, for the storage of import or export goods until the completion of customs formalities may be established by the Authority, business organizations, government entrpriseies or individuals.

2/ The establishment of customs warehouse by the Authority shall be disclosed by a public notice to be published on government newspapers.

3/ Business organizations and individuals may establish customs warehouses in accordance with licenses issued by the Authority.

### 22. Establishment of Licensed Customs Ware House

1/ Customs warehouses that may be established upon obtaining license from the Authority shall be for general or private cargos.

2/ Persons eligible to establish customs warehouses for general cargoes shall be:

a) business organizations engaged in freight transport;

b) business organizations established to operate ware house service; and

c) business organizations established to operate customs clearing services.

3/ Persons eligible to establish customs warehouses for private cargos shall be:

ሀ) ሰውና ጭነት የሚያጓጉዙ ዓለምዓቀፍ የአየር መንገድ ድርጅቶች፣

ለ) ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለመሸጥ የተቋቋሙ ድርጅቶች፣ እና

ሐ) ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚፈቀድላቸው ሰዎች፣

ይሆናሉ።

፬/ በፈቃድ የሚቋቋሙ የጉምሩክ መጋዘኖች ደረጃ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፭/ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ማውጫና ማሳደሻ ክፍያ፣ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ ፈቃድ ሚታደስበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል።

## ፳፫. የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ማመልከቻ

የጉምሩክ መጋዘን ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው፣

፩/ የሚያከናውነውን የሥራ ዓይነት የሚገልጽ ማስረጃ፣

፪/ ሥራውን ለማከናወን የተሰጠውን ፈቃድ፣

፫/ አመልካቹ ድርጅት ከሆነ የሕግ ሰውነት የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

፬/ የመጋዘኑን የሕንፃ ፕላን፣

፭/ ለመጋዘኑና በመጋዘኑ ለሚከማቹ ዕቃዎች የመድን ዋስትና የሚገባ ለመሆኑ የተሰጠ ማረጋገጫ፣

፮/ አዲስ የሚሰራ መጋዘን ከሆነ የመጋዘኑን የግንባታ ፍቃድ፣ ፕላን ፣ አድራሻ፣ የመድን ዋስትና የሚገባ ለመሆኑ የተሰጠ ማረጋገጫ፣

፯/ መጋዘኑ ለዕቃዎች አቀማመጥና ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን ማሟላቱን የሚያሳይ ማስረጃ፣ እና

፰/ አግባብ ካለው የግብር ባለሥልጣን የተሰጠውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት።

## ፳፬. እቃዎችን ወደጉምሩክ መጋዘን ስለማስገባት

፩/ ጉምሩክ ወደብ የደረሰ ማናቸውም እቃ ከደረሰበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ቀን ድረስ አግባብነት ወዳለው የጉምሩክ መጋዘን መግባት አለበት።

a) international airlines engaged in the transportation of passengers and cargo;

b) enterprises established to sale duty free goods; and

c) other persons that may be authorized by the Authority.

4/ Grades of licensed customs warehouses shall be determined by directives to be issued by the Authority.

5/ The issuance and renewal fees, the validity period and conditions of renewal and revocation of customs warehouse licenses shall be prescribed by regulations to be issued by the Council of Ministers.

## 23. Application for Warehouse License

Any person applying for a license to establish a customs warehouse shall submit his application to the Authority together with:

1/ documents showing the specific activities of his business;

2/ the license issued to operate the business;

3/ certificate of registration where the applicant is an enterprise;

4/ the building plan of the warehouse;

5/ declaration of commitment to enter in to an insurance contract for the warehouse and the goods to be stored in the warehouse;

6/ in case of a new warehouse to be established, site and building plan, construction permit and declaration of commitment to enter in to an insurance contract,

7/ documents showing that the warehouse is equipped with apparatus necessary for proper storage and safety; and

8/ the tax identification number provided by the appropriate tax Authority.

## 24. Warehousing of Goods

1/ Goods arriving at any customs port shall be deposited in the appropriate customs warehouse within five days from the date of arrival.

፪/ ማናቸውም ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ ዝርዝር ሁኔታው እየተገለፀ በመጋዘኑ መዝገብ ላይ ይመዘገባል:: ስለአመዘጋገቡና መዝገቡ ስለሚይዘው ዝርዝር ባለሥልጣኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

፫/ ምዝገባውና የዕቃው ዝርዝር ትክክለኛ ስለመሆኑ የጉምሩክ ሹም በመዝገቡና በጭነት መግለጫው ግርጌ ላይ በመፈረም ማረጋገጥ አለበት::

## ፳፭. ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ስለሚከማቹበት ሁኔታ

፩/ ለባለሥልጣኑ የቀረቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስኪፈፀምባቸው ድረስ በጊዜያዊነት ተከማችተው ሊቀመጡ ይችላሉ::

፪/ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ያሉ ዕቃዎች ይዞታቸውና መሠረታዊ ባህሪያቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው መቆየታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ብቻ መያዝ አለባቸው::

፫/ ለባለሥልጣኑ የቀረቡ ዕቃዎች በሰዎች ሕይወትና ጤና ላይ አደጋ የሚያደርሱ ወይም አካባቢን የሚበክሉ መሆናቸው ከተረጋገጠ በዕቃዎቹ ባለቤት ወጪ እንዲወገዱ ይደረጋል::

## ፳፮. በባለሥልጣኑ መጋዘን ውስጥ ስለሚከማቹ ዕቃዎች

የሚከተሉት ዕቃዎች ባለሥልጣኑ በመግቢያና በመውጫ የጉምሩክ ወደቦች ወይም በማናቸውም ሥፍራ በሚያቋቁማቸው መጋዘኖች ውስጥ ሊከማቹ ይችላሉ፤

፩/ በጭነት መግለጫ ውስጥ ያልተመለከቱ፤

፪/ የመጡበት ምክንያት ተለይቶ መግለጫ ያልቀረበባቸው፤

፫/ በተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን የሚቀመጡ መሆናቸው ተለይቶ ያልተገለጹ፤

፬/ በጉምሩክ መጋዘን ለመቀመጥ የመጡ፤

፭/ በማናቸውም ምክንያት ከተፈቀደ መጋዘን ወደ ባለሥልጣኑ መጋዘን የተዛወሩ፤

፮/ ባለስልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሕጎች በመተላለፍ የተያዙ ዕቃዎች::

2/ Particulars of goods stored in customs warehouse shall be registered in the warehouse register book. The Authority may issue directives on the manner of registration and particulars to be entered in the registration book.

3/ A customs officer shall verify and sign the entries in registration book and the cargo manifest.

## 25. Conditions of Storage of Goods in Customs Warehouse

1/ Goods presented to the Authority may be stored temporarily until the completion of customs formalities.

2/ Goods in customs warehouse shall be subject only to such forms of handling which are necessary for ensuring their preservation without altering their appearance and essential characteristics.

3/ Where goods presented to the Authority are proved to be hazardous to life and health of humans or the environment, they shall be disposed at the expense of the owner.

## 26. Goods to be Deposited in Authority's Warehouse

The following goods may be deposited in Authority's warehouse established at customs port of entry and exit or at any other place:

1/ goods not specified in a cargo manifest;

2/ goods for which no declaration is presented as to the purpose they are imported for;

3/ goods not specified to be deposited in a licensed customs warehouse;

4/ goods imported to be deposited in the Authority's warehouse;

5/ goods transferred from licensed customs warehouse to the Authority's warehouse for whatever reason;

6/ goods seized due to any contravention of the law to be enforced by the Authority.

## ፳፯. የጉምሩክ መጋዘኖችን ስለመቆጣጠር

፩/ ማናቸውም የጉምሩክ መጋዘንና ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገቡ እቃዎች በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

፪/ በባለሥልጣኑ ከተፈቀደላቸው በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት አይችልም፡፡

፫/ ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት ስለሚፈቀድላቸው ሰዎችና ስለሚገቡበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በጉምሩክ መጋዘኖችና ወደ ጉምሩክ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ በባለሥልጣኑ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይጨምራል፤

ሀ) ወደተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን የሚገቡና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው የሚወጡ እቃዎች ባለሥልጣኑ በወሰነው የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መመዝገባቸውንና በየጊዜው ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፤

ለ) ወደተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ገብተው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ የተመለከተው ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎች ወደ ባለሥልጣኑ መጋዘን እንዲተላለፉ መደረጋቸውን፤

ሐ) ወደተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን የገቡ እቃዎች እንደ አይነታቸውና እንደየ ባህሪያቸው ተለይተው ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን፤

መ) የተፈቀደው የጉምሩክ መጋዘን በተሰጠው ፈቃድ ደረጃ መሠረት ተግባሩን እንዲያከናውን እየተደረገ መሆኑን፡፡

## ፳፰. ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ስለሚቆዩበት ጊዜ

፩/ ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ትራንዚት ወደ አገር የገባ ዕቃ ወደ ጉምሩክ መጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት፡፡

## 27. Supervision of Customs Warehouses

1/ Any customs warehouse and goods deposited in the warehouse shall be under the supervision of the Authority.

2/ Except those authorized by the Authority, no person may allowed to enter a customs warehouse.

3/ The Authority shall issue directives regarding persons to have access to customs warehouses and the conditions thereof.

4/ Save as otherwise expressly provided in this Proclamation, supervision and control, by the Authority, of customs warehouse and goods deposited in customs warehouse include any measure taken to ascertain the following:

a) the registration and periodical reporting, in accordance with the manner specified by the Authority, of goods stored in and cleared from a licensed warehouse;

b) the transfer of those goods deposited in a licensed warehouse for more than the time specified in Article 28 of this Proclamation;

c) the segregation of goods stored in a licensed customs warehouse on the basis of their type and characteristics to enable their safe storage and accessibility for supervision;

d) a licensed customs warehouse is operated in accordance with the grade of the license given.

## 28. Time Limit of Storage in Customs Warehouse

1/ Any goods imported by using sea or land transport and stored in a customs warehouse shall undergo customs formalities and be removed within 60 days from the date of storage.

፪/ ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ወደ ጉምሩክ መጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት::

፫/ ወደ ጉምሩክ ቦንድ መጋዘን የገባ ማናቸውም የንግድ ዕቃ ወደ መጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በ፬ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት::

፬/ ወደ ጉምሩክ ቦንድ መጋዘን የገባ ማናቸውም የማምረቻ መሣሪያ ወይም የወጪ ምርቶች ግብዓት ወደመጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት ከመጋዘን መውጣት አለበት::

፭/ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከተፈፀመበት በኋላ ከ፯ ቀን በላይ በመጋዘን ሊቆይ አይችልም::

፮/ ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ ባለሥልጣኑ የተተው ዕቃዎች ማከማቻ መጋዘን እንዲዛወር ተደርጎ ወዲያውኑ እንዲወገድ ይደረጋል::

፯/ ወደ ቦንድድ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ የመቆያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት የመጋዘን ፈቃዱ ከተሰረዘ ቀሪውን ጊዜ ለማጠናቀቅ ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ይደረጋል::

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት ከቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ዕቃዎችን ወደ ሌላ የጉምሩክ መጋዘን ማዘዋወር የሚያስከትለውን ማናቸውም ወጪ ፈቃዱ የተሰረዘበት የመጋዘን ባለቤት ይከፍላል::

## ፳፱. ለናሙና ወጪ ስለሚደረጉ ዕቃዎች

፩/ ወደጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን በሚከተሉት ምክንያቶች ለናሙና በሚሆን መጠን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመጠናቀቁ በፊት ወጪ ማድረግ ይቻላል፤

ሀ) ዕቃውን በተገቢው ታሪፍ ለመመደብ ዓይነቱንና የተሰራበትን ጥሬ ዕቃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) የዕቃውን ዋጋ ለመተመን የዕቃውን ዓይነት፣ ጥራትና የተመረተበትን አገር ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

2/ Any goods imported by using air transport and stored in a customs warehouse shall undergo customs formalities and be removed within 30 days from the date of storage.

3/ Any commercial goods stored in custom bonded warehouse shall undergo customs formalities and be removed within four months from the date of storage.

4/ Any production machinery or inputs to be used for export products and stored in custom bonded warehouse shall undergo customs formalities and be removed within one year from the date of storage.

5/ Any goods stored in a customs warehouse may not be kept for more than 7 days after the completion of customs formalities.

6/ Any goods stored in a customs warehouse and not removed within the time specified in sub-article (5) of this Article shall be disposed after being transferred to the Authority's abandoned goods warehouse.

7/ Where the license for a bonded customs warehouse is cancelled before the expiry of the time limit prescribed for storage of goods, the goods shall be transferred to another customs warehouse for the remaining time of storage.

8/ Any expenses for transferring goods from a bonded customs warehouse to another warehouse in accordance with sub-article (7) of this Article shall be covered by the owner of the warehouse whose license has been cancelled.

## 29. Goods Taken for Sample

1/ Samples of goods stored in a customs warehouse may be removed from the warehouse in a quantity sufficient to:

a) ascertain the type and the material content of goods to classify them under the proper tariff headings;

b) ascertain the type, quality and origin of goods for valuation purpose;

ሐ) የዕቃው ናሙና ለፍርድ ቤት ወይም ለፖሊስ ምርመራ እንዲቀርብ ሲታዘዝ፤

መ) በዋጋ ሰነዱ ላይ የተሰጠው ዋጋ ለተጠቀሰው ዕቃ መሆኑን ለማረጋገጥ፤

ሠ) ዋና ዳይሬክተሩ በሚፈቅዳቸው ሌሎች ምክንያቶች::

፪/ ለናሙና የተወሰዱ ዕቃዎች በወጡበት መጠንና ሁኔታ ሥራው እንደተጠናቀቀ ወደመጋዘን መመለስ አለባቸው:: ሆኖም በተፈጥሮአቸው ወይም ለማነጻጸሪያ የሚፈለጉ በመሆናቸው ምክንያት ሊመለሱ የማይችሉ ሲሆን፣ ለቀረጥና ታክስ እንዲሁም ለሌሎች ሂሣቦች አተማመን በመጋዘን ውስጥ እንዳሉ ይቆጠራል::

## ፴. ስለመጋዘን ኪራይ

፩/ የመጋዘን ኪራይ እንደሚከተለው ይታሰባል፤

ሀ) ወደጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው እስኪወጡ ለቆዩበት ጊዜ፤

ለ) ከጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን የተዛወሩ ዕቃዎች ከተዛወሩበት ጊዜ ጀምሮ የጉም ሩክ ፎርማሊቲ ተፈፅሞባቸው እስኪ ወጡ ለቆዩበት ጊዜ፤

ሐ) ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሕጎች በመተላለፍ የተያዙ ዕቃዎች ከተሸጡበት ጊዜ ጀምሮ ገዢው እስከሚረከብ ለቆዩ በት ጊዜ::

፪/ የጉምሩክ መጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ ይወሰናል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) መሠረት የተሸጡ ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ከ፲፭ ቀናት በላይ ሊቆዩ አይችሉም:: ከ፲፭ ቀን በላይ ከቆዩ ባለሥልጣኑ ያለምንም ልዩ ሥነ-ሥርዓት ዕቃዎቹ እንዲሸጡ ወይም በሌላ ሁኔታ እንዲወገዱ ሊያደርግ ይችላል::

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ ዕቃዎች ባለቤቱ እንዲወስዳቸው በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳደር የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ እቃዎቹ ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ ውሳኔው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በመጋዘን ለቆዩበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ አይከፈልባቸውም::

c) satisfy a court or police order requiring the presentation of sample for inspection;

d) ascertain the price indicated on the invoice is actually related to the specified item;

e) other purposes determined by the Director General.

2/ Goods removed as sample shall be returned in the same quantity and condition as soon as the purpose for which they are taken out is fulfilled; provided, however, that where it is not possible to return them due to their nature or due to their being used for analysis, it shall be presumed as they are warehoused for the purpose of duties, taxation and other charges.

## 30. Warehouse Fee

1/ Warehouse fees shall be calculated as follows:

a) for goods stored in a customs warehouse, from the date of deposit until released upon completion of customs formalities;

b) for goods transferred from bonded customs warehouse from the date of transfer until released upon completion of customs formalities;

c) for goods seized due to contravention of laws that are enforced by the Authority, from the date of sales until the buyer takes delivery of them.

2/ The rate of warehouse fees shall prescribed by a public notice to be issued by the Authority.

3/ Goods sold pursuant to sub-article 1(c) of this Article may not be kept in the warehouse for more than 15 days. If they are not removed within 15 days the Authority can sale or dispose them in any way it thinks fit.

4/ Goods that could not be released upon deposit of guarantee under sub-article (2) of Article 61 of this Proclamation shall be exempted from warehouse charge from the date of seizure until released by a final court or administrative decision.

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ እንደተደነገገው በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ ዕቃዎች ወይም የፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ወይም የባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚጠብቁ ዕቃዎች በተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን የነበሩ ከሆነ ወደ ባለሥልጣኑ መጋዘን ተዛውረው መቆየት አለባቸው::

**፴፩. ስለዕቃ አወጋገድ**

፩/ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሽያጭ ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ሊተላለፉ ወይም ሊወገዱ ይችላሉ::

፪/ የሚበላሹ ዕቃዎችና የቁም እንስሳት በባለሥልጣኑ ሲያዙ ወዲያውኑ በሐራጅ ሊሸጣቸው ይችላል:: የሽያጭ ገቢውም ጉዳዩ የመጨረሻ የፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔ እስኪያገኝ ድርስ በዲፖዚት መቀመጥ ይኖርበታል::

፫/ ከታሪክ፣ ከቅርስ፣ ከባህል፣ ከኪነጥበብ ወይም ከሳይንስ አኳያ ጠቀሜታ ያላቸውን እንዲሁም ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውሉ ዕቃዎችን ባለሥልጣኑ አግባብነት ላላቸው የመንግሥት አካላት ሊያስተላለፍ ይችላል::

፬/ ለሰው፣ ለእንስሳት ወይም ለዕፅዋት ደህንነት ጐጂ በመሆናቸው ወይም በህግ በተወሰኑ ሌሎች ምክንያቶች ሊሸጡ ወይም ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ ዕቃዎች በሌላ አኳኋን በባለሥልጣኑ እንዲወገዱ ይደረጋል::

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት እንዲወገዱ የተወሰነባቸውን ዕቃዎች ለማስ ወገድ የሚወጣውን ወጪ የዕቃው ባለቤት ይከፍላል::

፮/ በዚህ አዋጅ የተወሰኑት ሁኔታዎች መሟ ላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ከሽያጭ የሚገኝ ገቢ፣

ሀ) የቀረጥና ታክሱን ሂሳብ፣

ለ) ሽያጩን ለማከናወን የወጣውን ወጪ፣

ሐ) የመጋዘን ኪራዩን፣ እና

መ) ዕቃውን ለማጓጓዝ የወጣውን ወጪ፣

እንደቅደም ተከተሉ ለመክፈል ከዋለ በኋላ ተራፊው ለባለቤቱ የሚከፈል ይሆናል::

፯/ በተራፊው ገንዘብ ላይ ባለመብት የሆነ ሰው ሽያጩ በተፈጸመ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልጠየቀ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል::

5/ If goods that could not be released upon deposit of guarantee pursuant to Article 61 of this Proclamation or that are awaiting the final decision of court or the administrative decision of the Authority are stored in a licensed customs warehouse, they shall be transferred and stored in the Authority's warehouse.

**31. Disposal of Goods**

1/ Goods under customs control may be sold, transferred or disposed otherwise by the Authority in accordance with the provisions of this Proclamation.

2/ The Authority may immediately sell perishable goods and live animals seized. The proceeds of the sale shall be deposited until final judicial or administrative decision is given on the case.

3/ The Authority may transfer goods having historical, archeological, cultural, artistic or scientific importance as well as goods intended for humanitarian purpose to appropriate government institutions.

4/ Goods that may not be sold or used due to their being a threat to the safety of humans, animals or plants or due to other reasons prescribed by law shall be disposed otherwise by the Authority.

5/ The owner of the goods disposed under sub-article (4) of this Article shall bear the cost of the disposal.

6/ The remaining balance of the proceeds of the sale after settlement of the following payments, in the order of their precedence, shall, upon ascertaining the fulfillment of conditions provided for by the provisions of this Proclamation, be paid to the owner of the goods:

a) duties and taxes;

b) costs of the sale;

c) warehouse charges; and

d) cost of transport.

7/ Where no claim of the owner is submitted to the Authority within six months after the date of the sale, the remaining balance shall be transferred to the Government.

፰/ በዚህ አዋጅ መሠረት ዕቃዎች ስለሚሸጡበትና ስለሚወገዱበት ሥነ-ሥርዓት ባለሥልጣኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ምዕራፍ ሦስት

## የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን ሥርዓት

### ፴፪. መርህ

፩/ የጉምሩክ ቀረጥንና ሌሎች በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚጠየቁ ክፍያዎችን ለማስላት እንዲሁም የውጭ ንግድን በሚመሩ ሕጐች የተዘረዘሩትን ታሪፍ ያልሆኑ እርምጃዎች በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል የሚተመነው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል።

፪/ ወደ አገር ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ጠቅላላ ወጪ ነው።

፫/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው የተሸጠበትና ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ ወደብ ድረስ ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ወጪ ድምር ይሆናል።

፬/ በዚህ አዋጅ ስለተዘረዘሩት የዋጋ መተመኛ ዘዴዎች አፈፃፀም እንዲሁም በነዚሁ ዘዴዎች መሰረት የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መወሰን በማይቻልበት ጊዜና ስለአገለገሉ ዕቃዎች ዋጋ የመተመኛ ዘዴ ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል።

### ፴፫. የግብይት ዋጋ

፩/ ወደአገር ውስጥ ለሚገባ እቃ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጐ የሚወሰደው ለዕቃው በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የግብይት ዋጋ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች የታከሉበት ሊሆን ይችላል። ሆኖም፣

ሀ) በሕግ ወይም ሕግን መሠረት ባደረገ ልዩ ውሳኔ ከተጣሉ ገደቦች፣ ዕቃዎቹ እንደገና ሊሸጡ የሚችሉበትን መልክአ-ምድራዊ አካባቢ ከሚወስኑ ገደቦች ወይም በዕቃዎቹ ዋጋ ላይ የጐላ ተፅዕኖ ከማያሳድሩ ገደቦች በስተቀር፣ ገዥው የገዛቸውን ዕቃዎች ለሌላ የሚያስተላልፍበትን ሁኔታ ወይም አጠቃቀሙን አስመልክቶ ሌሎች ተጨማሪ ገደቦች ሊደረጉ አይችሉም፤

8/ The Authority may issue directives to prescribe the procedures applicable to the sale and disposal of goods pursuant to this Proclamation.

## CHAPTER THREE

## CALCULATION OF CUSTOMS VALUE

### 32. Principles

1/ The customs value for the purposes of applying the Customs Tariff and calculating other import charges, as well as for applying non-tariff measures prescribed by laws governing foreign trade shall be determined in accordance with the provisions of this Proclamation.

2/ The customs value for imported goods shall be the actual total costs of the goods up to the first entry point to the customs territory of Ethiopia.

3/ The customs value for export goods shall be the actual total costs of the goods up to the final exit point from the customs territory of Ethiopia.

4/ The Authority shall issue directives on the manner of application of the valuation methods stipulated in this Proclamation, and to prescribe other methods to be applicable in the case where the methods stipulated under this Proclamation could not be applied and be applicable in the case of secondhand goods.

### 33. Transaction Value

1/ The customs value of imported goods shall be the price actually paid or payable for the goods and adjusted, where necessary, as set forth in Article 39 of this Proclamation; provided, however, that:

a) there are no restrictions as to the disposal or use of the goods by the buyer, other than restrictions imposed by law or by particular decisions issued based on such law, a limit in the geographical area in which the goods may be resold or limits that may not substantially affect the value of the goods;

ለ) የዕቃው ሽያጭ ወይም ዋጋው ሊተመኑ የማይችሉ ሁኔታዎች ወይም ገደቦች የተጣለበት ሊሆን አይችልም፤

ሐ) በገዥው ከሚፈጸም የመልሶ ሽያጭ፣ ማስተላለፍ ወይም አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከሚገኝ ገቢ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሻጩ የሚከፈል ገንዘብ ሲኖር አይችልም፤

መ) ገዥውና ሻጩ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ የግብይት ዋጋው የታክስና ቀረጥ መተመኛ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው።

፪/ ገዥና ሻጭ ግንኙነት አላቸው ሊባል የሚችለው፣

ሀ) አንዱ የሌላው የንግድ ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ዳይሬክተር ከሆነ፣

ለ) በሕጋዊ መንገድ ዕውቅና ያገኘ የንግድ ሽሪኮች ከሆኑ፣

ሐ) የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ካላቸው፣

መ) አንዱ የሌላውን የንግድ ድርጅት አክሲዮኖች ከ፲በመቶ ያላነሰ በባለቤትነት ከያዘ፣

ሠ) አንዱ ሌላውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠር ከሆነ፣

ረ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን ቁጥጥር የሚደረግባቸው ከሆነ፣

ሰ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉ ከሆነ፣ ወይም

ሸ) እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ካላቸው፣

ብቻ ነው።

፫/ ሻጭና ገዥው ግንኙነት ሲኖራቸው በሽያጩ ዙሪያ ያሉት ሁኔታዎች ተመርምረው በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተፅዕኖ እንዳላሳደረ ሲታመን የግብይት ዋጋው ተቀባይነት ያገኛል።

፬/ የሻጭና ገዥው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን ለማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ባለስልጣኑ ይህንኑን ለአስመጭው መግለጽ አለበት።

b) the sale or price of the goods is not subject to some conditions or restrictions for which a value cannot be determined;

c) no part of the proceeds of any subsequent resale, disposal or use of the goods by the buyer may accrue directly or indirectly to the seller,

d) where the buyer and seller are related, the transaction value shall be considered as the basis for valuation if it is accepted by the Authority.

2/ A buyer and a seller shall be deemed to be related only if:

a) one of them is an officer or director of the other's business;

b) they are legally recognized partners in business;

c) they have employer-employee relationship;

d) one of them owns at least 10 % of the shares of the other's business;

e) one of them directly or indirectly controls the other;

f) both of them are directly or indirectly controlled by a third party;

g) both of them directly or indirectly control a third party;

h) they are related by consanguinity or affinity up to the second degree.

3/ Where an examination of the circumstances surrounding a sale between a buyer and a seller who are related shows that the relationship did not influence the price, the transaction value shall be accepted.

4/ Where there are grounds for considering that the relationship of the seller and the buyer influenced the price, the Authority shall communicate same to the importer.

፭/ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በተፈጸመ ሽያጭ የዕቃዎቹ ዋጋ፣

ሀ) በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል በተከናወነ ሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ካላቸው ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ጋር፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ በተወሰነው መሠረት ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ጋር፣ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ በተወሰነው መሠረት ከአንድ ዓይነት ወይም ከተመሳሳይ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ጋር፣

የሚቀራረብ መሆኑን አስመጪው ለማረጋገጥ ከቻለ የዕቃዎቹ የግብይት ዋጋ ተቀባይነት ይኖረዋል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተጠቀሱትን ማነፃፀሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ የንግድ ደረጃ ልዩነት፣ የብዛት ልዩነት፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ መሠረት በዋጋው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች፣ ሻጩ ከገዥው ጋር ባልተዛመደበት ሁኔታ ያወጣቸው ወጪዎች እና ሻጩ ከገዥው ጋር በተዛመደበት ሁኔታ ደግሞ እነዚህ ወጪዎች በሻጩ ያልተከፈሉ መሆናቸው ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተጠቀሱትን ማነፃፀሪያዎች በአስመጭው አነሳሽነት ብቻ በጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናል።

## ፴፬. <u>የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን</u>

፩/ ወደአገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ መሠረት ሊወሰን ካልቻለ፣ በተመሣሣይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡና በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ አንድ ዓይነት ዕቃዎች የግብይት ዋጋ መሠረት ይወሰናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን መወ ሰን ካልተቻለ፣ የንግድ ደረጃው ወይም የብዛቱ ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ በተለየ የንግድ ደረጃ ወይም ብዛት ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ መጠቀም ይቻላል።

5/ The transaction value of goods in case of a sale between related persons shall be acceptable where the importer can prove that such value closely approximates to:

a) the transaction value in sales, between buyers and sellers who are not related, of identical or similar goods for export to Ethiopia during the same period;

b) the customs value of identical or similar goods as determined under Article 37 of this Proclamation; or

c) the customs value of identical or similar goods as determined under Article 38 of this Proclamation.

6/ In applying the tests under sub-article (5) of this Article, due account shall be taken of demonstrated differences in commercial levels, quantity levels, the appropriate amounts determined pursuant to Article 39 of this Proclamation and costs incurred by the seller in sales in which he and the buyer are not related and where such costs are not incurred by the seller in sales in which he and the buyer are related.

7/ The tests set forth under sub-article (5) of this Article shall only be used at the initiative of the importer.

## 34. **Valuation of Identical Goods**

1/ Where the customs value of imported goods cannot be determined on the basis of Article 33 of this Proclamation, it shall be determined by taking the transaction value of identical goods sold for export to Ethiopia at the same commercial level and in substantially the same quantity at or about the same time as the goods being valued.

2/ Where it is impossible to determine the customs value in accordance with sub-article (1) of this Article, the transaction value of identical goods sold at a different commercial level or in different quantities by making adjustments to take account of differences attributable to the commercial level or to the quantity.

፫/ የግብይት ዋጋው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱(፩) የተጠቀሱትን ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ የገቡትንና አንድ ዓይነት የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከሰቱ የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማውረድ፣ የአያያዝና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት።

## ፴፭. የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን

፩/ ወደአገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ እና ፴፬ መሠረት ሊወሰን ካልቻለ፣ በተመሣሣይ የንግድ ደረጃና በተቀራራቢ ብዛት በተሸጡና በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በተላኩ ተመሳሳይ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ መሠረት ይወሰናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን መወሰን ካልተቻለ፣ የንግድ ደረጃው ወይም የብዛቱ ልዩነት ለሚያስከትለው የዋጋ ልዩነት ማስተካከያ በማድረግ በተለየ የንግድ ደረጃ ወይም ብዛት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎችን የግብይት ዋጋ መጠቀም ይቻላል።

፫/ የግብይት ዋጋው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱(፩) የተጠቀሱትን ወጪዎች የሚያካትት ከሆነ ከርቀትና ከማጓጓዣ ዓይነት ልዩነት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ የገቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን ዕቃዎች እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከሰቱ የማጓጓዣ፣ የመጫን፣ የማውረድ፣ የአያያዝና የኢንሹራንስ ወጪ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት።

## ፴፮. ወደ ኋላ የማስላት ዘዴ

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፴፫ እስከ ፴፭ በተደነገገው መሠረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ፣ በተመሳሳይ ወይም በተቀራራቢ ወቅት ወደ አገር ውስጥ የገቡና በገቡበት ሁኔታ ግንኙነት በሌላቸው ገዥና ሻጭ መካከል በከፍተኛ ብዛት በተሸጡበት ነጠላ ዋጋ ላይ በመመሠረትና የሚከተሉትን ከዋጋው ላይ በመቀነስ ይወሰናል፤

ሀ) ወደ አገር ውስጥ ገብተው የሚሸጡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎችን በሚመለከት አብዛኛውን ጊዜ የሚታየውን የኮሚሽን፣ የወጪዎችና የትርፍ መጠን፤

3/ Where the transaction value includes costs referred to in Article 39(1) of this Proclamation, the adjustment shall take into account the differences in transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the imported goods and that of the identical goods to the port of entry of Ethiopia which may arise from differences in distance and means of transport.

## 35. Valuation of Similar Goods

1/ Where the customs value of imported goods cannot be determined on the basis of Articles 33 and 34 of this Proclamation, it shall be determined by taking the transaction value of similar goods sold for export to Ethiopia at the same commercial level and in substantially the same quantity at or about the same time as the goods being valued.

2/ Where it is impossible to determine the customs value in accordance with sub-article (1) of this Article, the transaction value of similar goods sold at a different commercial level or in different quantities by making adjustments to take account of differences attributable to the commercial level or to the quantity.

3/ Where the transaction value includes costs referred to in Article 39(1) of this Proclamation, the adjustment shall take into account the differences in transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the imported goods and that of the identical goods to the port of entry into the customs territory of Ethiopia which may arise from differences in distance and means of transport.

## 36. Deductive Value Method

1/ Where the customs value of imported goods cannot be determined as set forth in Articles 33 to 35 of this Proclamation, it shall be determined by using the unit price of identical or similar goods imported at or about the same time and which are sold in Ethiopia in their original state in the greatest aggregate quantity to persons who are not related to the seller; provided, however, that the price shall be reduced by:

a) an amount of commission, expenses and profit equal to that usually reflected in sales within Ethiopia of identical or similar imported goods;

ለ) ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚከፈሉትን የማጓጓዣ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች፤

ሐ) ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች የሚከፈሉ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች::

፪/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በተቀራረበ ጊዜ በአገር ውስጥ ካልተሸጡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወሰነው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ከዘጠና ቀን ባልበለጠ የጊዜ ልዩነት ውስጥ ወደ አገር ውስጥ ገብተው በተሸጡ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች ነጠላ ዋጋ ላይ ይመሠረታል::

፫/ ወደ አገር ውስጥ የገቡት አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በገቡበት ሁኔታ ካልተሸጡ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወሰነው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ዕቃዎቹ የተከናወነባቸው ቀጣይ የምርት ሂደት ያስከተለው ተጨማሪ እሴት ተቀንሶ ይተመናል::

## ፴፯. በወጪ ስሌት ላይ የተመሠረተ ዋጋ

፩/ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፴፫ እስከ ፴፮ በተደነገገው መሠረት ሊወሰን በማይቻልበት ጊዜ፣

ሀ) የዕቃዎቹን የማምረቻ ወይም የማዘጋጃ ወጪዎች፣

ለ) ዕቃዎቹ ወደ ኢትዮጵያ በተላኩበት አገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች በአምራቾች ሲሸጡ አብዛኛውን ጊዜ የሚያስከትሉን የመሸጫ ወጪና የሚያስገኙትን የትርፍ መጠን፣ እና

ሐ) ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ በር ለማድረስ የሚያስወጣውን የማጓጓዣ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪን፣

በሚያካትት ስሌት ላይ ተመሥርቶ ይወሰናል::

b) the usual charges for the transport, insurance and other related costs to be incurred within Ethiopia for identical or similar imported goods;

c) import duties, taxes and other charges payable with respect to identical or similar imported goods.

2/ In case where there are no identical or similar imported goods which are sold at or about the same time, the customs value to be determined under sub-article (1) of this Article shall be based on the unit price of identical or similar imported goods which are sold in Ethiopia within a period having a time difference not longer than 90 days.

3/ In case where the identical or similar imported goods are not sold in their original state, the customs value to be determined under sub-article (1) of this Article shall be calculated by deducting the additional value resulting from the subsequent processing of the goods.

## 37. Computed Value Method

1/ Where the customs value of imported goods cannot be determined as set forth in Articles 33 to 36 of this Proclamation, it shall be based on a computed value, consisting of the sum of:

a) the cost of manufacturing or processing of the goods;

b) an amount representing the selling expenses and profit equal to that usually reflected in the sale of identical or similar goods by producers in the country of export; and

c) the transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the goods to the port of entry into the customs territory of Ethiopia.

፪/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን ለመወሰን በአምራቹ ፈቃድ የሚገኘውን መረጃ ለማረጋገጥ፣ የአምራቹ አገር መንግሥት ጉዳዩን በቅድሚያ እንዲያውቀው በማድረግ የማይቃወመው መሆኑ መረጋገጥ አለበት::

## ፴፰. ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ዋጋ መወሰን

፩/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፴፫ እስከ ፴፯ በተደነገገው መሠረት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመወሰን ካልተቻለ፣ በአገር ውስጥ ያለውን ወቅታዊ መረጃ በመጠቀምና ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አጠቃላይ መርህ ጋር የተጣጣመ ሚዛናዊ ዘዴን በመጠቀም ይወሰናል::

፪/ በአስመጭው ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተተመነው ዋጋና የአተማመን ዘዴው በጽሑፍ ሊገለጽለት ይችላል::

## ፴፱. በግብይት ዋጋ ላይ የሚጨመሩ ክፍያዎች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ መሠረት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን፣ ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ የሚከተሉት መደመር አለባቸው፤

ሀ) በገዥው የሚሸፈኑ ወጪዎች ሆነው ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱ፣

(፩) ከግዥ ኮሚሽን በስተቀር ማናቸውም ዓይነት የኮሚሽንና የድለላ ክፍያ፤

(፪) ከዕቃዎቹ ተነጥለው ሊታዩ የማይችሉ የዕቃ መያዣዎች ወጪ፤

(፫) ዕቃዎቹን ለማሸግ የወጣ የጉልበትም ሆነ የማቴሪያል ወጪ፤

(፬) ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት፣የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ፤

ለ) ዕቃዎቹን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑና ከኢትዮጵያ ውጪ ለተከናወኑ የኢንጂነሪንግ፣ የዲዛይንና የፕላን ሥራዎች የተደረጉ ወጪዎች በገዥው የሚሸፈኑ እስከሆኑና ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱ ከሆነ፤

2/ In verifying, with the consent of the manufacturer, data necessary for determining customs value pursuant to the provisions of this Article, the government of the manufacturer's country shall be informed in advance and shall be ascertained that it does not object such verification.

## 38. Fallback Method

1/ Where the customs value of imported goods cannot be determined under the provisions of Articles 33 to 37 of this Proclamation, it shall be determined based on the data available in Ethiopia and using equitable methods consistent with the general principles embodied in the provisions of this Proclamation.

2/ The importer shall, when it so requests, be informed, in writing, of the customs value determined under the provisions of sub-article (1) of this Article and the method used thereto.

## 39. Costs to be included in Customs Value

1/ In determining the customs value of imported goods in accordance with Article 33 of this Proclamation, the following costs shall be added to the price actually paid or payable for the imported goods:

a) expenses incurred by the buyer, and not included in the price actually paid or payable for the goods, in respect of:

(1) commission and brokerage charges except buying commission;

(2) the cost of containers which are treated as integral part, for customs purposes, of the goods;

(3) the cost of packing, whether for labor or materials;

(4) the transport, loading, unloading, handling and insurance costs associated with the transport of the goods to the port of entry into the customs territory of Ethiopia;

b) costs of engineering, design and plan works necessary for the production of the goods and undertaken elsewhere other than in Ethiopia, to the extent that such costs are incurred by the buyer and not included in the price actually paid or payable;

ሐ) ለዕቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ውስጥ ያልተካተቱና በገዢው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲከፈሉ በሽያጭ ውሉ የተደነገጉ የአዕምሯዊ ንብረት ሮያሊቲና ፈቃድ ክፍያዎች፤

መ) ዕቃዎቹን መልሶ በመሸጥ፣ ለሌላ በማስተላለፍ ወይም በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለሻጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚከፈሉ ክፍያዎች።

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በግብይት ዋጋ ላይ የሚደመሩ ማናቸውም ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭና ሊለኩ በሚችሉ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው።

፫/ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ለመወሰን በዕቃው የተከፈለ ወይም የሚከፈል ዋጋ ላይ የሚደመር ክፍያ በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት ብቻ ይሆናል። ክፍያውም በሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም በሕግ በተፈቀደ ሌላ የክፍያ ሥርዓት አማካይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊፈጽም ይችላል።

፵. <u>በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎች</u>

፩/ ለዕቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል የግብይት ዋጋ ውስጥ ተለይተው እስከተቀመጡ ድረስ የሚከተሉት ክፍያዎች በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ አይካተቱም፤

ሀ) የፋብሪካ መሣሪያዎች፣ ማሺነሪዎች ወይም በመሣሪያዎች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ለተከናወነ ወይም ለሚከናወን የግንባታ፣ የማሻሻያ፣ የተከላ ወይም የጥገና ሥራ ወይም ለቴክኒክ ድጋፍ የሚከፈል ክፍያ፤

ለ) ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል ከገቡ በኋላ የሚከፈል የትራንስፖርት ክፍያ፤

ሐ) ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ዕቃዎች ግዥ ጋር በተያያዘ ገዢው ለገባው የብድር ወይም የፋይናንስ ስምምነት የሚከፈል የወለድ ክፍያ፤

መ) ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን መልሶ ለማምረት መብት የሚከፈል ክፍያ፤

ሠ) የግዢ ኮሚሽን፤

ረ) ወደ አገር ውስጥ ከገቡት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈለ የቀረጥና ሌሎች ክፍያዎች።

c) royalties for intellectual property rights and license fees related to the goods that the buyer is required to pay, either directly or indirectly, as a condition of sale of the goods, to the extent that such royalties and license fees are not included in the price actually paid or payable;

d) the value of any part of the proceeds of any subsequent resale, disposal or use of the goods that accrues directly or indirectly to the seller.

2/ Additions to the price actually paid or payable shall be made under this Article only on the basis of objective and quantifiable data.

3/ No additions shall be made to the price actually paid or payable in determining the customs value, except as provided in this Article. Such payments may be made directly or indirectly by a letter of credit or any other legally acceptable means of payment.

40. <u>Charges not to be included in Customs Value</u>

1/ Provided that they are shown separately from the price actually paid or payable, the following shall not be included in the customs value:

a) charges for construction, upgrading, erection, maintenance or technical assistance, which have been undertaken or are to be undertaken after the importation of industrial plants, machinery or equipment;

b) charges for the transport of goods after their introduction into the customs territory of Ethiopia;

c) charges for interest under a financial arrangement entered into by the buyer and relating to the purchase of imported goods;

d) charges for the right to reproduce imported goods;

e) buying commissions;

f) import duties or other charges paid in Ethiopia related to importation of the goods.

፪/ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን የሚከተሉት ክፍያዎች ለእቃው በተከፈለ ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ አይደመሩም፤

ሀ) ወደ አገር ውስጥ የገቡትን ዕቃዎች በአገር ውስጥ እንደገና ለማምረት መብት የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

ለ) ዕቃዎቹን ለመላክ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ ካልሆነ በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ለማከፋፈል ወይም እንደገና ለመሸጥ በገዢው የሚከፈሉ ክፍያዎች::

## ፵፩. ከግብይት ዋጋ ላይ ስለሚቀነሱ ሂሣቦች

ወደአገር ውስጥ ከሚገቡ ዕቃዎች የግብይት ዋጋ ላይ የሚከተሉት ሂሳቦች ተቀናሽ ይደረጋሉ፤

፩/ ዕቃዎቹ በጉዞ ላይ ሳሉ የደረሰ ጉዳት፤

፪/ ዕቃዎቹ በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ሳሉ የደረሰ ጉዳት፤

፫/ አደገኛ በመሆኑ ምክንያት እንዲቃጠል ወይም በሌላ አኳኋን እንዲወገድ የተደረገ ዕቃ ዋጋ::

## ፵፪. ተጨማሪ መግለጫና መረጃ ስለማቅረብ

፩/ ባለሥልጣኑ በቀረበው የዲክላራሲዮን ዝርዝሮች ወይም ደጋፊ ሰነዶች ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት የሚያደረግ ምክንያት ሲኖረው የተገለጸው የግብይት ዋጋ ለዕቃው የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ትክለኛ ዋጋ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ መግለጫ ወይም መረጃ እንዲያቀርብ አስመጪውን ወይም ወኪሉን ሊጠይቀው ይችላል::

፪/ ባለሥልጣኑ ተጨማሪ መግለጫ ወይም ሰነድ ካስመጪው ወይም ከወኪሉ ከተቀበለ በኋላ ስለግብይት ዋጋው ትክክለኛነት ያለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ካልቻለ ወይም አስመጪው ምላሽ ካልሰጠ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋን መወሰን እንዳልተቻለ ይቆጠራል:: የቀረበው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋም ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት በጽሑፍ ለአስመጪው ወይም ለወኪሉ ይገልጽለታል::

## ፵፫. የዋጋ አተማመን ዘዴዎች ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው ሌሎች ሁኔታዎች

ከላይ የተመለከቱት የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በሚከተሉትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

2/ In determining the customs value, the following shall not be added to the price actually paid or payable:

a) charges for the right to reproduce the imported goods,

b) payments made by the buyer for the right to distribute or resell the imported goods if such payment is not a condition of the sale for export to Ethiopia.

## 41. Deduction from Transaction Value

The following shall be deducted from the transaction value of imported goods:

1/ costs for damages in routes;

2/ costs for damages in customs warehouse;

3/ the value of dangerous goods destroyed or disposed otherwise.

## 42. Production of Additional Information and Evidence

1/ Where the Authority has reason to doubt the accuracy of particulars of a declaration or of documents produced in support of a declaration, it may require the importer or his agent to produce further information or evidence that shows the declared transaction value represents the amount actually paid or payable for the imported goods.

2/ Where the Authority, after receiving further information still has reasonable doubts about the accuracy of the declared value or in the absence of a response, it may be deemed that the customs value of the imported goods cannot be determined under the provisions of Article 33 of this Proclamation; and the reason for such decision shall be provided in writing to the importer or his agent.

## 43. Other Conditions in Which Valuation Methods be Applicable

The valuation methods stipulated in the preceding provisions of this Proclamation shall also be applicable to:

፩/ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው ከተለቀቁ በኋላ በድጋሚ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምበት ሁኔታ ሲያጋጥም፣

፪/ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው ከተለቀቁ በኋላ ኦዲት የሚካሄድባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት፤

፫/ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን እና በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን ዋጋ አተማመን በሚመለከት::

## ፵፬. የገንዘብ ምንዛሪ

ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ከአገር የሚወጡ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚሰላው ስለእቃዎቹ የቀረበው ዲክላራሲዮን በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባገኘበት እለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጸውን የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመጠቀም ይሆናል::

## ምዕራፍ አራት
## የዕቃዎች የታሪፍ አመዳደብ

## ፵፭. መርህ

፩/ ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሰረት ይሆናል::

፪/ ጭነቱ በተለያየ የታሪፍ አመዳደብ ላይ የሚመደቡ ዕቃዎችን የያዘ በመሆኑ ምክንያት ዕቃዎችን የመመደብ ወይም ዲክላራሲዮን ማዘጋጀት ሥራው አድካሚ ሆኖ ሲገኝና የጉምሩክ የታሪፍ ምጣኔ ልክ የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ በዲክላራሲዮን አቅራቢው ጥያቄ መሠረት ባለሥልጣኑ አጠቃላይ ጭነቱን ከፍተኛ ታሪፍ በሚመደብበት የታሪፍ መደብ ላይ በመመደብ የታሪፍ ምጣኔ ልኩ እንዲወሰን ሊፈቅድ ይችላል::

፫/ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥ ከማይከፈልባቸው በስተቀር ለግልና ለቤተሠብ አባላት ጠቀሜታ እንዲውሉ በማናቸውም ተጓዥ ግለሰብ ከውጭ አገር የሚመጡ ዕቃዎች በተለየ ሁኔታ የተዋሃደ የታሪፍ ምጣኔ መሠረት ቀረጥ ይከፈልባቸዋል:: ዝርዝሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፬/ ስለዕቃዎች የታሪፍ አመዳደብ ወሳኝ ማስረጃ ሆኖ የሚቆጠረው የዓለም የጉምሩክ ድርጅት ስለሽቀጦች አመዳደብ የሚያወጣው ሰነድ ነው::

1/ goods that have been released from customs control without paying duties and taxes undergo another customs procedure to pay duties and taxes;

2/ goods which may undergo post customs clearance audit;

3/ the valuation of non-commercial imported goods and temporarily imported goods.

## 44. Exchange Rate

The customs value of imported or exported goods shall be calculated on the basis of the official exchange rate declared by the National Bank of Ethiopia on the day of accepting the customs declaration by the Authority.

## CHAPTER FOUR
## CUSTOMS TARIFF

## 45. Principles

1/ Duties on goods imported into the customs territory of Ethiopia shall be paid at the rates specified by the Customs Tariff Regulations.

2/ Where classification of goods and drawing up of customs declaration becomes difficult due to a consignment containing goods falling under different tariff classifications, the Authorities may, at the request of the person presenting the declaration, allow that the customs duty for the entire consignment be charged on the basis of the tariff classification of the goods which are subject to the highest rate of customs duty.

3/ Integrated tariff rate shall be applicable to goods brought in or received from abroad by a traveler individual natural persons, intended to be used in their households, unless such goods are relieved from customs duty under relevant laws. The details shall be determend by the directive issued by the authority.

4/ Documents prepared by the World Customs Organization in relation to classification of goods shall be taken as conclusive evidence.

## ፵፮. የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ አስገዳጅ መረጃዎችን ስለመስጠት

፩/ ከአስመጪው ወይም ከወኪሉ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ ባለሥልጣኑ አስገዳጅ መረጃዎችን ይሰጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀውን መረጃ የሚጠቀም ሰው ያቀረበው የዕቃ ዝርዝር መግለጫ አስቀድሞ ከሠጠው መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል አለበት።

፫/ የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብን በተመለከተ የተሰጠ አስገዳጅ መረጃ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቀባይነቱን ያጣል፤

ሀ) አስገዳጅ መረጃው በአመልካቹ በቀረበ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ መረጃ ላይ የተመሠረተ ከሆነ፤

ለ) በደንቦች ወይም መመሪያዎች መለወጥ ምክንያት አስገዳጅ መረጃው በሥራ ላይ ካሉት ደንቦች ወይም መመሪያዎች ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

ሐ) አስገዳጅ መረጃው የተሰጠው ተገቢው ሥልጣን በሌለው ሰው ከሆነ፤

መ) አስገዳጅ መረጃው ከተሻረ ወይም ከተሰረዘና መሻሩ ወይም መሠረዙ ለመረጃው ባለቤት የተገለፀ ከሆነ።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) የተገለፀው ሁኔታ ሲከሰት ደንቡ ወይም መመሪያው በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ መረጃው የማያገለግል ይሆናል።

## ምዕራፍ አምስት
## የዕቃዎች የሥሪት አገር

## ፵፯. የዕቃዎች ሥሪት አገር አወሳሰን

፩/ አንድን ምርት በማምረት ሂደት ሁለትና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው አገሮች ተሳታፊ በሆኑበት ሁኔታ የምርቱ የሥሪት አገር የሚባለው የመጨረሻው መሠረታዊ የምርት ሥራ የተካሄደበት ወይም የኢኮኖሚያዊ የዋጋ ለውጥ ሂደት የተከናወነበት አገር ይሆናል፤ ሆኖም የምርት ሂደቱ በዚሁ አገር ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ ፋብሪካ ውስጥ የተከናወነና ሂደቱም በወሳኝ መልኩ በምርቱ ላይ ለውጥ ያስከተለ ወይም አዲስ ምርት ያስገኘ መሆን አለበት።

## 46. Binding Information Regarding Tariff Classification

1/ At the request of an importer or his agent, the Authority shall issue binding information in respect of the classification of goods.

2/ The person using information referred to under sub-article (1) of this Article shall be able to prove that the goods declared correspond in every respect to those described in the information previously provided by him to get the binding information.

3/ Binding information regarding tariff classification shall become invalid:

a) where it is based on inaccurate or incomplete information supplied by the applicant;

b) where regulations or directives have been changed, and the information no longer conforms to the applicable regulations or directives;

c) where the binding information was not provided by the competent authority;

d) where the information has been annulled or revoked, and the holder of the information has been notified of such annulment or revocation.

4/ When the situations referred to in sub-article 3(b) of this Article occur, the information shall become invalid as of the date such regulations or directives become effective.

## CHAPTER FIVE
## ORIGIN OF GOODS

## 47. Determination of Country of Origin

1/ Where two or more countries are involved in the production of a product, the origin of the product shall be the country in which the last substantial manufacturing or transformation process of economic value took place; provided, however, that such process was carried out in a plant equipped for this purpose and led to a substantial transformation of the product or the creation of a new product altogether.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ሲባል የዕቃውን የሥሪት አገር ለመወሰን የሚያስፈልጉት መስፈርቶች፣

ሀ) የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ፣

ለ) የተጨማሪ እሴት መቶኛ መመዘኛ፣

ሐ) የማምረቻ ወይም የዝግጅት ሥራ ሂደት መመዘኛ፣

ናቸው::

፫/ በምርት ግብአቶች ላይ የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎችና የምርት ሂደቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ እንደተጠቀሰው የተሟላ ሥራ ሂደት ሆነው ይቆጠራሉ::

፬/ ማናቸውም የሥራ ወይም የምርት ክንውን የዚህን አዋጅ የስሪት ሀገር አወሳሰን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ዓላማ በማድረግ የተከናወነ መሆኑ ከተረጋገጠ የምርት ክንውኑ ከሥሪት አገር ደንብ አንፃር ትክክለኛ ሆኖ አይቆጠርም::

፭/ የዕቃዎች ስሪት አገር አወሳሰንን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል::

## ፵፰. የዕቃዎች የሥሪት አገርን ለመወሰን ግምት ውስጥ የማይገቡ ሁኔታዎች

የሚከተሉት የአሠራር ሂደቶች የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያስከትሉ ሆነም አልሆነ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን የስሪት አገር ለመወሰን ከግምት ውስጥ አይገቡም፤

፩/ በምርት ማጓጓዝ ወይም ክምችት ወቅት ምርቱን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የሚከናወኑ ተግባራት፤

፪/ ዕቃዎችን የማጓጓዝ ሂደት ለማቀላጠፍ ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፤

፫/ ዕቃዎችን ለማሸግ ወይም ለሽያጭ ለማዘጋጀት ሲባል የሚከናወኑ ተግባራት፤

፬/ ዕቃዎችን በአየር የማናፈስ፣ የማስጣት፣ የማድረቅ፣ የማቀዝቀዝ፣ የተበላሹ ክፍሎችን የመቀየር፣ ማለስለሻ የመቀባት ወይም ዝገት የማስወገድ፣ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች በዕቃው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀለም የመቀባት፣ የማጠብ፣ የማጽዳት፣ የማበጠር፣ የመፈተግ፣ የመለየት፣ የመመዘን፣ የመሞከር፣ የመለካት፣ የማሸግ፣ እሽጎችን የመፍታት፣ መልሶ የማሸግ፣ የመከፋፈል፣ ምልክት የማድረግ፣ በውሃ ወይም በሌላ ፈሣሽ ነገር አያያዝ ማድረግ፣ በጨው የመንከር፣ የመላጥ፣ የመከካት፣ የመውቃት እና የእንስሳት ዕርድ የመሳሰሉ ቀላል ሂደቶች ክንውን፤

2/ For the purposes of sub-article (1) of this Article, the criteria for determining origin, shall be the following:

a) change of tariff classification;

b) the ad valorem percentage criterion; and

c) the criterion of manufacturing or processing operation.

3/ Working or processing methods because of which the products obtained receive tariff classification other than that covering the various non-originating materials used shall be regarded as complete process referred to sub-article (1) of this Article.

4/ Any processing or working the sole object of which is to circumvent the rules of origin of this Proclamation shall not be deemed authentic.

5/ The Authority may issue detail directives on the applications of rules of origin.

## 48. Conditions not Considered When Determining Rules of Origin

The following operations shall not be taken into consideration when determining the origin of imported goods, whether or not accompanied by a change in the tariff classification:

1/ operations carried out to insure that the goods are preserved in good condition during transport or storage;

2/ operations carried out to facilitate transportation of goods;

3/ operations carried out to package or prepare goods for sale;

4/ simple operations on goods such as ventilation, spreading out, drying, cooling, removal of damaged parts, greasing or rust removal, adding a coat of paint to protect against natural elements, washing, cleaning, sifting or screening, sorting or classifying, scaling, testing or calibration, packaging or breaking up of assembled packages or repackaging, dividing the bulks, affixing marks, labels or other distinguishing signs on the packages of goods, dilution by water or any other aqueous solution, ionization, salting, peeling, crushing, removal of seeds from fruits and slaughtering of animals;

፭/ የተሟላ የምርት ውጤት ለማስገኘት የሚከናወን ቀላል የመገጣጠም ሥራ፤

፮/ ከላይ የተዘረዘሩትን የሥራ ሂደቶች በማጣመር የሚከናወን ማንኛውም የሥራ ሂደት፡፡

**፵፱. <u>የሥሪት አገርን ለመወሰን የሚረዱ ሰነዶችን ስለማቅረብ</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች ህጎች የተደነገጉትን ለማስፈፀም ሲባል የዕቃዎችን የሥሪት አገር የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት በቀረበለት ሠነድ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው ባለስልጣኑ የዕቃውን የሥሪት አገር በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፶. <u>የታሪፍ ቅናሽ ከሚሰጣቸው አገሮች የሚመጡ ዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን</u>**

በዓለም አቀፍ፣ በአካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነት መሰረት የታሪፍ ቅናሽ የሚሰጣቸው ሀገሮች የስሪት ሀገር ደንብ በስምምነቶቹ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>ስለቀረጥና ታክስ እና የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

**፶፩. <u>በገቢ ዕቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ</u>**

በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ ወይም በመንግስት በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ይከፈላል፡፡

**፶፪. <u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ስለሚወሰንበት ጊዜ</u>**

በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ የሚወሰንበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ተቀባይነት በሚያገኝበት ቀን፤

ለ) ተጓዦች ይዘዋቸው ለሚመጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በሚፈፀምበት ቀን፤

ሐ) በአደራ ዕቃ ክምችት ለሚቀመጡ ዕቃ ዎች ገዢው በሚረከብበት ቀን፤

5/ simple assembly of parts to constitute a complete product;

6/ any combination of the above.

**49. <u>Production of Documents</u>**

1/ The Authority may, for the purpose of applying the provisions of this Proclamation or other laws, order the production of documents that show the origin of goods.

2/ Where the Authority has doubts as to the authenticity of documents the produced pursuant to sub-article (1) of this Article, it may require any additional proof in respect of the origin of goods.

**50. <u>Preferential Rules of Origin</u>**

The rules on preferential origin of goods shall be determined in accordance with rules of origin contained in international, regional or bilateral agreements providing for reduction or relief from import duties.

## <u>CHAPTER SIX</u>

## <u>PAYMENTS OF CUSTOMS DUTIES AND TAXES, AND SERVICE CHARGES</u>

**51. <u>Obligation to Pay Import Duties and Taxes</u>**

Unless otherwise provided by this Proclamation or other laws or decided by government, import duties and taxes shall be payable for any imported goods.

**52. <u>Applicable Dates for Determination of Duties and Taxes</u>**

The applicable dates for determining customs duties and taxes shall be as follows:

a) for goods imported, the date when the customs declaration is accepted;

b) for goods carried by passengers, the date of customs clearance;

c) for goods placed in consignment stock, the date of delivery to the buyer;

መ) ከአደራ ዕቃ የማከማቻ ስፍራ ወደጉምሩክ መጋዘን ለሚሸጋገሩ ዕቃዎች ከአደራ ዕቃ ማከማቻው በወጡበት ቀን፤

ሠ) በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ለገባ ዕቃ፣ ዕቃው በአገር ውስጥ እንዲቀር ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበው ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ባገኘበት ቀን፤

ረ) ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ዓላማ በጉምሩክ ክልል ውስጥ ትራንዚት ለተደረጉ ዕቃዎች የዕቃዎቹ ዲክላራሲዮን በቀረበበት ቀን፤ ዲክላራሲዮን ያልቀረበ ከሆነ ደግሞ የገቢ ዕቃ ቀረጥ ክፍያዎች ውሣኔ በተሰጠበት ቀን::

፶፫. <u>የአገልግሎት ክፍያ</u>

ባለሥልጣኑ ከገቢና ወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ በደንብ ይወሰናል::

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

## <u>ዕቃዎችን በጊዜያዊነት ስለማስገባት፣ ስለማስወጣትና ተመልሰው ስለሚወጡ የገቢ ዕቃዎች</u>

፶፬. <u>በጊዜያዊነት ዕቃዎችን ስለማስገባት</u>

፩/ ንግድን ከማስተዋወቅ፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ከቱሪዝምና ከባህል ልውውጥ፣ ከግንባታ ሥራ ወይም ከምክር አገልግሎት ጋር የተያያዙ ዕቃዎች የመጡበት ምክንያት እንደተጠናቀቀ በመጡበት አኳኋን እንዲወጡ ሆኖ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ሊገቡ ይችላሉ::ሆኖም መለዋወጫዎችና አላቂ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ሊገቡ አይችሉም::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ውጪ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡባቸው ሌሎች ሁኔታዎች ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፫/ ዕቃዎችን በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው ከቀረጥና ታክስ ነፃ ባስገባው ዕቃ ላይ በሚፈለገው ቀረጥና ታክስ መጠን ዋስትና ማቅረብ አለበት::

፬/ በጊዜያዊነት ወደአገር ውስጥ የገባን ዕቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ከተደረገበት ዓላማ ወይም ሥራው ከሚከናወንበት ሥፍራ ውጪ በጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው::

d) for goods transferred from consignment stock to customs warehouse, the date when the goods are taken out from the consignment stock;

e) for goods temporarily imported, the date when the customs declaration presented for the second time is accepted if they are declared for home consumption;

f) for goods transited within customs territory for the purpose of import, the date when declaration for such goods is lodged, or where there is no declaration, the date when decision on payment of import duties is made.

53. <u>**Service Charges**</u>

The service charges to be collected by the Authority in connection with the application of customs formalities to import and export goods shall be determined by regulations.

## <u>CHAPTER SEVEN</u>

## <u>TEMPORARY IMPORTATION, EXPORTATION AND RE-EXPORTATION OF IMPORTED GOODS</u>

54. <u>**Temporary Importation**</u>

1/ Goods necessary for trade promotion, technology transfer, tourism and cultural exchange, construction works and consultancy services may temporarily be imported without payment of duties and taxes subject to their re-export at the completion of such tasks. However spare parts and consumable goods shall not be temporary imported.

2/ The Ministry of Finance and economic development may, by directives, determine conditions other than those stated under sub-article (1) of this Article under which temporary importation of goods without payment of duties and taxes may be permitted.

3/ Any person who imports goods temporarily, without payment of duties and taxes, shall provide security equivalent to the duties and taxes payable with respect to such goods.

4/ It is prohibited to use goods imported on temporary basis other than the purposes for which they are imported or to use them out of the locality where the activities are carried out.

፭/ ከግንባታ ሥራዎች ወይም ከምክር አገልግሎት ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎች አገር ውስጥ እንዲቆዩ በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን ለማስገባት መብት ላላቸው ሰዎች እንዲተላለፉ ባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፮/ በጊዜያዊነት ገብተው ተመልሰው በሚወጡ ያገለገሉ ዕቃዎች እርጅና ዋጋ ላይ ዕቃዎች ሲወጡ ባለው ታሪፍ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

፯/ በጊዜያዊነት ያስገባውን ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ለሌላ የሚያስተላልፍ ሰው ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እስከተላለፈበት ጊዜ ድረስ በሚታሰበው የእርጅና ቅናሽ ላይ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፰/ ከፕሮጀክት ስራዎች ጋር በተያያዘ በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ክፍያ ነፃ ሆነው የገቡ ዕቃዎች አገልግሎት ላይ የዋሉበት ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የመጨረሻ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ወይም የፕሮጀክቱ ጊዜ ሲራዘም የፕሮጀክቱ ባለቤት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

፱/ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች በአገር ውስጥ የሚቀሩበት ሁኔታና የቀረጥና ታክስ ክፍያው አፈፃፀም የንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፶፭. <u>የጊዜ ገደብ</u>

፩/ ከቱሪዝምና ከባህል ልውውጥ ወይም ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር የተያያዙ እቃዎች ወደ አገር ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው፡፡

፪/ ንግድ ለማስተዋወቅ የገቡ ዕቃዎች የማስተዋወቁ ተግባር በተጠናቀቀ በሁለት ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ መውጣት አለባቸው፡፡

፫/ ከግንባታ ሥራና ከምክር አገልግሎት ወይም በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ወደ አገር የገቡ እቃዎች በፕሮጀክት ስምምነት በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሰው መውጣት አለባቸው፡፡

፬/ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ እቃ በዚህ አዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ተመልሶ ከአገር ሊወጣ የማይችል መሆኑን አስመጪው ከጠየቀና በቂ ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ባለስልጣኑ የጊዜ ገደቡን ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

5/ The Authority may permit the transfer of temporarily imported goods for construction works or consultancy services, within the authorized period, to other duty free right holders with respect to similar goods.

6/ Customs duties and taxes shall be paid on the depreciated values of temporarily imported goods up on their re-exportation based on the tariff currently applicable.

7/ Any person who transfers temporarily imported goods to another person in accordance with sub-article (5) of this Article shall have the obligation to pay duties and taxes on the depreciated value of the goods calculated for the period from the date of importation until the date of transfer.

8/ The project owner where temporarily imported goods, without payment of duties and taxes, are deployed shall inform the Authority, in writing, the completion of the project, prior to settlement of final payments, or any period of extension of the project.

9/ The conditions under which temporarily imported goods may remain within the country and the manner of payment of duties and taxes shall be determined by the directives to be issued by the Ministry of Finance and economic development.

## 55. <u>Time Limit</u>

1/ Imported goods for tourism, cultural exchange or technology transfer shall be re-exported within six months.

2/ Imported goods for trade promotion shall be re-exported within two months.

3/ Imported goods for construction works and consultancy services or as per a project agreement shall be re-exported within the time limit prescribed in the agreement.

4/ The Authority may extend the time limit where the importer proves on acceptable ground that the goods imported temporarily can not be re-exported within the time specified time.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት እቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ እቃው ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል::

## ፶፮. በጊዜያዊነት ወጥተው የሚመለሱ ዕቃዎች

፩/ በሚከተሉት ምክንያቶች በጊዜያዊነት ለመውጣት የጉምሩክን ሥነ-ሥርዓት የፈጸሙ ዕቃዎች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ተመልሰው መግባት ይችላሉ፤

ሀ) በአገር ውስጥ ለመጠገን ወይም ለመታደስ የማይችሉ በመሆናቸው ምክንያት የተከፈለባቸው ቀረጥ ተመላሽ ሳይደረግ ተጠግነው ወይም ታድሰው ለመመለስ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች፤

ለ) በጊዜያዊነት አገር ውስጥ የገቡና በአገር ውስጥ ለመጠገን ወይም ለመታደስ ባለመቻላቸው ምክንያት በገቡበት ጊዜ የተሰጠው ዋስትና ሳይወርድ በውጭ አገር ታድሰው ወይም ተጠግነው እንዲመለሱ የሚላኩ ዕቃዎች፤

ሐ) ወደውጭ አገር ለሥራ የሚሄድ ሰው የሚሄድበትን ሥራ ለማከናወን የሚጠቀምባቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች፣ የግል ተሽከርካሪ፣ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፤

መ) ለንግድና፣ ለባህል፣ ወይም ለማናቸውም ዓይነት ትርዒቶች ወይም ኢግዚቢሽኖች ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) ወይም (ለ) መሠረት ተመልሰው በሚመጡ ዕቃዎች ላይ ለጥገና ወይም ለእደሳ በወጣው ወጪ መጠን ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል::

፫/ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር በተፈቀደ ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር፣ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደውጭ አገር ሄደው ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው መግባት የሚችሉት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው የመጡ እንደሆነ ብቻ ነው::

## ፶፯. ተመልሰው ስለሚወጡና ተመልሰው ስለሚገቡ ዕቃዎች

፩/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተብሎ የተመዘገበ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡ ሕግን የማይፃረር ከሆነ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከመፈፀሙ በፊት ወደ ውጭ ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ የቀረጥና ታክሱን ፭ በመቶ ተከፍሎበት እንዲወጣ ሊፈቀድ ይችላል::

5/ The security provided for temporarily imported goods shall be transferred to the government treasury if the goods are not re-exported within two months after the completion of the specified period, unless the period is extended in accordance with sub-article (4) of this Article.

## 56. Temporary Export

1/ Goods exported temporarily by completing customs formalities for the following reasons may be allowed to re-enter the country without payment of duties and taxes:

a) imported goods sent abroad for repair and maintenance without repayment of duties and taxes;

b) temporarily imported goods sent abroad for repair and maintenance without cancellation of the guarantee given at the time of their importation;

c) personal effects, automobiles for personal use, machinery and equipment taken out by a person for the purpose of carrying out his work abroad;

d) goods exported for trade fair, exhibition or cultural show.

2/ Good returning pursuant to sub-article 1(a) or (b) of this Article shall be subject to duties and taxes on the cost of maintenance and repair incurred abroad.

3/ Goods may be eligible for exemption from duties only if returned from abroad within one year, unless a longer period is specified in an agreement approved by the Ministry of Finance and economic development.

## 57. Re-Exportation and Re-Importation of Goods

1/ Goods imported and declared for home consumption that are not prohibited or the entrance of which is not contrary to the law may be re-exported at the request of the importer before completing customs formalities upon payment of 5% of the duties and taxes to be paid on the goods.

፪/ የአገር ውስጥ ምርት ሆነው ወደ ውጭ ከተላኩ በኋላ በሽያጭ ውሉ ወይም በንግድ ግንኙነት የተመለከተውን የጥራት ደረጃ ባለማሟላታቸው ምክንያት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከተመለሱ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ፡፡

፫/ በባለጉዳዩ ጥያቄ መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በአሳማኝ ምክንያት ሊራዘም ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃዎች ተመልሰው ወደ አገር የሚገቡት ወደ ውጭ ከመላካቸው በፊት የመጨረሻ ጥቅማቸውን ታሳቢ በማድረግ ቀረጥ ተቀንሶላቸው ወይም ሙሉ ለሙሉ ተነስቶላቸው ከጉምሩክ ክልል ለነፃ ዝውውር የተለቀቁና ለተመሳሳይ ተግባር የሚውሉ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

፭/ ተመልሰው የሚገቡ ዕቃዎች ለተመሣሣይ ዓላማ የማይውሉ ከሆነ የሚከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ዕቃው ለመጀመሪያ ጊዜ ለነፃ ዝውውር በተለቀቀበት ጊዜ በተከፈለው መጠን ይቀንሳል፡፡

፮/ ቀደም ሲል የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ዕቃው ተመልሶ ሲገባ ከሚከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ የሚበልጥ ቢሆን ገንዘቡ ተመላሽ አይሆንም፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ዕቃው ወደ ውጭ በተላከበት ሁኔታ የሚገኝ ካልሆነ በስተቀር በንዑስ አንቀጹ ላይ የተደነገገው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፯) የተደነገጉት ማካካሻ ተደርጕባቸው በሚመለሱ፣ ቀደም ሲል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው በተላኩ ወይም በወጡ እና በአገር ውስጥ የምርት ስርዓት ከተፈፀመባቸው በኋላ በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፱/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ዝርዝር አፈፃፀም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ Exported domestic goods that have been returned within one year because of their failure to meet the quality standards specified by the contract of sale or business relation that has been the basis for their export shall be relieved from customs duties and taxes.

3/ The period specified in sub-article (2) of this Article may be extended at the request of the interested party on justifiable grounds.

4/ Without prejudice to the provision of sub-article (2) of this Article, were re-imported goods prior to their exportation from the customs territory had been released for free circulation at a reduced import duty or totally relieved from import duty on account of their end use shall be granted only where they are re-imported for the sane purpose

5/ Where the goods are not re-imported for the same purpose, the amount of customs duty shall be reduced by the amount of the duty paid on their first release for free circulation.

6/ Where the amount of the previously paid customs duty in higher than the amount of duty payable on re-importation, refund shall not be granted.

7/ The provisions of sub-article (2) of this Article shall not apply in the case of goods exported from the customs territory under the outward processing procedure unless those goods remain in the same state in which they were exported.

8/ The provisions of sub-article (2) to (7) of this Article shall apply *mutatis mutandis* to the return of compensating products previously exported or re-exported sub-segment to an inward processing procedure.

9/ The detailed application of the provisions of this Article shall be prescribed by directives to be issued by the Authority.

## ፶፰. <u>በምትክነት ስለሚገቡ ዕቃዎች</u>

፩/ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ ከጉምሩክ ቁጥጥር ሳይወጣ በስህተት፣ በብልሽት፣ ለታለመለት ዓላማ መዋል ካለመቻል፣ ወይም የተሟላ ካለመሆን የተነሳ በዋራንቲ ሰርተፊኬት ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ እንዲወጣ በአስመጪው ጥያቄ ከቀረበ ዕቃው ከአገር እንዲወጣ ተደርጐ በምትክነት የሚመጣው ተመሣሣይ ዕቃ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት እንዲገባ ሊፈቀድለት ይችላል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ዝርዝር አፈፃፀም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## ፶፱. <u>ዕቃዎችን ለነፃ ዝውውር ስለመልቀቅ</u>

፩/ በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ለነፃ ዝውውር አይለቀቅም::

፪/ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ተፈጽሞበት ለነፃ ዝውውር የተለቀቀ ማናቸውም እቃ አገር ውስጥ እንደተመረተ እቃ ይቆጠራል::

፫/ ለነፃ ዝውውር የተለቀቀ ዕቃ እንደ አገር ውስጥ ዕቃ የሚታይበትን ሁኔታ በሚከተሉት ምክንያት ሊያጣ ይችላል፤

ሀ) ዕቃዎቹ ከተለቀቁ በኋላ ለነፃ ዝውውር የተለቀቀበት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ሕጋዊነቱን ካጣ፣

ለ) ወደ ውጪ የሚላክ ምርት ለማምረት በጥሬ ዕቃነት የገባና በቀረጥ ተመላሽ ስርዓት የሚስተናገድ ሲሆን፤

ሐ) የተበላሸ ወይም ጥራቱን ያልጠበቀ በመሆኑ ምክንያት በተገባው ውል መሰረት ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ የሚደረግ ሲሆን፤ ወይም

መ) ዕቃው ተመልሶ ሲወጣ ወይም በባለሥልጣኑ ለተፈቀደ አገልግሎት ብቻ ሲውልና ቀረጥና ታክስ ተመላሽ የሚደረግበት ሲሆን:

## 58. <u>Replacement Procedure</u>

1/ Goods imported for home consumption, because of their incompatibility to their intended purpose, defect, error of consignment or their incompleteness, may be allowed to be re-exported and replaced without additional payment of duties and taxes upon the request of the importer within the time specified under the warranty certificate before their release for free circulation.

2/ The detailed application of the provisions of sub-article (1) of this Article shall be prescribed by directives to be issued by the Authority.

## 59. <u>Release of Goods for Free Circulation</u>

1/ Unless otherwise provided by law, any goods may not be released before the payment of customs duties and taxes.

2/ Any imported goods that have completed the necessary customs formalities and released for free circulation shall be considered as domestic goods.

3/ Goods released for free circulation shall lose the status of domestic goods where:

a) the customs declaration for their release for free circulation is invalidated;

b) they are imported for inward processing and treated under the drawback procedure;

c) they have to be re-exported in accordance with the terms of the contract due to the fact that they are defective or fail to meet the required standards; or

d) they are re-exported or used only for the permitted purpose and subject to drawback system.

## ምዕራፍ ስምንት

## የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያን ለመሸፈን የሚሰጥ ዋስትና

### ፷. ጠቅላላ

፩/ ባለሥልጣኑ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያ መከፈሉን ለማረጋገጥ ዋስትና ሊጠይቅ ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በባለሥልጣኑ የሚጠየቅ ዋስትና የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ ወይም የባንክ የዋስትና ሰነድ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በፅሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ሊሆን ይችላል::

፫/ ባለሥልጣኑ ለአንድ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎች ማረጋገጫ አንድ ዋስትና ብቻ ይጠይቃል፤ ሆኖም ለጉምሩክ የሚከፈል ቀረጥና ታክስ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ በሚሆነው ሰው ጥያቄ መሠረት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ኦፕሬሽኖች ምክንያት የሚከሰት ክፍያን የሚሸፍን ዋስትና እንዲሰጥ በባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል::

፬/ ባለሥልጣኑ ዋስትናው እዳው ከሚመለከተው ሰው ውጭ በሆነ በሌላ ሰው እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል::

፭/ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም በሚያቀርቡት የደብዳቤ ዋስትና ሊስተናገዱ የሚችሉ ሲሆን የጥሬ ገንዘብ፣ የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና እንዲሰጡ አይገደዱም::

፮/ ባለስልጣኑ የቀረበው ዋስትና የዕዳ ክፍያውን የማይሸፍን ሆኖ ካገኘው፣ ባለዕዳው ተጨማሪ ዋስትና እንዲያቀርብ ወይም የመጀመሪያውን ዋስትና በሌላ እንዲቀየር ማድረግ ይችላል::

፯/ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳው በከፊል ከተጠናቀቀ ባለጉዳዩ በሚጠይቀው መሠረት ዋስትናው ይቀነሳል::

### ፷፩. ዋስትና የሚጠይቅባቸው ሁኔታዎች

፩/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ ዋስትና በመቀበል ዕቃዎችን ሊለቅ ይችላል፤

ሀ) የጉምሩክን ሥነ-ሥርዓት ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሰነዶች በበቂ ምክንያት ያልተሟሉ ሲሆንና እነዚህን ሰነዶች ለማሟላት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግ፤

## CHAPTER EIGHT

## SECURITIES TO GUARANTEE PAYMENT OF CUSTOMS DUTIES AND TAXES

### 60. General

1/ The Authority may requires security to be provided in order to ensure payment of customs duties and taxes.

2/ The security specified under sub-article (1) of this Article may be cash deposit, bank guarantee, insurance bond or a written commitment.

3/ The Authority shall require only one security to be provided in respect of one payment of customs duties and taxes and other charges; provided, however, that at the request of the debtor, the Authority may permit comprehensive security to be provided to cover payments arising from two or more customs operations.

4/ The Authority may authorize the security to be provided by a person other than the debtor.

5/ Government institutions that are financed by government allocated budget may provide letter of guaranty with out being required to provide security to cover customs duties and taxes in the form of cash deposit, bank guarantee or insurance bond.

6/ Where the Authority establish that the security provided does not fully cover the liability, it shall require the debtor to provide additional security or to replace the original security with a new one.

7/ Where the customs duty and tax liability has been extinguished in part, the security shall be reduced accordingly at the request of the debtor.

### 61. Conditions of Security

1/ The Authority may release goods upon receiving security for the following reasons:

a) when additional time is required to produce complete documents necessary for the completion of customs formalities;

ለ) ቀረጥ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ተመልሰው መውጣታቸውን ለማረጋገጥ፤

ሐ) ተሳላፊ ዕቃዎች በተወሰነው መስመር ተንጉዘው በተፈቀደ መውጪያ በር ከአገር መውጣታቸውን ወይም መራገፊያቸው ወደሆነው የጉምሩክ ጣቢያ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ፤

መ) የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ተሰጥቷቸው በገቡ ጥሬ ዕቃዎች ተመርተው ወደውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች መውጣታቸውን ለማረጋገጥ፤

፪/ የወንጀል ክስ የሚቀርብባቸውና ለፍርድ ቤት በማስረጃነት የሚፈለጉ ካልሆነ በስተቀር የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ የሚያዙ ዕቃዎችና ማጓጓዣዎች ጉዳይ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ዋስትና ተቀብሎ ባለሥልጣኑ መልቀቅ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ዕቃዎች በዋስትና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፪. ዋስትናን የተመለከቱ መብትና ግዴታዎች

፩/ የዋስትና አይነቶችን በሚመለከት በዚህ አዋጅ የተደነገገት ቢኖሩም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) ለሚሸፈኑ ጉዳዮች የጥሬ ገንዘብ ዋስትና በመያዣነት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቅ ሰው በዚህ ሕግ ከተደነገጉት የዋስትና አይነቶች አንዱን መምረጥ ይችላል፤ ሆኖም ባለስልጣኑ የተመረጠው ዋስትና ከጉምሩክ አሰራር ጋር የማይጣጣም ከሆነ ባለስልጣኑ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የተቀበለው የዋስትና ዓይነት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንዲያገለግል ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ ዋስትና ሰጪው ከባለዕዳው ጋር በአንድነትና በነጣላ እዳውን ከነወለዱና ወጪውን የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፭/ ዋስትና የተገባለት ግዴታ ሙሉ በሙሉ እንደተፈፀመ ዋስትናው ቀሪ ይሆናል፡፡ ባለሥልጣኑ ዋስትና የተገባለት ግዴታ የተፈፀመ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

b) to ensure the re-exportation of goods imported on temporary basis;

c) to ensure that transit goods exit through the approved customs route or arrive at the predetermined customs point of destination;

d) to ensure that goods which are produced by duty relieved imported raw materials are exported;

2/ Goods and means of transport seized due to contravention of customs law may, unless they are subject to criminal charges and required as evidence by court, be released by the Authority upon receiving security until a final administrative decision is passed with respect to them.

3/ The Authority may issue detailed directives on the release of goods on security basis pursuant to this Article.

## 62. Right and Obligations Related to Security

1/ Notwithstanding the provisions of this Proclamation relating to types of security, the Authority my require cash deposit for goods falling under sub-article 1(a) of Article 61 of this Proclamation.

2/ Any person required to provide security shall be allowed to choose any form of security prescribed under this Proclamation; provided, however, that the Authority may reject the type or security chosen where it is incompatible with the required customs procedure.

3/ The Authority may require that the type of security chosen be maintained for a specified period.

4/ A guarantor shall be jointly and severally liable with the debtor for the secured amount of a customs debt, including interests and costs incurred.

5/ Any security shall be extinguished upon the full settlement of the debt. The Authority shall, when requested, issue evidence showing the extinction of the secured debt.

## ፷፫. የዋስትና መጠን

፩/ ለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርበው ዋስትና መጠን፣

ሀ) ዋስትናው በሚቀርብበት ጊዜ ሊከ ፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች በእር ግጠኝነት የሚታወቁ ከሆነ ከነዚሁ መጠን ማነስ የለበትም፤

ለ) ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች መጠን በእርግጠኝነት ማወቅ ባልተቻለበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በገመተው ከፍተኛ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች መጠን ይሆናል።

፪/ ለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች የቀረበው ዋስትና መጠን ዋስትናው በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥ ሊለያይ የሚችል ከሆነ በማንኛውም ጊዜ የሚኖረውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሊሸፈን የሚችል መጠን ሊሆን ይገባል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የድህረ ዕቃ አወጣጥ ምርመራ፣ በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ እና ስለቀረጥና ታክስ ተመላሽ

## ፷፬. የድህረ ዕቃ አወጣጥ ምርመራ

፩/ ባለስልጣኑ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠ ናቀው የተለቀቁ ዕቃዎችን የጉምሩክ ዲክ ላራሲዮን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በድጋሚ በድንገተኛ ፍታሻ ሊመረምር ይችላል።

፪/ ባለስልጣኑ ዕቃዎች ከተለቀቁ በኋላ በጉም ሩክ ዲክላራሲዮን ውስጥ ያሉትን ዝርዝ ሮች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፣ ከወጪ ወይም ገቢ ዕቃዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸ ውን የንግድ ሰነዶችና መረጃዎችን በድኅረ እቃአወጣጥ ሥርአት ሊመረምር ይችላል።

፫/ ባለሥልጣኑ የሚያደርገው ምርመራ ዕቃዎ ቹን በማስመጣትና በመላክ የንግድ ሥራ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በተሳተፈው ሰው ቅጥር ግቢ ወይም ለምርመራ የተፈ ለጉትን መረጃዎችና ሰነዶች በያዘ ሌላ ማናቸውም ሰው ቅጥር ግቢ ሊከናወን ይችላል።

፬/ ባለስልጣኑ ባደረገው የምርመራ ግኝት የጉምሩክ አሰራር ደንብ መጣሱ ከተረጋገጠ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ወይም የሁለቱንም ኃላፊነት የሚያስከትል ውጤት ይኖረዋል።

## 63. Amount of Security

1/ The amount of security to be provided pursuant to the provisions of this Proclamation shall:

a) be equal to the precise amount of customs duties and taxes and other charges for which it is provided, where that amount can we established with certainty at the time when the security is provided;

b) in cases, where the amount can not be established with certainty, be equal to the maximum amount as estimated by the Authority.

2/ Where comprehensive security is provided for customs duties and other charges which vary in amount during the secured period, the amount of such security shall be set at a level enabling the customs debts in question to be covered at all times.

## CHAPTER NINE

## POST CLEARANCE AUDIT, DEFERRED PAYMENT AND RE-PAYMENT OF DUTIES AND TAXES

## 64. Post Clearance Audit

1/ The Authority may, after the release of goods, undertake surprise inspection to ascertain the accuracy of customs declaration.

2/ The Authority may, after the release of goods, and for the purpose of ascertaining the accuracy of particulars contained in customs declaration, inspect commercial documents and data relating to the import or export operations in respect of the goods.

3/ The Authority's inspections may be carried out at the premises of the person who is directly or indirectly involved in the business operations of the import or export of the goods or at the premises of any other person in possession of the data and documents subject to the inspection.

4/ The findings of post-clearance examination may, if it reveals that the provisions governing customs formalities have been breached, entail civil or criminal liability or both.

፭/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በባለሥልጣኑ የሚደረገው ምርመራ ሊካሄድ የሚችለው የጉምሩክ ዴክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ እስከ አስር ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው::

## ፷፭. በልዩነት ስለሚፈለግ ቀረጥና ታክስ

፩/ ወደ አገር ለገባ ወይም ከአገር ለወጣ ዕቃ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለስልጣኑ የዕቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ጎድሎ ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተጠየቀውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ክፍያውን በመቃወም ይግባኝ ያላቀረበ ባለዕዳ ለቀረጥና ታክሱ አሰባሰብ በገቢ ግብር ሕግ ላይ የተመለከተው ንብረትን ይዞ የማስፈጸም ስርዓት ተፈፃሚ ይሆንበታል::

## ፷፮. ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ

፩/ በዕቃዎች አሰያየም፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሳብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ለከፋዩ ተመላሽ ይደረጋል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አጠናቆ ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ከቀረበ ብቻ ነው::

## ምዕራፍ አስር
## ስለቀረጥ ነፃ መብት ሥርዓት

## ፷፯. የቀረጥ ነፃ መብት አሰጣጥ

የገቢና ወጪ ዕቃዎችን በሚመለከት የቀረጥ ነፃ መብት በሕግ፣ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር በሚያወጣው መመሪያ ሊሠጥ ይችላል::

5/ The Authority's inspection under this Article may be carried out only within ten years from the date a customs declaration has been accepted.

## 65. Deferred Payment

1/ Where the amount of customs duties and taxes paid in respect of goods imported or exported is less than the actual amount required, the difference shall be collected within ten years of the date of such difference by the Authority from the owner or his agent.

2/ The seizure procedure prescribed under the Income Tax Proclamation shall be applicable to the property of a debtor who is not willing to pay the customs duties and taxes referred to in sub-article (1) of this Article or has not lodged an appeal against the decision thereto.

## 66. Reimbursement of Duties and Taxes

1/ Reimbursement claims shall be granted if duties taxes are overcharged as a result of incorrect commodity classification, tariff setting, valuation or other calculation mistakes.

2/ Claims for reimbursement of duties and taxes submitted pursuant to sub-article (1) of this Article shall be considered only if it is submitted within six month after the goods are imported or exported upon completion of customs formalities.

## CHAPTER TEN
## RELIEF PROCEDURE

## 67. Granting Duty Free Privilege

Duty free privilege with respect to import and export goods may be granted by the law, international agreement to which Ethiopia is a party or by the directives to be issued by the Ministry of Finance and economic development.

**፷፰. ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ስለገባ ዕቃ**

፩/ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባን ዕቃ ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈልበት ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ለሌው ማንኛውም ሰው ማስተላለፍ ወይም የቀረጥ ነፃው መብት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ መገልገል ወይም በሌሎች ሰዎች ይዞታና አገልግሎት እንዲውል ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባ እቃ ተመልሶ ከአገር ሲወጣ ወይም ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ላለው ሰው ሲተላለፍ ወይም ቀረጥና ታክሱ ተከፍሎበት ለሌላ ሰው ሲተላለፍ ይችላል፡፡ ቀረጥና ታክሱም የሚሰላው ዕቃው በተላለፈበት ጊዜ በሚያወጣው ዋጋና ፀንቶ ባለው የታሪፍ ልክ መሠረት ይሆናል፡፡

፫/ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጠፋ ወይም ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ አስመጪው ለባለስልጣኑ ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ የቀረበለት ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ቀረጡ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ ለኢንቨስትመንት ሥራ የቀረጥ ነፃ መብት የተሰጠው ሰው ከቀረጥ ነፃ ሆነው የገቡ ዕቃዎችን ለሌላ ሰው ሲያስተላልፍ ወይም የኢንቨስመንት ፈቃዱን ሲመልስ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የክሊራንስ ሰነድ የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፭/ ፈቃድ የሚሰጠው ወይም ምዝገባ የሚያከናውነው አካልም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ሁኔታ መሟላቱን የማረጋገጥና ክትትል የሚደረግባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን እንዳወቀ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብትን ስለማስከበር

**፷፱. በጉምሩክ ክልል መግቢያና መውጫ በሮች የሚደረግ ቁጥጥር**

፩/ አግባብነት ባለው ሕግና ዓለም አቀፍ ስምምነት የተወሰኑትን የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብቶች በሚፃረር ሁኔታ ዕቃ ከውጭ ማስገባት ወይም ወደ ውጭ መላክ ወይም ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ባለስልጣኑ በአዕምሯዊ ንብረት ባለመብቱ ጥያቄ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሲቀርቡለት መብትን ይፃረራሉ ተብለው የሚጠረጠሩትን ከውጪ የሚገቡ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም የሚተላለፉ ዕቃዎችን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ማገድ ወይም እቃዎችን ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

**68. Duty Free Imports**

1/ It is prohibited to transfer duty free imported goods to a person who is not enjoying similar privileges or use them for a purpose other than which the duty free privilege is granted or place them under the possession and service of others, before payment of the duties and taxes applicable to them.

2/ Any duty free imported goods may be re-exported or transferred to a person who enjoys similar privileges or transferred to any person upon payment of the duties and taxes. The duties and taxes shall be calculated at value of the goods and tariffs rate prevailing during the time of disposed.

3/ Where duty free imported goods are lost or damaged the importer shall forthwith report to the Authority. And where the report proves the situation to the satisfaction of the Authority, the whole or part of the duties and taxes may be cancelled.

4/ Any persons who enjoys duty free privileges for investment purposes shall be required to produce a clearance document from the Authority prior to the transfer of duty free imported goods to other persons or the return of his license.

5/ The licensing or registry office shall have the obligation to ascertain the fulfillment of the conditions stated under sub-article (4) of this Article and to inform the Authority incases of conditions that require follow up.

## CHAPTER ELEVEN
## ENFORCEMENT OF INTELLECTUAL PROPERTY RIGHTS

**69. Border Enforcement of Intellectual Property Rights**

1/ The importation, exportation or transit of goods which infringe intellectual property rights stipulated in the relevant legislations and international conventions.

2/ The Authority shall upon request of an intellectual property right holder suspend customs formalities and withhold goods in case of imported, exported or transited goods suspected to be in violation of intellectual property rights.

፫/ ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት በበቂ መረጃ ላይ በመመስረት ማንኛውም አይነት የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት ተጥሷል ብሎ ሲያምን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም እንዲቆምና ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች እንዳይለቀቁ ሊያግድ ይችላል።

## ፸. እገዳን ስለማሳወቅ

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀም እንዲቆምና ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ወደ ውጪ የሚላክ ዕቃ እንዳይለ ቀቅ ሲያግድ፣

ሀ) ለአስመጪው ወይም ለላኪው፣

ለ) ለአዕምሯዊ ንብረት መብት ባለ ቤቱ፣ እና

ሐ) ለኢትዮጵያ የአዕምሯዊ ንብረት ጽህፈት ቤት፣

ማሳወቅ አለበት።

፪/ ባለሥልጣኑ ማስታወቂያውን ለሚመለከታ ቸው ወገኖች ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ፲ የስራ ቀናት ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ካልተገለፀለት በስተቀር ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል እገዳውን የሚያራዝም እርምጃ ካልተወሰደ የተያዘው ዕቃ መልቀቅ አለበት።

፫/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰውን የጊዜ ገደብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ሰዎች በአንዳቸው በጽሑፍ ጥያቄ ሲቀርብለትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ፭ የሥራ ቀናት ሊያራዝም ይችላል።

## ፸፩. እቃዎችን የመለየት መብት

የመብቱ ባለቤት፣ የእቃው አስመጪ፣ ላኪ ወይም ባለቤት የተያዙት ዕቃዎች በጉምሩክ ጣቢያ ውስጥ እያሉና በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ በማንኛውም ተገቢ መንገድ የመለየትና የመመርመር መብት ይኖረዋል።

## ፸፪. አዋጁ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው እቃዎች

በዚህ አዋጅ ከአዕምሮአዊ ንብረት መብቶች ጋር በተያያዘ የተደነገጉት አንቀጾች የንግድ ባልሆኑና መንገደኞች ይዘዋቸው በሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

3/ The Authority may upon its own initiative suspend customs clearance and release of imported or exported goods if it has sufficient evidence to believe that an intellectual property right has been infringed.

## 70. Notification of Suspension

1/ Where the Authority decides to suspend customs clearance and release of imported or exported goods pursuant to sub-article (3) of Article 69 of this Proclamation, it shall notify same to:

a) the importer or exporter;

b) the holder of the intellectual property right; and

c) the Ethiopian intellectual property right office.

2/ If within a period not exceeding ten working days after the notice of the suspension has been notified to interested parties or that the competent authority has taken provisional measures prolonging the suspension, the goods shall be released.

3/ Where the Authority, upon the request of a person referred to in sub-article (1) of this Article, finds it necessary, it may extend the time limit referred to in sub-article (2) of this Article for additional five working days.

## 71. Right of Identifying Intellectual Property

The right holder, importer, exporter or the owner of the goods, shall have the right to identify withheld goods in any appropriate manner, including the right to inspect the goods, provided that such inspection is done in the customs premises and under customs supervision.

## 72. Exception

Measures related to the protection of intellectual property rights provided in this Proclamation shall not apply to non-commercial and personal effects brought by passengers.

## ምዕራፍ አስራ ሁለት
## ከጉምሩክ ሥራ ጋር በተያያዘ የተጣሉ ሌሎች ግዴታዎች

**፸፫. ጠቅላላ**

በዚህ አዋጅ ከጉምሩክ ሥራ ጋር በተያያዘ የተጣሉት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱት ግዴታዎች አግባብነት ባላቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**፸፬. ስለዕቃዎች መግለጫ የማቅረብ ግዴታ**

፩/ የመጓጓዣው ኃላፊ፣ የተጫነው ዕቃ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የመጣ ወይም በመጋዘን ውስጥ የሚቆይ ወይም በጊዜያዊነት ወደ አገር የሚገባ ወይም በመጣበት ማጓጓዣ ወይም ሌላ ማጓጓዣ በመቀየር አገር አቋርጦ የሚሄድ መሆኑን ለይቶ በማሳወቅ፣ ወደጉምሩክ መጋዘን እንዲገባ ወይም የተላለፊነት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈጸምበት ማድረግ ይኖርበታል።

፪/ ወደጉምሩክ መጋዘን እንዲገባ የተደረገ ዕቃ ርክክብ እንደተፈጸመ የጉምሩክ መጋዘን ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገኘው መረጃ መሠረት ዕቃውን ለይቶ ይመዘግባል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) እና በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፫ እስከ ፲፭ በተመለከተው መሠረት መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንደመጣ ተቆጥሮ ቀረጥና ታክስ ይከፈልበታል።

፬/ የጤና ምርመራ ሊደረግበት የሚገባ ዕቃ ከማጓጓዣው እንደተራገፈ አስፈላጊው የጤና ምርመራ እስከሚፈጸም ድረስ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይቶ በኳራንቲን ክልል መቆየት አለበት።

፭/ በባህሪያቸው ምክንያት ተቀጣጣይና አደገኛ የሆኑ ዕቃዎች ከማጓጓዣው ከመራገፋቸው በፊት በተለየ መጋዘን እንዲቆዩ ወይም በአስቸኳይ ከወደብ እንዲወጡ የማጓጓዣው ኃላፊ ማስታወቅ አለበት።

፮/ ስለዕቃዎች የተሰጠው መግለጫ ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነና ድርጊቱም ሆን ተብሎ የተፈፀመ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ማረሚያ እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላል።

## CHAPTER TWELVE
## OTHER OBLIGATIONS RELATED TO CUSTOMS OPERATION

**73. General**

Without prejudice to the obligations related to customs operations provided for under this Proclamation, the provisions of this Chapter shall apply to relevant persons.

**74. Obligation to Present Goods Declaration**

1/ The master of a means of transport shall provide information regarding the loaded goods, identifying its purpose either for home consumption, warehousing, temporary admission, transiting or transshipment and deliver them to customs warehouse or complete the necessary transit customs formalities.

2/ The warehouse operator on receiving the goods shall identify and register the goods on the basis of the information supplied in accordance with sub-article (1) or this Article.

3/ Goods without declaration pursuant to sub-articles (1) and (2) of this Article and Articles 13 to 15 or this Proclamation shall be presumed to have been imported for home consumption and shall be subject to payment of duties and taxes accordingly.

4/ Goods requiring passing quarantine examination shall, as soon as they are discharged from the means of transport, be stored in a separate zone until the accomplishment of quarantine examinations.

5/ The master of a means of transport shall provide information regarding inflammable or dangerous goods, before they are discharged, so that they shall be stored in a separate warehouse or be removed urgently from the port.

6/ Where incomplete or erroneous goods declaration is presented and if ascertained that it is due to inadvertent error, an amendment shall be allowed by furnishing supplementary report.

፯/ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ ውጪ አገር በሚሄድ ማጓጓዣ ላይ የተጫኑና ለማጓጓዣው አስፈላጊ የሆኑ ነዳጅ፣ ቅባት፣ መለዋወጫዎችና ዕቃዎች ወይም በጉዞ ላይ ለመንገደኞችና ለሠራተኞች የሚውሉ ምግብና መጠጦች ወይም የስጦታና የሽያጭ እቃዎች በጉዞ ወቅት ጥቅም ላይ ከዋሉ ወይም ከተሸጡ ማጓጓዣው ዕቃዎቹ ወደተጫኑበት የጉምሩክ ጣቢያ ሲመለስ የማጓጓዣው ሃላፊ ጥቅም ላይ የዋለውን፣ በስጦታ የተላለፈውን፣ የተሸጠውንና የተረፈውን የሚያሣይ መግለጫ ማቅረብ አለበት::

## ፸፭. የማጓጓዣ ኃላፊ ግዴታ

፩/ ማንኛውንም የማጓጓዣ ሀላፊ፣

ሀ) ወደአገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ማጓጓዣ በባለስልጣኑ ከተፈቀደው የጉዞ መስመር ውጭ ማንቀሳቀስ፣ ማቆም፣ መንገደኛ ማሳፈር፣ ዕቃ ማውረድ ወይም ማራገፍ የለበትም::

ለ) ጭነት ወይም ሰው ለማጓጓዝ የሥራ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ አግባብ ላለው የጉምሩክ ሹም ያቀርባል፤

ሐ) ማጓጓዣው ወደጉምሩክ ወደብ በደረሰ ወይም ከጉምሩክ ወደብ ከመነሳቱ በፊት በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የሚጫነውን ወይም የሚራገፈውን ወይም የሚሳፈ ውን ወይም የሚወርደውን ወይም አገር አቋርጦ የሚሄደውን እንዲሁም በማጓጓዣ ውስጥ የሚቀረውን ዕቃና መንገደኛ የሚያመለክት ዝርዝር መግለጫ አግባብ ላለው የጉምሩክ ሹም ማቅረብ አለበት፤

መ) ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠውና ጉምሩክ ሹም በሥፍራው ሳይገኝ መንገደኛ ማሳፈር ወይም ማውረድ ወይም ዕቃ መጫን ወይም ማራገፍ አይችልም፤

ሠ) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውም ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲጠጋ መፍቀድ የለበትም፤

ረ) ማጓጓዣው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የተፈፀመበትን ዕቃ ጭኖ እንዲንቀሳቀስ በጉምሩክ ሹም ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ ጉዞው ከ፳፬ ሰዓት በላይ ከዘገየ ወይም ከተሰረዘ ይህንኑ ለጉምሩክ ሹም በማሳወቅ ዕቃዎቹ እንዲራገፉና በባለሥልጣኑ ጥበቃ ሥር እንዲሆኑ ማድረግ አለበት::

7/ The master of a means of transport shall present a declaration, upon return to the initial loading customs port, about the consumed, sold or disposed and remaining fuel, lubricants, spare parts and other goods necessary for the operation of the means of transport or food staff, drinks and articles for gift or sale to passengers and employees onboard of the means of transport and which were loaded without payment of duties and taxes.

## 75. Obligation of Master of Means of Transport

1/ The master of any means of transport shall:

a) only use authorized customs routs for arrival and departure of the means of transport, for loading and unloading of goods, and for embarkation and disembarkation of passengers;

b) submit to the appropriate customs officer documents that show the means of transport is duly licensed to transport cargos or passengers;

c) submit manifest to the appropriate customs officer within 24 hours after the arrival or before departure of the means of transport that show the list of goods and persons loaded and taken onboard, discharged and stay onboard or continue in transit;

d) refrain from embarking or disembarking passengers or loading or unloading cargos in the absence of customs officer unless authorized or by the Authority;

e) never allow any unauthorized person to approach to the means of transport;

f) report to the customs officer and discharge the cargo for customs control where the time for departure of the means of transport is delayed for more than 24 hours or canceled after it is authorized to depart.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ማንኛውም ማጓጓዣ ከጉምሩክ ወደብ ውጭ ሊያርፍ ወይም ሊቆም ይችላል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ የማጓጓዣው ኃላፊ ሁኔታውን በአቅራቢያው ላለው የጉምሩክ ጽሕፈት ቤት ወይም በአካባቢው የጉምሩክ ጽሕፈት ቤት ከሌለ ለአካባቢው አስተዳደር ማሳወቅ አለበት::

**፸፮. <u>የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው ግዴታ</u>**

የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው የሚከተሉትን ግዴታዎችመፈጸም አለበት፤

ሀ) ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮ ዎች ንና ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መሳሪያዎችና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የማሟላት፤

ለ) ወደ መጋዘን የሚገቡና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው የሚወጡ ዕቃዎችን ባለሥልጣኑ በሚወስነው የመዝ ገብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መመዝ ገብና በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፤

ሐ) በመጋዘኑ የሚቀመጡትን ዕቃዎች እንደ ዓይነታቸውና እንደባህሪያቸው በመለየት ለደህንነታቸው ተስማሚ በሆነና ለቁጥ ጥር በሚያመች ሁኔታ የማስቀመጥ፤

መ) ባለሥልጣኑ የሚልካቸው የጉምሩክ ሹሞች ለሚያቀርቡት ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠትና ለቁጥጥርና ለምርመራ ሥራቸው የመተባበር፤

ሠ) በመጋዘኑ ውስጥ ገብተው የተፈቀደው የጊዜ ገደብ የሞላቸውን ዕቃ ዎች ዝርዝር በማውጣት ማሳወቅና ዕቃዎቹን ለባለሥልጣኑ የማስተላለፍ፤

ረ) በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ዕቃ ወደ መጋዘን እንዳይገባ ወይም ከመጋዘን እንዳይ ወጣ የመቆጣጠር፤

ሰ) የተሰጠውን የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በወቅቱ የማሳደስ፤

ሸ) ፈቃድ ያልተሰጣቸው ሰዎች ወደ መጋ ዘን እንዳይገቡ የመቆጣጠር፤

ቀ) የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የተጠናቀቀበትን ዕቃ ወዲያውኑ እንዲወጣ የማድረግ::

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article 1(a) of this Article, the master of any means of transport may, in case of *force majeure,* land or stop the means of transport at any place other than a customs port; provided, however, that he shall immediately report the incident to the nearest customs office or, in the absence of customs office, to the local administration office.

**76. <u>Obligations of warehouse Licensee</u>**

Any person licensed to establish a customs warehouse shall:

a) provide offices equipments and technological devices necessary for customs operations;

b) keep registration book in accordance with directive issued by the Authority for the goods entering into and cleared from the warehouse, and report to the Authority from time to time;

c) segregate goods on the basis of their type and nature for the purpose of their safe storage and convenience in control;

d) provide proper reply to the queries made by customs offices assigned by the Authority and cooperate for inspection and investigation;

e) report and transfer to the Authority those goods deposited in the warehouse for more than the time specified under this Proclamation;

f) ensure that no goods enter or removed from the warehouse without the permission of the Authority;

g) secure renewal of his customs warehouse license within the specified time;

h) prohibit unauthorized persons from entering the customs warehouse;

i) release goods from the customs warehouse upon the completion of customs formalities.

## ፸፯. የጉምሩክ ስነ ሥርዓት አስፈፃሚ ግዴታ

፩/ ማንኛውም ሰው የዕቃ አስመጪውን ወይም ላኪውን ወክሎ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አስፈፃሚነት ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የዕቃው ባለቤት የሙያ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማቅረብ ሳያስፈልገው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት መፈፀም ይችላል፡፡

፫/ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀመው በወኪል አማካኝነት ከሆነ ወኪሉና የእቃው ባለቤት ስለቀረጥና ታክስ ክፍያ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

፬/ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አስፈፃሚነት ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታና ባለፈቃዶች የሚኖሯቸው መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፸፰. መረጃ የመስጠት ግዴታ

፩/ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ ቀረጥ ያልተ ከፈለበት ወይም ባነስተኛ የተከፈለበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም የኮንትሮባንድ ዕቃ መኖሩን የሚያውቅ ማንኛ ውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ ጽሕፈት ቤት ወይም የሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል የሚሰጠው መረጃና ማንነቱ በሚስጥር ይጠበቃል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጸው መሠረት ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪው አካል በተሰጠ ማስረጃ መሠረት የተገኙት ዕቃዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ለማድረግ ለተባበሩት፣ ድጋፍና መረጃ ለሰጡት ሰዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወሮታ ይከፈላል፡፡

## ፸፱. መረጃዎችን ይዞ ስለማቆየት

፩/ ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሚያ ስፈልጉ ሰነዶችን ወይም መረጃዎችን የያ ዘና ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለ በት ሰው መረጃዎቹን ለአስር ዓመታት ይዞ ማቆየት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመ ለከተው ሰነዶችና መረጃዎች የሚቆዩበት ጊዜ የሚታሰበው፣

## 77. Obligations of Customs Clearing Agents

1/ Any person who engages in clearing goods on behalf of an importer or exporter shall be required to be licensed as a customs clearing agent.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the owner of goods shall, without showing certificate of professional competence, be able to complete customs formalities by himself.

3/ Where customs formalities are completed through a customs clearing agent, the owner of the goods and the agent shall jointly and severally be liable for the payment of customs duties and taxes.

4/ Conditions of licensing clearing agents, and their rights and obligations shall be prescribed by regulations to be issued hereunder.

## 78. Obligation to provide Information

1/ Any person who has information about uncustomed or less taxed or prohibited, restricted of contraband goods shall immediately inform the nearest customs office or law enforcement authority.

2/ The information supplied and the identity of the informant shall not be disclosed.

3/ Where the information supplied to the Authority or other law enforcement authority pursuant to sub-article (1) of this article leads to seizer of the goods, all persons that have provided information, cooperated and supported the Authority shall be rewarded in accordance with directives issued by the Authority.

## 79. Retaining Information

1/ Any person who is responsible to pay duties and taxes and thus possessed any documents or information necessary for customs formalities shall retain them for a period of 10 years.

2/ The period referred to in sub-article (1) of this Article shall count down from the day on which:

ሀ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ የገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞባቸው ከተለቀቁበት ቀን፣

ለ) የወጪ ዕቃዎች ዲክላራሲዮን ተቀባይነት ካገኘበት ቀን፣

ሐ) ከቀረጥ ነፃ ሆነው በጊዜያዊነት የገቡ ዕቃዎችን ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከተጠናቀቀበት ቀን፣

ጀምሮ ይሆናል።

፫/ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኙና ፲ ዓመት ያለፋቸው ዲክላራሲዮኖችና ደጋፊ ሰነዶች በማናቸውም ኤሌክትሮኒካል ዘዴ እንዲቀረፁ ተደርገው ሊወገዱ ይችላሉ።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተቀረፁ ሰነዶች በህግ ፊት እኩል ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

## . የመተባበር ግዴታ

፩/ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ በሥራ ላይ ያሠማራቸው ሠራተኞች ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዲችሉ ትብብር ማድረግ አለበት።

፪/ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት አካላት ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር በሚደረግ ስራ የመተባበር ኃላፊነት አለባቸው።

፫/ ኮንትሮባንድንና ሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር በሚደረግ ጥረት ባለሥልጣኑ ከአቅሙ በላይ ሲሆን፣ ከሚመለከታቸው የፌድራልና የክልል መንግስት የፀጥታ አስከባሪ አካላት ጋር በመሆን በጣምራ ስራውን ሊያከናውን ይችላል።

፬/ የጉመሩክ ሹም ተግባሩን ለማከናወን ዕርዳታ ሲጠይቅ ማናቸውም ሕግ አስከባሪ አካል ድጋፍ መስጠት አለበት።

፭/ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት አካላት ተገቢና ተመጣጣኝ ሃይል ተጠቅመው ሕገወጥ ስራን ማስቆም ይችላሉ።

a) goods imported for home consumption are released for free circulation upon the completion of customs formalities;

b) an export declaration is accepted for export goods;

c) customs formalities are completed to transfer goods imported temporarily on duty free basis.

3/ Customs declaration and supporting document accepted by the Authority and which elapsed 10 years may be disposed after being stored electronically.

4/ Documents retained pursuant to sub-article (3) of this Article shall have the same legal effect.

## 80. Duty to Cooperate

1/ Any person shall have the duty to cooperate with employees assigned by the Authority in discharging their official duties efficiently.

2/ Federal and regional state organs shall cooperate with the Authority in the fight against contraband.

3/ Where the Authority, in the fight against contraband, encounters circumstances which are beyond its control, it may discharge its duties in collaboration with the Federal and Regional enforcements organs.

4/ Any law enforcement body shall, upon request, assist a customs officer in discharging his duty properly.

5/ The bodies referred to in this Article may use appropriate and proportional force to stop an illegal activity.

## ምዕራፍ አስራ ሦስት
## የጉምሩክ ሹም ሥልጣንና ተግባር

### ፹፩. ጠቅላላ

፩/ የጉምሩክ ሹም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

ሀ) በመደበኛ ሥራው ላይ ባለበት ጊዜ ይህን አዋጅ ወይም ባለሥልጣኑ የሚያስፈፀማቸውን ሌሎች ሕጎች የተላለፉ ሰዎችን፣ እቃዎችንና የመጓጓዣ ዘዴዎችን ይፈትሻል፣ በቁጥጥር ሥር ያውላል፤ በዚህ አዋጅ መሰረትም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

ለ) ከጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ማስረጃዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሰወሩ ወይም ሊጠፉ ይችላሉ የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲያድርበት በማናቸውም ጊዜና ቦታ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብርበራ ማካሄድ ይችላል፤

ሐ) የጉምሩክ ሕጎች በመተላለፍ የተፈፀሙ ወንጀሎችን ምርመራ ያጣራል፣ መዝገብ ያደራጃል፤ አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ክስ እንዲመሰረት ለአቃቤ ሕግ ያስተላልፋል፤ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ በተደነገገው መሰረት ተጠርጣሪዎችን በዋስትና ሊለቅ ይችላል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) መሠረት በተካሄደ ብርበራ የተገኘ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፫/ የጉምሩክ ሹም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) የተመለከተውን ተግባር በማስፈጸም ረገድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ለፖሊስ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፬/ የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ህግ ለማስፈፀም ፍተሻ ሲያደርግ በቅድሚያ ማንነቱን የሚያስረዳ መታወቂያና ዩኒፎርም ማድረግ አለበት፡፡ ፍተሻውም በተመሳሳይ ፆታ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### ፹፪. የመፈተሽ፣ የመያዝና በቁጥጥር ሥር የማዋል ስልጣን

፩/ የጉምሩክ ሹም፣

ሀ) በማናቸውም ማጓጓዣ ውስጥ በመግባት የማጓጓዣ አላፊውን የግል መገልገያ ሳይጨምር በማጓጓዣ ውስጥ የሚገኙ ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን እቃዎች በመለየት፣ በመፈተሽና በማሸግ ለተገቢው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም መግለጫ እንዲቀርብባቸው ለማድረግ ይችላል፤

## CHAPTER THIRTEEN
## POWERS AND DUTIES OF CUSTOMS OFFICERS

### 81. General

1/ Any customs officer shall have the powers and duties to:

a) while in discharging his duties, examine and detain or seize persons or goods and means of transport contravening this Proclamation or other laws to enforced by the Authority; and shall take necessary measures in accordance with this Proclamation;

b) where there is sufficient ground to suspect an evidence relating to customs formalities may be lost within a short period of time, conduct a search at any time and place without court warrant;

c) investigate offences committed in violation of customs laws, prepare files, gather necessary evidences and forward same to the prosecutor to institute criminal proceedings; release a suspect on bail in accordance with the Criminal Procedure Code;

2/ Evidence produced by search conducted pursuant to sub-article 1(b) of this Article shall be acceptable by courts.

3/ A customs officer shall, in exercising his powers and duties specified under sub-article 1(c) of this Article, have the powers and duties vested in a police officer under the Criminal Procedure Code.

4/ A custom officer shall possess identification card and wear an officer uniform before he commences search in executing the customs laws. The search shall be undertaken by the same gender.

### 82. Power to Examine, Seize and Detain

1/ Any customs officer:

a) may enter into any means of transport and, except the personal effects of the master of the means of transport, identity, examine and seal goods subject to payment of duties and taxes and make them pass through customs formalities;

ለ) ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል በሚወጣ ማናቸውም ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመበት እቃ ስለመጫኑ በቂ መረጃ ወይም ጥርጣሬ ሲኖረው ማጓጓዣውን እና እቃውን በቁጥጥር ስር የማዋል ሥልጣን ይኖረዋል፤

ሐ) ቀረጥ ያልተከፈለባቸው እቃዎች በሚገኙበት ቦታ በመግባት የብር በራ ሥራ ለማከናወንና እቃዎቹን ለመያዝ ይችላል፤

መ) በጉምሩክ የማቋረጫ መስመሮችና የጠረፍ መስመሮች በሚንቀሳቀስ ማናቸውም ሰው፣ እቃና ማጓጓ ዣዎች ላይ ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፤

ሠ) በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣ ንና ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ የፌዴራል ፖሊስን ሊጠቀም ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ለተያዘ እቃ ባለቤት ወይም ሀላፊ የሆነ ሰው ያልተገኘለት ሲሆን ባለስልጣኑ የእ ቃው ባለቤት ወይም ሀላፊነቱን የሚ ወስድ ሰው እንዲቀርብ ወዲያውኑ በማስ ታወቂያ ይጠራል::

፫/ የተያዘው እቃ ባለቤት ወይም ሀላፊ የሆነ ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ፴ ቀን ውስጥ ካልቀረበ ወይም በዚሁ ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት ክስ ካልመሠረተ በእቃው ላይ የሚኖረው መብት ተቋርጦ እቃው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ መሠረት ይወገዳል::

## ፹፫. እሽጐችን የማንሳትና ቁልፎችን የመክፈት ሥልጣን

፩/ የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ሕግን ወይም ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ሕጎች በመተላለፍ በማናቸውም ማጓጓዣ ውስጥ የተገኙ እቃዎችን እሽግ የማን ሳት ወይም በቁልፍ የተዘጉ እቃዎችን የመክፈት ሥልጣን ይኖረዋል::

፪/ የጉምሩክ ሹም የጉምሩክ ሕግን ወይም ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ሕጎች በመተላለፍ የተደበቁ እቃዎች ይገኙበታል ተብሎ በተጠረጠረ ቦታ በመግባት እቃዎችን እሽግ በማንሳት ወይም በቁልፍ የተዘጉ እቃዎችን በመክፈት ፍተሻ ማድረግ ይችላል::

b) shall have the power to detain a means of transport where he has sufficient information or reasonable suspicion to believe that it is carrying import or export goods which have not undergone customs formalities and to seize the goods;

c) may enter any place where goods which have not undergone customs formalities are deposited and examine and seize the goods;

d) shall have the power to control the movement of any individual, goods and means of transport at customs crossings and in frontier strips;

e) may use the Federal Police in discharging his powers and duties under this Proclamation.

2/ Where goods are seized pursuant to the provisions of this Article in the absence of the owner or person responsible for them, the Authority shall immediately issue a notice to summon the owner or responsible person.

3/ If the owner or the responsible person failed to report to the Authority or to take the case to the court within 30 days since the first date the notice is issued, he shall lose his legal right to the goods and they shall be disposed pursuant to Article 31 of this Proclamation.

## 83. Power to Remove Seals and Open Locks

1/ A customs officer shall have the power to remove the packages or open the container of goods found in any means of transport in contravention of customs laws or other laws enforced by the Authority.

2/ A customs officer may enter any place where goods are believed to have been concealed in contravention of customs laws or other laws enforced by the Authority and examine the goods by removing their packages or opening their containers.

፫/ የጉምሩክ ሹም በቅድሚያ የራሱን ማንነት በአግባቡ ገልጾ በዚህ አንቀጽ መሠረት የእቃዎችን እሽግ በማንሳት ወይም በቁልፍ የተዘጉ እቃዎችን በመክፈት ፍተሻ ለማድረግ የሚመለከተውን ሰው ጠይቆ ፈቃድ ካላገኘ የፖሊስ ኃይል ሊጠቀም ይችላል::

**፹፬. <u>ሰነዶችን የመመርመርና በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥልጣን</u>**

፩/ የጉምሩክ ሹም ከዋጋ በታች በተገመቱ ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመባቸው እቃዎች ላይ የምርመራ ሥራ ለማከናወን በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኝ ሰነድ አስቀርቦ ሊመረምርና የሰነዶቹን ቅጂ ለመውሰድ ይችላል::

2/ የጉምሩክ ሹም በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ አገር የገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ እየተደረገ ያለ ዕቃ ስለመኖሩ በቂ መረጃ ወይም ጥርጣሬ ሲኖረው ዕቃውንና ዕቃውን የተመለከቱ ሰነዶችን ሊመረምር ይችላል::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የተመረመሩ ሰነዶች ለወንጀል ክስ በማስረጃነት የሚፈለጉ ሲሆን የጉምሩክ ሹም ሰነዶቹን በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥልጣን ይኖረዋል::

**፹፭. <u>በፖስታ እቃን የመክፈትና የመመርመር ሥልጣን</u>**

፩/ የጉምሩክ ሹም ለቀረጥና ታክስ ክፍያ አፈፃፀም ሲባል የፖስታ እቃዎችን ባለቤቱ ወይም ወኪሉ ወይም የፖስታ ድርጅቱ ተወካይ ባለበት የመክፈትና የመመርመር ሥልጣን ይኖረዋል::

፪/ የጉምሩክ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ምርመራ ውጤት መሠረት የፖስታ እቃን በቁጥጥር ሥር እንዲውል ማድረግ ወይም እንቅስቃሴውን መግታት ይችላል::

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም "ባለቤት" ማለት ለገቢ እቃ ተቀባዩ ወይም ለወጪ እቃ ላኪው ነው::

**፹፮. <u>የፌዴራል ፖሊስ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የፌዴራል ፖሊስ ይህን አዋጅ ወይም ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሌሎች ሕጐች በማስከበር ረገድ፣

3/ A customs officer may use the police force where he is denied to remove the packages or open the containers of goods for examination pursuant to the provisions of this Article after properly introducing himself to the concerned person.

**84. <u>Power to Examine and Seize Documents</u>**

1/ A customs officer may, while investigating cases of under invoiced goods or goods found without completing customs formalities, examine and take copies of documents under the possession of any person.

2/ A customs officer may, where he has sufficient grounds to believe that the law is violated with respect to imported or export goods, examine the goods and their documents.

3/ A customs officer shall have the power to seize documents examined pursuant to sub-article (1) or (2) of this Article where they are needed as evidence for instituting criminal proceedings.

**85. <u>Power to Open and Examine Postal Goods</u>**

1/ A customs officer shall, for the purpose payment of customs duties and taxes, have the power to open and examine postal goods in the presence of the owner of the goods or his agent or a representative of the post officer.

2/ The customs officer may seize or restrict the movement of postal goods upon the result of the examination conducted pursuant to the provisions of sub-article (1) of this Article.

3/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, the term "owner" means the consignee for import goods and sender for export goods.

**86. <u>Powers and Duties of the Federal Police</u>**

The Federal police shall, with respect to the enforcement of this Proclamation and other laws that are enforced by the Authority:

፩/ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን ይከላከላል፤ የኮንትሮባንድ እቃዎችን ይይዛል፣ ለባለሥልጣኑ ያስረክባል፤

፪/ የወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪዎችን አድኖ በመያዝ ለሕግ ያቀርባል፤

፫/ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለፍርድ ቤት ያቀርባል፤

፬/ ተላላፊ የጉምሩክ እቃዎችንና ተሽከርካሪዎችን ያጅባል፤

፭/ የጉምሩክ ሹም በሕግ የተሰጠውን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት የፖሊስ ኃይል መጠቀም ሲያስፈልገው ድጋፍ ይሰጣል፤

፮/ የፍተሻ ሥራ እንዳይከናወን የሚፈጠርን ሁከት በቁጥጥር ሥር ለማዋል ተገቢና ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ይጠቀማል፤

፯/ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው የባለሥልጣኑ ተቋማት፣ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና የጉምሩክ መጋዘኖች ጥበቃ ያደርጋል፤

፰/ ሕገወጥ እቃ ሊተላለፍባቸው በሚችሉ የአገሪቱ ድንበሮችና ኬላዎች ጥበቃ ያደርጋል።

## ፹፯. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

፩/ በዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን፣ ዋጋ አተማመን፣ አሰያየም፣ አመዳደብ ወይም በታሪፍ ልክ ላይ ተቃውሞ የቀረበ እንደሆነ የተቃውሞው ነጥብ ከተመዘገበ በኋላ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ቀረጡ ይከፈላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቀረጡን በተቃውሞ የከፈለ ሰው ክፍያ በፈጸመ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በባለሥልጣኑ ለተቋቋመው አቤቱታ አጣሪ ቡድን ማቅረብ ይችላል።

፫/ የባለሥልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ቡድን፣

ሀ) በዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን፣ ዋጋ አተማመን፣ አሰያየም፣ አመዳደብና በታሪፍ ልክ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፯ መሠረት በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች፣ እና

ሐ) ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በሚሰጡ ሌሎች አስተዳደራዊ ውሳኔዎች፣

ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ለዋና ዳይሬክተሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

1/ control contraband activities; seize contraband goods and hand over them to the Authority;

2/ apprehend criminal suspects and bring them to justice;

3/ Produce prosecutor's witnesses to the court of law;

4/ accompany customs transit goods and vehicles;

5/ where requested by customs officers, provide the necessary support in the discharge of their duties;

6/ use appropriate and proportional force to control any act of obstruction in conducting inspections;

7/ guard institutions, controlling stations and warehouse of the Authority, which require protection;

8/ guard customs check points and national frontiers through which illicit goods may cross border.

## 87. Complaint Handling Procedure

1/ Where any protest arises as to origin, valuation, commodity description, classification or tariff rate, the duties shall be payable in accordance with the decision of the Authority upon registration of the point of protest.

2/ A person who has paid duties under protest pursuant to sub-article (1) of this Article may appeal to a review committee established by the Authority, within 15 days after the date of payment.

3/ The review committee of the Authority shall examine complaints regarding:

a) origin, valuation, commodity description, classification and tariff rates;

b) administrative decision given in accordance with Article 107 of this Proclamation; and

c) other administrative decisions in respect completion of customs formalities;

and submit recommendations to the Director General.

፬/ በተቃውሞ ቀረጥ የከፈለ ሰው ባስመዘገበው ተቃውሞ መሠረት ውሳኔ የተሰጠለት እንደሆነ በትርፍ የተከፈለው ገንዘብ ውሳኔ በተሰጠ በ፴ ቀን ውስጥ ይመለስለታል::

፭/ በተቃውሞ ቀረጥ የከፈለ ሰው በዋና ዳይሬክተሩ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ውሳኔው በደረሰው ፴ ቀን ውስጥ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል::

፮/ ዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ካልቀረበ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል::

፯/ የግብር ይግባኝ ጉባኤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ በሕግ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል::

፰/ የግብር ይግባኝ ጉባኤ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረቡለትን ጉዳዮች መርምሮ ለመወሰን በገቢ ግብር አዋጅ የተሰጠው ሥልጣን ይኖረዋል::

፱/ የግብር ይግባኝ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔ በተሰጠ ፴ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል::

፲/ ሌሎች ስለይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት በገቢ ግብር አዋጅ የተመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቀርቡ ይግባኞችም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## ፹፰. የጉምሩክ ሹም መብት

ማንኛውም የጉምሩክ ሹም ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ለሚቀርብበት ክስ በባለሥልጣኑ ወጪ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኝ ወይም የባለሥልጣኑ ነገረፈጅ እንዲከራከርለት ይደረጋል::

4/ Where a decision is given in favor of the person who paid under protest, the excess amount of money paid shall be refunded within 30 days after the date of the decision.

5/ The person who paid duties under protest and is aggrieved by the decision of the Director General may lodge an appeal to the Tax Appeal Commission within 30 days after the date he received the decision of the committee.

6/ Where no appeal is lodged to the Tax Appeal Commission in accordance with sub-articles (5) of this Article, the decision of the Director General shall be final and conclusive.

7/ The Tax Appeal Commission shall examine and decide, in accordance with the law, on cases submitted to it within the time specified in sub-article (5) of this Article.

8/ The Tax Appeal Commission shall have the power granted to it in the Income Tax Proclamation to decide cases submitted to it in accordance with this Proclamation.

9/ Any party dissatisfaction with the decision of the Tax Appeal Commission may appeal to the Federal High Court within 30 days from the date of receipt of the decision of the Appeal Commission.

10/ Other appeal procedures prescribed by the Income Tax Proclamation shall be applicable to appeals presented pursuant to this Proclamation.

## 88. Right of Customs Officer

Any customs officer shall be entitled to the services of an advocate at the expense of the Authority or to be represented by the Authority's attorney in legal proceedings instituted against him in connection with any act committed in the course of properly discharging his official duties.

# ክፍል አራት
## በጉምሩክ ሥራ ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች
## ምዕራፍ አንድ
## በባለስልጣኑ ሠራተኞች ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

**፹፱. የሙስና ድርጊት**

ማንኛውም የጉምሩክ ሹም መደለያ በመቀበል፣ በዝምድና ወይም በሌላ የጥቅም ግንኙነት፣

፩/ የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም ቀረጥ ያልተከፈለበት ዕቃ ወደ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ ወይም ለማድረግ የሞከረ እንደሆነ፣

፪/ በሀሰተኛ ወይም በተጭበረበረ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ወይም ደጋፊ ሰነድ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈጸም፣ ቀረጥና ታክስ እንዲቀነስ ወይም እንዳይከፈል ያደረገ ወይም ለማድረግ የሞከረ፣ የተባበረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ድርጊቶችን የፈፀመ እንደሆነ፣

አግባብነት ባላቸው የወንጀል ህግ እና በስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የወንጀልና የማስረጃ የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል፡፡

**፺. በሥልጣን አላግባብ ስለመጠቀም**

በወንጅል ሕግ አንቀጽ ፬፻፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የጉምሩክ ሹም ወይም የፌዴራል ፖሊስ አባል ወይም በባለስልጣኑ ስራ በመተባበር የተሳተፈ ሰው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ወይም በቸልተኝነት፣

ሀ/ አገልግሎቶችን ያጓተተ፣ ዕቃዎች እንዲያዙ ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ፈጽመው እንዳይወጡ ያደ ረገ፣ ማጓጓዣዎች ከጉዞአቸው እን ዲስተጓጎሉ ያደረገ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ድርጊቶችን የፈጸመ እንደ ሆነ ወይም፣

ለ/ የተሰጠውን ሹመት ወይም ስልጣን በግልጽ ተግባር ወይም በግድፈት ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ ወይም፣

ሐ/ በግልጽ ከተሰጠው ስልጣን አልፎ የሰራ እንደሆነ ወይም፣

# PART FOUR
## OFFENCES AGAINST CUSTOMS ACTIVITIES
## CHAPTER ONE
## OFFENCES COMMITTEE BY CUSTOMS OFFICERS

**89. Corrupt Practices**

Any customs officer who, by receiving a bribe, by reason of nepotism or in consideration of any other unlawful benefit:

1/ allows or attempt to allow the importation or exportation of prohibited or restricted goods or goods on which duties are not paid;

2/ allows the completion of customs formalities on the basis of false or deceitful customs declaration or supporting documents, reduce or relief or attempt to reduce or relief payments of duties and taxes, cooperates in committing such acts or engages in similar activities;

shall be punishable in accordance with the relevant provisions the criminal law and of evidence and procedural law of the Federal Ethics and Anti Corruption Commission.

**90. Abuse of Power**

Subject to the provisions of sub- article 2 and 3 of Article 407 of the Criminal Code any customs officer or a member of the Federal Police or a person collaborate in the business of authority, with intent to inflict damage to person, to obtain for himself or to injure the right or interest of another or negligently:

a/ lags in providing services, seize goods or retard their customs clearance, disrupt the voyage of a means of transportation or commits other similar offences,

b/ misuses his official position or the power proper to his office, whether by a positive act or by a culpable omission, or

c/ exceeds the power with which he is officially invested, or

መ/ ስልጣኑ የማይፈቅድለትን ጉዳይ በተለይም ስልጣን ሳይኖረው ወይም ከስራው ከታገደ፣ከተዛወረ፣ ወይም ስልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኃላ የሰራበት እንደሆነ፣

ከሶስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

## ምዕራፍ ሁለት
## በሌሎች ሰዎች ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

### ፺፩. የኮንትሮባንድ ወንጀል

፩/ ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም ባለሥልጣኑ የሚያስፈፅማቸውን ሌሎች ሕጎች ወይም በነዚሁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገባቸው ወይም የጉምሩክ ሥነ-ስርአት ያልተፈፀመባቸው እቃዎች ወደ ጉምሩክ ክልል ካስገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ካስወጣ ወይም በህጋዊ መንገድ የወጡ እቃዎችን በህገወጥ መን ገድ መልሶ ካስገባ ወንጀሉ የተፈፀመባቸው እቃዎችና መሣሪያዎች እና የወንጀሉ ፍሬ መውረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከሰባት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንጽ (፩) ላይ በተመለከተው ሕገወጥ መንገድ የተገኙ እቃዎች መሆናቸውን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው እቃዎቹን ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የገዛ ማንኛውም ሰው በቅን ልቦና ለወንጀሉ ባዕድ የሆኑት ሰዎች መብት ሳይነካ ወንጀሉ የተፈፀመበት ዕቃና መሳሪያ እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በእቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንረዘብ መቀጫና ከሰባት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የዕቃው መወረስና የገንዘብ መቀጫው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፲፭ እስከ ፳ ዓመት ፅኑ እስራት ይቀጣል::

### ፺፪. በሕጋዊ እቃ ከለላነት የሚፈፀም የማጭበርበር ወንጀል

፩/ ማንኛውም ሰው በሕጋዊ እቃ ከለላነት፣

d/ performs official acts when he is not, or no longer, qualified to do so, especially in the case or in consequence of incompetence, suspension, transfer, removal from office or its cessation,

shall be punishable with rigorous imprisonment from 3 up to 10 years.

## CHAPTER TWO
## OFFENCES COMMITTED BY OTHER PERSONS

### 91. Contraband

1/ Any person who, in contravention of this Proclamation or other laws enforced by the Authority, including regulations and directives issued there under, imports or exports prohibited or restricted goods or without customs clearance or illegally imports duly exported goods shall, without prejudice to the forfeiture of the goods and equipments used in the commission of the offence and the proceeds thereof, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable on the goods and with rigorous imprisonment from 7 to 15 years.

2/ Any person who transports, stores, offers for sale or buys goods referred to in sub-article (1) of this Article while being or ought to have been aware of the illegality of their acquisition shall, without prejudice to the forfeiture of the goods and equipments used in the commission of the offence and the proceeds thereof without affecting the rights of third parties who transacted in good faith, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable on the goods and with rigorous imprisonment from 7 to 15 years.

3/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by the use of force or by an organized group with the offender the punishment shall be, without prejudice to the forfeiture of the goods seized and fine, from 15 to 20 years rigorous imprisonment.

### 92. Fraudulent Acts Committed under the Cover of Legally Declared Goods

1/ Any person who imports or exports or attempts to import or export:

ሀ) ክልከላ የተደረገበትን እቃ ወደ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ ወይም የሞከረ እንደሆነ ተቀላቅሎ የተገኘው የተከለከለ እቃና በሽፋንነት ያገለገለው እቃ በአንድነት መወረሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፪፻ሺ በማይበልጥ መቀጫና ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤

ለ) ገደብ የተደረገበትን እቃ ወደ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ ወይም የሞከረ እንደሆነ ተቀላቅሎ የተገኘው ገደብ የተደረገበት እቃና በሽፋንነት ያገለገለው እቃ በአንድነት መወረሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ገደብ በተደረገበት እቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከ7 እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፤

ሐ) ክልከላም ሆነ ገደብ ያልተደረገበትን ሌላ እቃ ወደ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ ወይም የሞከረ እንደሆነ ተቀላቅሎ የተገኘው እቃ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በእቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከ፯ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል::

፪/ በወንጀል ሕግ የተደነገጉት ቅጣቶች እና ተጨማሪ እርምጃዎች እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት የሆነ እንደሆነ የገንዘብ መቀጮው እጥፍ ይሆናል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ወይም ለጥፋቱ መፈጸም ምክንያት የሆነው ሌላ ሰራተኛ በድርጅቱ የተፈጸመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጣለው የገንዘብና የእስራት ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል::

፺፫. <u>ሌሎች የማጭበርበር ወንጀሎች</u>

፩/ ማንኛውም ሰው፣

ሀ) ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም በቀረበ ዴክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠበት እቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወይም አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ እንደሆነ፣

a) prohibited goods under the cover of legally declared goods shall, without prejudice to the forfeiture of both the prohibited and legally declared goods, be punishable with a fine from Birr 50,000 up to 200,000 and with rigorous imprisonment from 10 to 15 years;

b) restricted goods under the cover of legally declared goods shall, without prejudice to the forfeiture of both the restricted and legally declared goods, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable on the restricted goods and with rigorous imprisonment from 7 to 15 years;

c) goods other than prohibited or restricted goods under the cover of legally declared goods shall, without prejudice to the forfeiture of the intermingled goods, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable on the intermingled goods and with rigorous imprisonment from 7 to 15 years.

2/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by a corporate body the fine shall be, without prejudice of the punishment and additional measures stated under the Criminal Code, raised to be double.

3/ Save what is provided under sub-article 2 of this article, the manager of such cooperated body whose on duty by the time the offence has been committed and the employee to whom the commission such offence shall be attributed shall be deemed to have committed such offence and shall be punishable with fines and imprisonment provided under sub- article 1 of this article.

93. <u>Other Fraudulent Acts</u>

1/ Any person who:

a) imports or exports goods not registered or wrongly registered in a customs declaration and without the payment of customs duties and taxes or with the payment of reduced customs duties and taxes;

ለ) በእቃዎች የሥሪት አገር ላይ ተመሥርቶ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል ወይም አነስተኛ የቀረጥና ታክስ ክፍያ እንዲፈፀም ወይም የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚያደርግ ሀሰተኛ ማስረጃ ወይም መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ፣

ሐ) ሰነዶችን የደለዘ፣ የሰረዘ፣ የፋቀ ወይም አስመስሎ የሠራ እንደሆነ፣ ወይም

መ) በሌሎች ማናቸውም ሁኔታዎች ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዳይከፈል የሚያደርግ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፣

ማስረጃ ያልቀረበበት ወይም ሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠበት እቃ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በእቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከሰባት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት የሆነ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል::

## ፺፬. <u>የባለስልጣኑን ሰነዶችና መለያዎች ወደሀሰት ስለመለወጥ</u>

ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፣

፩/ ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበትን ቅጽ፣ ማህተም፣ መታወቂያ፣ ዓርማ ወይም ማንኛውም ምልክት አስመስሎ የሠራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም በእጁ ይዞ የተገኘ እንደሆነ ከብር ፲ሺ እስከ ፳ሺ በሚደርስ መቀጫና ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፪/ ባለሥልጣኑ የሚጠቀምበትን የደንብ ልብስ አስመስሎ የሠራ ወይም ይህንኑ ያከፋፈለ፣ የተጠቀመ ወይም በእጁ ይዞ የተገኘ እንደሆነ ከብር ፭ሺ እስከ ፲ሺ በሚደርስ መቀጫና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

b) provides false documents or information in relation to the country of origin of goods with the purpose to evade the payment of customs duties and taxes or to obtain reduction or refund of customs duties and taxes;

c) deletes, cancels, erases or forges documents; or

d) commits any mischievous acts to evade the payment of customs duties and taxes; shall, without prejudice to the forfeiture of the goods undeclared or those in respect of which false information is presented, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable on the goods and with rigorous imprisonment from seven to ten years.

2/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by a corporate body, provisions of sub-article (2) and (3) of article 92 of this proclamation shall be applicable.

## 94. <u>Falsifying Documents and Symbols of the Authority</u>

Any person who, with intent to cause damage to the Authority or to procure undue advantage for himself or for any other person:

1/ falsifies forms, seal, identity cards, emblem or any other symbol of the Authority or distributes, uses or possesses same shall be punishable with a fine from Birr 10,000 up to Birr 20,000 and with rigorous imprisonment from five to ten years;

2/ imitates uniforms used by the Authority or distributes, uses or possesses same shall be punishable with a fine of Birr 5,000 up to 10,000 and with rigorous imprisonment form three to five years.

## ፺፭. <u>እሽጐችን ስለመፍታትና ምልዕክቶችን ስለማንሳት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የባለ ሥልጣኑ ሹም ፈቃድ ሳያገኝ፣

ሀ) በመተላለፍ ላይ ያሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ማጓጓዣዎች ወይም የዕ ቃዎች መያዣ ላይ የተደረገውን ማሽ ጊያ የፈታ ወይም ያላቀቀ እንደሆነ፣

ለ) በዕቃው ወይም በዕቃው መያዣ ላይ የተደረገውን ምልክት ያነሳ፣ የፋቀ፣ የሰረዘ ወይም የለወጠ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ) መያዣውን ከፍቶ ወይም ሰብሮ አንዱን ዕቃ ከሌላው የደባለቀ ወይም ያጎደለ እንደሆነ፣

ጥፋቱ በሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከብር ፭ሺ እስከ ፲ሺ በሚደርስ መቀጫና ከ፯ ዓመት እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የፅኑ እስራት ቅጣቱ ከአስር እስከ አስራ አምስት ዓመት ከፍ ይደረጋል፡፡

## ፺፮. <u>መደለያ ስለመስጠት</u>

፩/ የጉምሩክ ሹም ወይም የፌዴራል ፖሊስ በጉምሩክ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የታዘዘውን እንዳይፈጽም ወይም የተከለ ከለውን እንዲያደርግ መደለያ የሰጠ ወይም መደለያ እንዲሰጥ ወይም እንዲቀበል ያደረገ ማንኛውም ሰው ከብር ፶ሺ እስከ ፩፻ሺ በሚደረስ መቀጫና ከ፯ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ድርጊት የፈጸመ ሰው ዕቃው ከጉምሩክ ከመውጣቱ በፊት ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር አድራጐቱን ለሚመለከተው አካል ካስታወቀ በወንጀሉ ላይከሰስ ይችላል፡፡

## 95. <u>Opening of Parcels and Removal of Marks</u>

1/ Any person, who, without being Authorized by the appropriate customs officer:

a) removes or disconnects the fastenings affixed on a means of transport or container of goods;

b) removes, defaces, cancel or alter labels affixed on goods;

c) open or break containers and mix up or remove goods;

during transit or arrival at customs port, shall, unless a server penalty is imposed by other laws, be punishable with a fine from Birr 5,000 up to Birr 10,000 and with a rigorous imprisonment from 7 to 10 years.

2/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by the use of force or by an organized group the rigorous imprisonment shall extend from ten to fifteen years.

## 96. <u>Soliciting of Corrupt Practices</u>

1/ Any person who bribes a customs officer or police officer, or induces the offer or acceptance of such bribe, with intent to procure him to perform or omit an act in violation of customs laws, regulations or directives shall be punishable with a fine of Birr 50,000 up to Birr 100,000 and with rigorous imprisonment from 7 to 15 years.

2/ Any person who has committed an offence specified under sub-article (1) of this Article may not be prosecuted where he reports to the concerned body the commission of the offence with tangible evidence before the goods are released from customs.

## ፺፯. የጉምሩክ ሥራ አፈፃፀምን ስለማሰናከል

፩/ ማንኛውም ሰው ያለበቂ ምክንያት፣ የጉምሩክ ሹም ሰነዶችን እንዳይመረመር ወይም ማጓጓዣዎችን ወይም ዕቃዎችን እንዳይፈተሽ ወይም ወደ መጋዘን፣ የንግድ መደብር ወይም መኖሪያ ቤት እንዳይገባ ያደረገ ወይም ሁከት የፈጠረ ወይም ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያልሰጠ ወይም ለምርመራ ያልተባበረ ወይም በማናቸውም መንገድ ሥራውን ለማደናቀፍ ጣልቃ የገባ እንደሆነ ከብር ፭ሺ እስከ ፲ሺ በሚደረስ መቀጮና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ወንጀል የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ የእስራት ቅጣቱ ከአምስት እስከ አስር ዓመት ጽኑ እስራት ከፍ ይደረጋል::

## ፺፰. ከቀረጥ ነፃ በገባ ዕቃ አላግባብ መገልገል

፩/ በሌላ ሕግ ወይም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባን ዕቃ ይህንን አዋጅ በሚቃረን ሁኔታ፣

ሀ) የቀረጥ ነፃ መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጭ በሌላ አገልግሎት ላይ ያዋለ ወይም ለሌላ ሰው ያስተላለፈ ወይም በማናቸውም መልኩ ከቤተሰብ ውጭ በሌሎች ሰዎች አገልግሎት ወይም ይዞታ ሥር እንዲውል ያደረገ፣ ወይም

ለ) ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የገዛ፣ የተቀበለ፣ የተገለገለ፣ ያስተላለፈ ወይም ለሌሎች ሰዎች ግልጋሎት እንዲውል ያደረገ፣

ማንኛውም ሰው የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው በገባ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጮና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል::

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) አፈጻጸም "ቤተሰብ" የሚለው ቃል የባለመብቱን የትዳር ጓደኛ፣ ልጆችና ወላጆችን ብቻ ያጠቃልላል::

## 97. Obstruction of Customs Formalities

1/ Any person who, without good cause, obstructs or hinders the duties of a customs officer in the investigation of documents or the inspection of a means of transport or goods, prohibits him from entering a warehouse, a business premise or a dwelling house, refuses to reply to the inquiries of the customs officer, resists to co-operate for investigation or interferes by any means so as to obstruct the duties of the customs officer shall be punishable with a fine of Birr 5,000 up to 10,000 and with imprisonment from 3 to 5 years.

2/ Where the offence referred to in sub-article (1) of this Article is committed by the use of force or by an organized group the imprisonment shall extend from five to ten years rigorous imprisonment.

## 98. Misuse of Duty Free Goods

1/ Unless otherwise provided by other laws or treaties ratified by Ethiopia, any person who, in violation of this Proclamation:

a) uses duty free goods or goods imported on the basis of reduced duty and tax rates for purposes other than which the duty relief is granted or transfers them to another person or places them, in any manner, under the service or possession of other persons outside of his family; or

b) while being or should have been aware of the facts, buys, receives, uses, transfers or places such goods under the services of others;

shall, without prejudice to the forfeiture of the goods, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable when such good were imported and with imprisonment from 3 to 5 years.

2/ For the purpose of sub-article 1(a) of this Article, the term "family" includes only the spouse, children and parents of the right holder.

**፺፱. ሕገ-ወጥ ዕቃዎችን ይዞ ስለመገኘት**

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ይዞ ከተገኘ የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕቃው ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**፻. ናሙናዎችን አለመመለስ**

ማንኛውም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ለናሙና የወሰደውን ዕቃ ያልመለሰ ወይም በዕቃው የተገለገለ ወይም ዕቃው እንዲጠፋ ያደረገ እንደሆነ የዕቃውን ዋጋ፣ ቀረጡንና ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፫ሺ እስከ ብር ፭ሺ በሚደርስ መቀጫና ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**፻፩. የመጓጓዣ ኃላፊ ግዴታዎችን ስለመጣስ**

፩/ ማንኛውም የመጓጓዣ ኃላፊ፣

ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንገደኞችን ወይም የዕቃ ጭነት መግለጫ ካላቀረበ፣

ለ) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ መጓጓዣው እንዲጠጋ ካደረገ፣ ወይም

ሐ) መጓጓዣው ከጉምሩክ ወደብ እን ዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሹም ሳያስረዳና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ፣

ከብር ፪ሺ እስከ ብር ፭ሺ በሚደረስ መቀጫ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም የመጓጓዣ ኃላፊ ጉምሩክ ወደብ በደረሰ መጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ዕቃ የጫነ ወይም ያራገፈ ወይም ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሙከራ ያደረገ እንደሆነ ከብር ፯ሺ እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጫና ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

**99. Possession of Unlawful Goods**

Without prejudice to other provisions of this Proclamation, any person who, knowing or ought to have known the fact, possesses prohibited or restricted goods or goods that have not undergone customs formalities shall, without prejudice to the forfeiture of the goods, be punishable with a fine equivalent to the amount of the customs duties and taxes payable on the goods and with rigorous imprisonment from three to five years.

**100. Failure to Return Samples**

Any person who, with intent to procure undue advantage for himself or for any other person or with intent to cause damages to others, fails to return samples of goods or who uses or damages them, shall, without prejudice to the payment of the value of the goods and duties and taxes payable on the goods, be punishable with a fine from Birr 3000 up to Birr 5000 and with rigorous imprisonment from two to five years.

**101. Contravention by Master of Means of Transport**

1/ The master of any means of transport who:

a) fails to submit passengers' or cargo manifest within the specified time;

b) gives access to any unauthorized person to the means of transport; or

c) delays the departure of the means of transport from the customs port without notifying and getting permission from the customs officer;

shall be punishable with a fine from Birr 2,000 up to 5,000.

2/ The master of any means of transport who load or unload or attempt to load or unload goods in the absence of customs officer shall be punishable with a fine of Birr 7,000 up to Birr 10,000 and with imprisonment from 5 to 7 years.

፫/ ማንኛውም የመጓጓዣ ኃላፊ ከውጭ አገር የሚመጡ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ወደብ ውጭ ካራገፈ ወይም ከጫነ ወይም ለማራገፍ ወይም ለመጫን ከሞከረ የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፯ሺ. እስከ ብር ፲ሺ. መቀጮና ከሰባት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል::

፻፪. <u>የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው ግዴታን ስለመጣስ</u>

የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ባለፍቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፮ የተደነገጉትን ግዴታዎች ሳይፈጽም የቀረ እንደ ሆነ ከብር ፶ሺ. እስከ ብር ፻ሺ. የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ተቀጥቶ ፈቃዱ ሊሠረዝ ይችላል::

፻፫. <u>ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ የሚያስከትለውን ግዴታ ስለመጣስ</u>

ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ የሚያካሂድ ሰው በተፈቀደለት የመተላለፊያ መንገድ ላይ ለሚገኝ ወይም መተላለፍ ለሚያበቃበት የጉምሩክ ጣቢያ በተወሰነው ጊዜ መድረሱን ያላስታወቀ እንደሆነ ከብር ፭ሺ. እስከ ብር ፳ሺ. መቀጫ ተቀጥቶ ፈቃዱ ይሰረዛል::

፻፬. <u>ጥፋተኛ ወይም ነፃ የማድረግ ውሳኔ በውርስ ላይ የሚኖረው ውጤት</u>

፩/ ማንኛውንም እቃ ወይም ማጓጓዣ ሊያ ስወርስ በሚችል ወንጀል በተከሰሰ ሰው ላይ የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሰጠ ተጨማሪ ትዕዛዝ መስጠት ሳያስፈልግ እቃው ወይም ማጓጓዣው እንዲወረስ ይደረጋል::

፪/ መወረስ ያለበት እቃ ወይም ማጓጓዣ የጠፋ ወይም ያልተገኘ ከሆነ ተከሣሹ እቃው ወይም ማጓጓዣው ቀረጥ ተከ ፍሎ የሚያወጣውን ዋጋ ያህል ገንዘብ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል::

፫/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው በነፃ የተሰናበተ ከሆነ ፍርድ ቤቱ፣

ሀ) እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉም ሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካገኘው የው ርስ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

3/ The master of any means of transport who unloads or loads or attempts to unload or load import or export goods at a place other than a customs port shall, with out prejudice to the forfeiture of the goods, be punishable with a fine from Birr 7,000 up to Birr 10,000 and with rigorous imprisonment from 7 to 15 years.

102. <u>Contravention by the Warehouse Licensee</u>

A licensee who has failed to discharge the obligations stated under article 76 of this proclamation may punish with a fine of Birr 50,000 to 100,000 and his license may be revoked.

103. <u>Contravention in Relation to Transit of Goods</u>

Any person engaged in the transit of goods fails to arrive and report within the specified time to customs station in route or at the customs port of destination about goods in transit shall be punishable with a fine of Birr 5,000 to 20,000 and his license shall be revoked.

104. <u>Effects of Conviction or Acquittal on Forfeiture</u>

1/ Any goods or means of transport shall, without further order, be forfeited upon the conviction of a person accused of an offence entailing forfeiture of such goods or means transport.

2/ If any goods or means of transport liable to forfeiture is lost or can not be found the court may order the offender to pay an amount equal to the duty paid value of such goods or means of transport.

3/ Where a person prosecuted for violation of the provisions of this Proclamation is acquitted the court:

a) shall order the goods or means of transport seized be forfeited where it is satisfied that the provisions of this Proclamation are not observed in respect of such goods or means of transport;

ለ) እቃው ወይም ማጓጓዣው የጉምሩክ ሕግን የመተላለፍ ድርጊት የተፈጸመበት ስለመሆኑ የቀረበለት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው ተገቢው ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት እቃው ወይም ማጓጓዣው ለባለቤቱ ወይም ለተያዘበት ሰው እንዲመለስ ያዛል፤ ወይም

ሐ) የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት እቃ በተከሣሹ ወጪ ከአገር ተመልሶ እንዲወጣ ሊያዝ ይችላል::

b) shall order the release the goods or means of transport upon payment of duties and taxes or give such other orders it deems appropriate where it is not satisfied that the provisions of this Proclamation are breached in respect of such goods or means of transport; or

c) may order the re-export of prohibited or restricted goods at the expense of the accused.

## ፩፻፭ የውርስ ውሳኔ ሽፋን

በዚህ አዋጅ መሠረት የተላለፈ የውርስ ውሣኔ የውርስ ውሣኔ ያረፈበት እቃ የተሸፈነበት፣ የተጠቀለለበት ወይም የተከተተበትን መያዣ፣ ለሽፋንነት ወይም ለመደበቂያነት ያገለገሉትን ሌሎች እቃዎችን እና ለእቃው ወይም ለመጓጓዣው በባለስልጣኑ የተያዘውን ዋስትና ጭምር ይመለከታል::

## 105. Coverage of Forfeiture

The forfeiture of goods under this Proclamation shall extend to the package in which such goods are covered, wrapped or contained, other goods that have served to cover or conceal such goods and any security retained by the Authority in respect of such goods or means of transport.

## ፩፻፮. ተከሣሽ በሌለበት ክስ ስለመስማት

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገ ወንጀልን በሚመለከት የቀረብ ክስ ተከሣሹ በሌለበት ሊሰማ ይችላል::

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አፈጻጸም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ያሆናል::

## 106. Proceedings in the Absence of the Accused

1/ Offences provided under this Proclamation may be tried in the absence of the accused.

2/ The Criminal Procedure Code shall, where appropriately be applicable for the purpose of application of sub- article 1 of this Article.

## ፩፻፯. በጉምሩክ ስራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሳኔ ስለመጨረስ

፩/ ኮንትሮባንድ ወይም መከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ውስጥ ከ፳፭በመቶ ወይም ከብር ፭፻ሺ የሚበልጥ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸውን ሳይጨምር በጉምሩክ ስራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ባህሪና በሕዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአስተዳደራዊ ውሣኔ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

፪/ አስተዳደራዊ ውሣኔ የሚሰጥባቸው የጉምሩክ ወንጀሎች ዓይነት፣ የሚወሰዱ የቅጣት እርምጃዎችና የውሣኔ አሰጣጡ ሥነ ሥርዓት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

## 107. Administrative Settlement of Customs Offences

1/ The Authority is hereby empowered to settle customs offences, other than those relating to contraband or involving above 25% or Birr 500,000 of the payable duties and taxes, administratively by taking due account on the nature of the offences and their impact on the interests of the public and government.

2/ The categories of customs offences subject to administrative settlement, the types penalties and procedures of such settlement shall be prescribed by a directive to be issued by the Authority.

፫/ ባለስልጣኑ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሣኔ ላይ ቅሬታ የሚኖረው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፯ መሰረት የባለሥልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ቡድን ውሣኔ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል። የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## ፻፰. የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት

በወንጀል ሕግ ወይም በሌላ ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ቅጣቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፻፱. የመያዝና በቁጥጥር ሥር የማዋል ሥልጣን

፩/ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን አግባብ ያለው የመጨረሻ ሕጋዊ ውሣኔ እስከሚሰጥባቸው ድረስ መያዝና በቁጥጥር ሥር ማዋል ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የማጓጓዣው ባለቤት የተፈጸመው ወንጀል ከራሱ ዕውቀት ወይም ፈቃድ ውጪ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ የተፈፀመው ወንጀል ክብደት እየታየ ከብር ፲ሺ እስከ ብር ፶ሺ ተቀጥቶ ማጓጓዣው ይመለስለታል። ዝርዝር አፈፃፀሙ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ዓላማ "ባለቤት" የሚለው ቃል ተከራይን አይጨምርም።

## ፻፲. የጉምሩክ ቅጾች

፩/ ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ቅጾችን ማዘጋጀትና ማሳተም የሚችለው ባለሥልጣኑ ብቻ ይሆናል።

፪/ በባለሥለጣኑ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው የጉምሩክ ቅጾችን መያዝና ማከፋፈል አይቻልም።

3/ Any person who is aggrieved by the administrative settlement of the Authority may appeal to the Tax Appeal Commission within 30 days after receiving the decision of the review committee of the Authority pursuant to Article 87 or this Proclamation. The decision of the Tax Appeal Commission shall be final.

## 108. Applicability of other Laws

Unless otherwise higher penalties provided in the Criminal Code or other laws, penalties provided under this proclamation shall be applicable.

# PART FIVE
# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 109. Power of Seizure and Detention

1/ The Authority may seize and detain, until the appropriate final decision is given, goods and means of transport with respect of which offenses under this Proclamation are committed.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, where the owner a means of transport proves that the offense is committed without his knowledge or consent, the means of transport shall returned to him upon being penalized with a fine from Birr 10,000 up to Birr 50,000 depending on the magnitude of the offence. The detailed application of this provision shall be prescribed by directives of the Authority.

3/ For the purpose of sub-article (2) or this Article the term "owner" shall not include a lessee.

## 110. Customs Forms

1/ Forms necessary for the completion of customs formalities shall be prepared and published only by the Authority.

2/ Unless with due authorization of the Authority, possession and distribution of customs forms shall be prohibited.

## ፩፻፲፩. መረጃ ስለመስጠት እና አቤቱታ ስለማቅረብ

፩/ ባለስልጣኑ ከጉምሩክ ጋር የተያያዙ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ስርዓቶች የኤሌክትሮኒክ ዘዴዎችን ጨምሮ በልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎች እንዲሰራጩ ያደርጋል::

፪/ ዕቃዎችን ወደአገር ውስጥ የሚያስገባ ወይም ወደውጭ አገር የሚልክ ማንኛውም ሰው ወይም ማንኛውም የሚመለከተው ወገን የጉምሩክ መመሪያዎችን አፈፃፀም በተመለከተ ያለምንም ክፍያ ከባለሥልጣኑ መረጃ ለማግኘት ይችላል::

፫/ ማንኛውም ሰው በጉምሩክ አሠራር ላይ ቅሬታ ካለው አቤቱታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፤ ላቀረበው አቤቱታም በጽሁፍ ምላሽ የማግኘት መብት ይኖረዋል::

## ፩፻፲፪. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

፪/ ባለስልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

## ፩፻፲፫. የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች

፩/ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደ ገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷/፲፱፻፺፱ (እንደ ተሻሻለ)፣ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፭/፲፱፻፺፩ እና አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፰/፲፱፻፺፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል::

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም::

## ፩፻፲፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተመሰረቱ የወንጀል እና የፍትሐ ብሄር ክሶች በነበረው ሕግ መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ::

## 111. Providing Information and Complainant

1/ The Authority shall disseminate laws, regulations, directives and operational procedures related to customs using various communication media including electronic media.

2/ Any person importing or exporting goods or ay interested party may get information concerning the application of customs rules from the Authority without being charged.

3/ Any person dissatisfied with the treatments of customs may lodge his complaints to the Authority, and shall be entitled to a written reply.

## 112. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

## 113. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Re-Establishment and Modernization of Customs Authority Proclamation No. 60/1997, Proclamation No 125/1998 and Proclamation No. 368/2003 are hereby repealed.

2/ No law, regulations, directives or practices shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 114. Transitory Provisions

1/ Criminal or civil cases instituted prior to the coming effect of this Proclamation shall be disposed in accordance with the previous laws.

፪/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በእንጥልጥል ላይ ያሉ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሰረት ውሳኔ ሊያገኙ ይችላሉ::

፫/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ ደንቦችና መመሪያዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል::

## ፻፲፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2/ Cases to be settled by administrative decision that have been pending prior to the coming into effect of this proclamation shall be settled in accordance with the provisions of this proclamation.

3/ Existing regulations and directives shall, in so far as they are consistent with provisions of this Proclamation, continue in force until replaced by regulations and directives issued hereunder.

## 115. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of February, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት